የቀዶ ጥገና ህክምና ክፍሉን ለቅቄ የወጣሁት የዴቪድ ጀንቲሊስና በሌሎች ፀሎት ነበር፡፡ “እኛ ይህንን እንወጣዋለን፡፡ ለመኖር አንተ ማድረግ የሚገባህ ነገር የለም፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ እኛ እንጸልያለን”

እንደማልሞት እያወቅኩ መጣሁ፡፡

የእግዚአብሔር ሰዎች እንድሞት አልፈቀዱም፡፡



# 8 የሕመም ሥቃይና ማስተካከያዎች

“እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ፤ እኔ አምላክህ ነኝና አትደንግጥ፣ አበረታሃለሁ፤ እረዳህማለሁ፤ በጽድቄም ቀኝ ደግፌ እይዝሃለሁ፡፡”

ኢሣ 41፥10

ምንም እንኳን ሆን ብለው ባይሆንም፤ ጠያቂዎች ሁኔታዬ እንዲባባስ ምክንያት ሆኑ፡፡ ስለ እኔ ግድ ያላቸው ነበሩ፤ እናም ያንን ስሜታቸውን ለመግለጽ ይፈልጉ ነበር፡፡ ለእኔ ግድ ያላቸው በመሆኑ ምክንያት በዓለም ላይ የተለመደውን ነገር ነበር የሚያደርጉት፡፡ ይጎበኙኝ የነበረው በህክምናው ሆስፒታል ውስጥ በነበረው የመኝታ ክፍሌ ነው፡፡ ችግሩ ደግሞ ያ ነበር፡፡

በክፍሌ ውስጥ የሚፈጠረው የማያቋርጥ የመግባትና የመውጣት እንቅስቃሴ አሰልቺ ሆኖብኝ ነበር፡፡ እዚያ ተኝቼ እንዲቀመጡ በማድረግ ላጫውታቸው አልችልም፡፡ ምናልባትም እንደ ቤተክርስቲያን መጋቢነቴ መጫወት የሚገባኝን ሚና መጫወት ወይም እነርሱን ለማዝናናት የተወሰነ የሃላፊነት ስሜት ይሰማኝ ነበር፡፡ ጠያቂዎቼን ክፍሉን ለቀው እንዲወጡ በመጠየቅ ወይም ዳግመኛ እንዳይመጡ በመናገር የማንንም ስሜት መጉዳት አልፈለግኩም፡፡

ብዙ ጊዜ ምንም እንኳን ፍላጎቴ ጥቅልል ብሎ መተኛት ቢሆንም ያለውዴታ ፈገግታ አሳያቸዋለሁ ወይም አዋራቸዋለሁ:: አንዳንድ ጊዜም እጅግ ከባድ የሆነው የህመም ስቃዬ መልካም እንግዳ ተቀባይ ልሆን አያስችለኝም፤ ይሁን እንጂ በዚያ ሁኔታ ውስጥ ሆኜም ደስተኛ ለመምሰል እጣጣራለሁ:: ለእኔ እንደሚያስቡልኝና እኔን ለማየት ብዙ ዋጋ ከፍለው እንደመጡ ራሴን ማሳሰብ ቀጠልኩ::

በወዳጆቼ፣ በዘመዶቼና በቤተክርስቲያን አባላት ከሆስፒታሉ የመግቢያ በር እስከ መኝታ ክፍሌ ድረስ ያለው ሰልፍ እየተሳበ የሚሄድ ነው የሚመስለው:: ኢቫ አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ ስትመጣ ጠያቂዎቼ ምን ያህል ችግር እንደፈጠሩብኝ ተገነዘበች:: እንዲህ እስኪሆን ድረስ ዝም በማለቴ ገሰጸችኝ::

እንደተረዳሁት ሰዎቹን ተመልሰው እንዳይመጡ እንዳልነገርኳቸው የገመተች ይመስለኛል፤ ስለዚህ ወደ ነርሶቹ በመሄድ የሚፈቅዱላቸውን ጠያቂዎች ቁጥር እንዲቀንሱ ጠየቀቻቸው:: ሁሉንም ሰዎች ከመምጣት አላገዳቸውም፤ ይሁን እንጂ ወደክፍሉ የሚገባውንና የሚወጣውን የሰው ቁጥር በጥቂቱ ጋብ አደረገው::

በሰውነቴ ላይ ከደረሰው ስቃይና ህመም እንዲሁም ከገቢውና ከወጭው ሀዝብ በተጨማሪም በድብርት ውስጥ ነበር የምኖረው:: የዚህ ትልቁ ምክንያት በደረሰብኝ ድንገተኛ አደጋ ሊከሰት የሚችል ድብርት ሲሆን፤ በጥቂቱም የምወስዳቸው መድሃኒቶች ካስከተሉት ተጽእኖ ሊሆን ይችላል:: ይሁን እንጂ እኔ እንደማምነው የውጤቱ መጨረሻ ያልታወቀና ማስቂያ የሌለው የህመም ስቃይ የተጋፈጥኩ በመሆኑ፤ ወደፊት ብሩህ ቀን ይጠብቀኛል የሚል ተስፋ ከውስጤ በመጥፋቱ



ይመስለኛል:: ብዙውን ጊዜ በሕይወት ለመኖር በፍጹም አልፈልግም ነበር::

ፍጹምነት ከሞላው መንግስተ ሰማይ በምድር ወዳለ ስቃይ ወደሞላበት ሕይወት ለምንድነው ተመልሼ እንድመጣ የተደረገው? ምንም ያህል አጥብቄ ብሞክርም፤ ሕይወቴ እንደገና ደስተኛ ሊሆን አልቻለም፤ እንደገና ወደ መንግስተ ሰማይ መሄድ እፈልግ ነበር::

የህመም ስቃይ ከአደጋው በኋላ የሕይወቴ አንድ አካል ሆነ፤ እርግጠኛ ነኝ ይህ ነገር በብዙዎችም ላይ ደርሷል:: በዚህ ሁኔታ ውስጥ መኖርን መለማመዳችን ደግሞ አስደናቂው ነገር ነው:: አሁን እንኳን በአንዳንድ አጋጣሚዎች ሌሊቱን መልካም እንቅልፍ ተኝቼ ከነቃሁ በኋላ በአልጋዬ ላይ ተጋድሜ፤ የትኛውም ቦታ ላይ ያልተጎዳሁ መሆኔን በድንገት ማሰብ እጀምራለሁ:: ከዚያ በኋላ ደግሞ የቀኑን ሃያ ሦስት ሰዓትና ሃምሣ አምስት ደቂቃዎች በማያቋርጥ የህመም ስቃይ ውስጥ እየኖርኩ እንደሆነ እንዳስብ እደረጋለሁ::

ያለሁበት ሁኔታዬ በስነልቡናዬ ላይ ያስከተለውን ከፍተኛ ተጽእኖ የተረዳሁት ጥቂት ዘግየት ብሎ ነበር::

እጸልያለሁ፤ ሰዎችም አብረውኝ ይጸልያሉ፤ ይሁን እንጂ ውስጤ ፈጥኖ ተስፋ ይቆርጥና፤ "አሁን ይሄ ሁሉ አስፈላጊ ነው?" እያልኩ በቀኑ ውስጥ ብዙ ጊዜ ራሴን እጠይቃለሁ::

ዶክተሮቹና ነርሶቹ ድብርቱን ከእኔ ላይ ለማስወገድ መድሃኒቶችን አብዝቼ እንድወስድ ያበረታቱኝ ነበር፤ እኔ ግን ተቃወምኩ:: ለምን

እንደዚያ እንዳደረኩ እርግጠኛ አይደለሁም። ምናልባትም በርካታ መድሃኒቶች የወሰድኩ በመሆኑ ከዚያ በላይ ባለመፈለጌ ሊሆን ይችላል። ከዚህም በላይ ከዚያ በላይ ተጨማሪ መድሃኒት የሚፈይደው ነገር እንደሌለ አስባለሁ።

አሁን በሕይወቴ እየሆነ ካለው ውስብስቡ ከወጣ ሕይወት ነፃ መሆንና መሞት እፈልግ ነበር። ነገሮች ስለሚለወጡበት ጉዳይ ለማሰላሰል ሙሉ ለሙሉ ብቃት እንዳልነበረኝ ግልጽ ነበር። አሁን አንድ ነገር ደግሞ ተገነዘብኩ በድብርት ውስጥ ገብቻለሁ።

ፈጥኖ ሁሉም ሰው ያለሁበትን ይህንን ሁኔታ አወቀው።

"የስነ አዕምሮ ጠቢብ ማነጋገር ትፈልጋለህ? " ሲል ዶክተሬ ጠየቀኝ።

"አልፈልግም" ስል መለስኩለት።

ከጥቂት ቀናት በኋላ አንዷ ነርስ እንዲህ ስትል ጠየቀችኝ፤ "አማካሪ ሃኪም እንድጠራልህ ትፈልጋለህ? ሊያማክርህ የሚችል አንድ ሰው?"

የኔ መልስ የተለመደው ነበር።

ማንንም ሰው ማነጋገር የማልፈልግ በመሆኑ "አደጋ ጣይ የአዕምሮ ጠበብት" ብዬ የምጠራቸው ወደ ክፍሌ በዝግታ ይገቡ ጀመር።

"በጣም ከፍተኛ አደጋ እንዳጋጠመህ አያለሁ" አለኝ አንድ በስውር የመጣ የሥነ አዕምሮ ጠበብት የሐኪሙን ዘገባ ካነበበ በኋላ።



"ስለ አደጋው ምንም አይነት ነገር ማውራት አልፈልግም" አልኩት እውነቱ ደግሞ ስለማልችል ነበር። ከዚህ ምድር ተለይቼ በሄድኩባቸው ዘጠና ደቂቃዎች ውስጥ የሆነውን ነገር ለእያንዳንዱ ሰው እንዴት መግለጽ እችል ነበር? የማይገለጸውን ነገር ለመግለጽ ቃላትን ከየት መፈለግ እችላለሁ? እውነታዊ በሆነ ቋንቋ መንግስተ ሰማይ ስለመሄዴ ጉዳይ እንዴት መግለጽ እንደምችል አላውቅም። በዚያ መንገድ መናገር ጀምሬ ቢሆን ኖሮ በጣም እርግጠኛ ነኝ ወደ እብደት እንደማመራ አውቃለሁ።

እጅግ በሚያስከፋ ሁኔታ በአዕምሮዬ ላይ አንዳች ችግር እንደደረሰ ያስብ ነበር። ይሄ ችግር ደግሞ ያልተፈጠረና የሌለን ነገር እንደሆነና እንደተፈጠረ አድርጎ በአዕምሮ የመሳልና የማሰብ ችግር በመሆኑ፤ ይህንን ቅዥት ለማስወገድ ብርቱ መድሃኒት መውሰድ እንደሚገባኝ ደምድሟል። በሕይወት ዘመኔ ሁሉ ከተለማመድኩት ደስታ ይልቅ የላቀውንና ካየሁት ኃያል ነገር ሁሉ የበለጠውን ያንን እውነታ በምን ቃላት ልገልጸው እችላለሁ? ይህን ሁሉ ካየሁ በኋላ ሞት መምረጤን በመናገሬ እንዴት አዕምሮዬን እንደሳትኩ እቆጠራለሁ? እኔ ምን እንደሚጠብቀኝ አውቃለሁ፤ እርሱ ግን አያውቅም።

በእኔ ላይ ስለሆነው ነገር ከሥነ አዕምሮ ጠበብትም ይሁን ከማንኛውም ሰው ጋር ለመነጋገር ፍላጎት አልነበረኝም። እንደዚያ አይነቱ ልምምድ ለሌሎች ሊያካፍሉት የሚከብድ እጅግ ኃይለኛና የጠለቀ ነገር መሆኑን ተመልክቻለሁ። እኔና ኢቫ ምንም እንኳን እጅግ የተቀራረብን ብንሆንም በወቅቱ ግን ለእርሷ እንኳን ልነግራት አልችልም ነበር።

ወደ መንግስተ ሰማይ መሄድ እጅግ የተቀደሰ ነገር ነው፤ እጅግ የተለየም:: በመንግስተ ሰማይ ስሰነበረኝ የዘጠና ደቂቃዎች ቆይታ ማውራት እነኛን ድንቀኛ ጊዜያት ማንኳሰስ ይመስለኛል:: ወደ መንግስተ ሰማይ ስለነበረኝ ጉዞ እውነትነት በጭራሽ ተጠራጥሬም ይሁን ጥያቄ ኖሮኝ አያውቅም:: ያ በጭራሽ አስጨንቆኝ አያውቅም:: ሁሉም ነገር ግልጽና እውነታዊ ነበር፤ ልክድ ብፈልግ እንኳን ላደርገው አልችልም:: በጭራሽ:: ችግር የሆነው ነገር ግን ያንን ኃያል የሆነ ልምምዴን ከማንም ጋር ልጨዋወተው አለመፈለጌ ነበር::

ያ ሁኔታዬ የሥነ አእምሮ ጠቢባኑን ወደ መኝታ ክፍሌ ከመምጣትና እኔን ለመርዳት ከመሞከር አላገዳቸውም:: ከጥቂት ጊዜያት በኋላ፤ የሥነ አእምሮ ጠቢባን መሆናቸውን ለእኔ አይናገሩም ነበር:: አሁን ሲታሰብ ነገሩ ሁሉ አስቂኝ ነው፤ የሆስፒታሉ የሥነ አእምሮ ሀኪሞች እኔን ሊረዱኝ ወስነው ነበር:: እነርሱን ለማነጋገር ፈቃደኛ ባልሆንኩ ጊዜ፤ በድብቅ ወደ መኝታ ክፍሌ እየገቡ ሁኔታዬን ማጥናት ጀመሩ:: አንዳንድ ጊዜ የሚመጡት ነርሷ እርዳታ በምትሰጠኝ ሰዓት ነበር:: አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ወደ ክፍሌ ገብተው የሐኪሙን ሪፖርት ያጠኑና ምንም ሳይናገሩ ይሄዳሉ፤ እኔ ንግግሩን እንድጀምር ተስፋ አድርገው እንዲህ እንደሚያደርጉ አገምታለሁ::

ብዙውን ጊዜ ወደ ውስጥ ይገቡና እንደዚህ የመሰለ ንግግር ይናገራሉ፤ "እኔ ዶ/ር ጆንስ እባላለሁ" በቃ ይሄው ነው:: ዶክተሩ የደም ምቴን ያጣራል ከዚያም፤ "ዛሬ ሆድህ እንዴት ነው?" ሲል ይጠይቃል:: የሐኪም ሪፖርቱን ከተመለከተ በኋላም ጠቃሚ ጥያቄዎችን ያስከትላል:: አዘወትሮ ንግግር የሚጀምረው "ዛሬ እንዴት ይሰማሃል?" በሚል ቀላል ጥያቄ ነው::



"ያው እንደተለመደው ነው"

"አሁን እየሆነ ስላለው ነገር ሁሉ የሚሰማህ ምንድን ነው?" ምንም ያህል አቀራረባቸውን ቢቀያይሩትም፤ ሁልጊዜም የሚጠይቁት ምን እንደሚሰማኝ ነው::

"አንተ የሥነ አዕምሮ ሃኪም ነህ፤ አይደለህም? " ስል እጠይቃለሁ::

"እ ... ማለት ... በእርግጥም ነኝ"

"ጥሩ፤ ማወቅ የምትፈልገው ነገር ምንድን ነው? በድብርት ውስጥ እንዳለሁ ለማወቅ ነው የምትፈልገው? መልሱን ማወቅ ከፈለግክ በታላቅ ድብርት ውስጥ ነው ያለሁት:: ስለእርሱ ደግሞ መነጋገር አልፈልግም:: "

የቃላት ልውውጡ ይቀጥላል፤ ይሁን እንጂ አብዛኞቹን ቃላት በአዕምሮዬ ወንፊት እያጣራሁ እጥላቸዋለሁ:: ዶ/ር ጆንስንም ይሁን ሌሎቹ የሥነ አዕምሮ ሃኪሞች ሊረዱኝ እንደሚሞክሩ ባውቅም ምንም ተስፋ ያለው ነገር እንዳለ አላምንም:: በድብርት ውስጥ መግባቴን ጠልቼዋለሁ፤ ነገር ግን በዚህ ጉዳይ ላይ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም::

በአልጋዬ ላይ ለረዥም ጊዜ በተኛሁ መጠን፤ ወደፊት ምንም ተስፋ እንደሌለኝ እራሴን ማሳመኔ እየጨመረ ይሄድ ነበር:: መንግስተ ሰማይ ፍጹም የሆነች፣ የተዋበችና ደስታ የሞላባት ነች:: ከዚህ ስቃይ ተላቅቄ ተመልሼ መሄድ እፈልግ ነበር::

"አንድ ሰው መንግስተ ሰማይን ከተመለከተ በኋላ በዚህ ለመቆየት ለምን ይፈልጋል? " ስል እግዚአብሔርን እጠይቀዋለሁ፤ "እባክህ ... እባክህ መልሰህ ውሰደኝ::"

አልሞትኩም፤ ከገባሁበት ድብርት ውስጥም አልወጣሁም::

መነጋገርን ያልፈለኩት ከሥነ አዕምሮ ሃኪሞቹ ጋር ብቻ አልነበረም፤ ስለ ምንም ነገር ከማንም ጋር መነጋገርን አልፈልግም ነበር::

ማንንም ማየት አልፈልግም:: ጠያቂዎች በማይኖሩበት ጊዜ ጥሩ ስሜት ይሰማኛል ወይም እንደዚያ እያልኩ ራሴን አሳምናለሁ::

ድብርት ውስጥ በገባሁበት ጊዜ፤ ብቻዬን ሆኜ እንድሞት፤ ማንም ወደ አዕምሮዬ እንዳይመልሰኝ ብቻዬን መሆን እፈልግ ነበር::

በተጨማሪም እንደ ቤተክርስቲያን መጋቢነቴ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆኜ ማንም ሊመለከተኝ አልፈልግም ነበር፣ ውስጣዊ የሆነ በቂ ኩራት ይሰማኛል:: እንዲህ ስል አካላዊ ስለሆነው ጉዳቴ ብቻ አይደለም የምናገረው፤ ይልቁንም ስለነበርኩበት እጅግ የዘቀጠ ስሜታዊ ውድቀት ጭምር ማለቴ ነው::

ሰዎች ወደ ክፍሌ ገብተው ሊያዩኝ በመጡ ጊዜ ከሚናገሩት ቃላትና ከእስተያየታቸው እንዲህ እያሉ በውስጣቸው እንደሚናገሩ እስባለሁ፤ "በምድር ላይ ካየኋቸው ሰዎች ሁሉ ምስኪን ነህ "

እንደሆንኩም እገምታለሁ::

እናም ድብርቱ እየቀጠለ ሄደ:: እግዚአብሔር ሌላ ተአምር እስኪያለማምደኝ ድረስ ረዥም ጊዜ ወስዶ ነበር::



የሦስት ልጆች አባትና የምትደነቅ ሚስት ባል ነበርኩ:: አደጋው እስከደረሰብኝ ጊዜ ድረስ ታላቅና ብሩህ የሆነ መፃኢ የሕይወት ተስፋ የነበረኝም ሰው ነበርኩ:: በአደጋው ወቅት የሰላሳ ስምንት ዓመት ጎልማሣና እስኪዚያም ጊዜ ድረስ የጤነኛ ሰው ምሳሌና መልካም ተክለ ቁመና የነበረኝ ሰው ነበርኩ:: ከአደጋው በኋላ በጥቂት ቀናት ውስጥ እንደገና ጠንካራና ጤነኛ ሰው ልሆን እንደማልችል አወቅኩት:: አሁን ሙሉ ለሙሉ ተስፋ የለሽ ሆኛለሁ:: በራሴ ላደርገው የምችል ምንም ነገር የለም፤ እጄን ማንሣት እንኳን አልችልም:: እስከ ሕይወት ዘመኔ መጨረሻም እንደዚሁ ተስፋ የለሽ ሆኜ እቀራለሁ የሚል ውስጣዊ ፍርሃት ነበረብኝ::

ተስፋ ቢስ እንደሆንኩ ጠቋሚ ከነበሩት ነገሮች መካከል አንዱ፤ በሆስፒታሉ ውስጥ በነበርኩባቸው የመጀመሪያዎቹ አሥራ ሁለት ቀናት ሰውነቴ አንዳችም አይነት እንቅስቃሴ አለማድረጉ ነበር:: ውስጣዊ የሰውነት ክፍሎቼ እንደሚመረዙ በማወቃቸው፤ ወደ ትንሹ የአንጀቴ ክፍል ፈሳሽ መድሃኒት አስገቡ፤ ነገር ግን ምንም ያህል ጠቃሚ አልነበረም::

"ያን ያህል ጥሩ አይደለም" አልኩ፤ ይወጣ የነበረው ጥቂት ጥቂት ብቻ ነበር፤ ነርሷ ወይም የነርሷ ረዳት በደስታ ፈገግ አለች::

አንድ ቀን በመጠኑ ጨመር አድርጌ ማማጥ ተሳካልኝ:: "አ! በጣም ጥሩ ነው:: ስለ አንተ በጣም ደስተኞች ነን:: እስኪ እንጠብቅ ምናልባት የሚወጣ ተጨማሪ ነገር ይኖራል:: "

በድብርት ውስጥ በነበርኩበት ወቅት፤ በሕይወቴ የመጨረሻውን አሳዛኝ ክስተት ያየሁበት ሁኔታ ውስጥ የገባሁበት ጊዜ ነበር:: ልክ እንደ

ህፃን ልጅ የሆንኩ ይመስል ነበር፤ እያንዳንዱ የአንጀቴ ትንሽ እንቅስቃሴ ሰዎችን ሁሉ ያስደስታቸዋል።

ለነርስ ረዳቷ ምን እንደተናገርኳት በትክክል አላስታውስም፤ ያም ቢሆን ደስተኛ እንዳልነበርኩ እርግጠኛ ነኝ።

ክፍሉን ለቃ ወጣች። ጠያቂ በአጠገቤ ካልነበረባቸው በጣም ጥቂት ጊዜያቶች አንዱ ወቅት ነበር። ሙሉ ለሙሉ ብቻዬን በመሆኔ ደስተኛ ነበርኩ፤ ሰላምና ውስጣዊ ጸጥታ ተሰማኝ።

ነርሷ በሄደች በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ በሆዴ ውስጥ ፈሳሹ መድሃኒት መሥራት ጀመረ።

ፈነዳ! በሕይወቴ አንጀቴ እንደዚያ ሲንቀሳቀስ ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር። የወጣው ቆሻሻ ሽታ አንገሸገሸኝ።

ድንገተኛ በሆነው ሁኔታዬ ውስጥ ሆኜ እንደ ምንም ተንጠራረሁና የመጥሪያ ደወሉን በጣቴ ነካሁ። ከሰከንዶች በኋላ ወጣቷ የነርስ ረዳት ሮጣ ወደ ክፍሌ መጣች።

በጣም አዝናለሁ፤ እንዲህ አደርጋለሁ ብዬ አላሰብኩም አልኩ። "በማጽዳት እረዳሻለሁ።" እርሷን መርዳት አለመቻሌን ከመገንዘቤ በፊት ካሉ ጥቂት ሰኮንዶች በፊት ነበር ቃላቶቹ አፈትልከው የወጡት ምስኪንነቴ፣ አቅም አልባነቴና እድለቢስነቴ ተሰማኝ።

እናም ማልቀስ ጀመርኩ።

"በጭራሽ፣ በጭራሽ በምንም ነገር አትጨነቅ፤ ስለአደረከው እኛ እኮ ደስተኞች ነን። ይሄ እኮ ጥሩ ነው፤ ምክንያቱም ይህ ማለት ከእንግዲህ ሆድህ እንደገና በአግባቡ ይሠራል ማለት ነው።"



በፍጹም ትህትና ውስጥ ሆኜ እንደተጋደምኩ ወጣቷ ምስኪን ሴት ሁሉን ነገር ስትቀያይር እመለከት ነበር። ክፍሉን ለማጽዳት የወሰደባት ጊዜ ምን አልባት ግማሽ ሰዓት ያህል ይሆናል፤ ሽታው ከክፍሉ ለቆ ለመሄድም አንድ ሰዓት ያህል ጠይቋል።

ሃፍረቴ ጥሎኝ ሲሄድ አልቻለም፤ አዕምሮዬ ግን የተለየ ነገር ሊነግረኝ እየፈለገ ነበር። ላለፉት አስራ ሁለት ቀናት የቀመስኩት ነገር ጥቂት ነው፤ እናም ይህ የመጀመሪያው እፎይታ ነበር። ይሁን እንጂ እኔ አስበው የነበረው ነገር ይህ ሁኔታ በሕይወቴ እጅግ አሳፋሪው ክስተት እንደሆነ ነበር።

ለእኔ አስከፊ፤ በጣም አሳፋሪና ምስኪንነቴን የገለጠ ሁኔታ እንደነበረ ነው የተሰማኝ። የሽንት መቀበያ የፕላስቲክ ቱቦ ተደርጎልኛል፣ ራሴን ማጽዳት አልችልም፤ መላጨት አልችልም። የራሴን ጸጉር እንኳን መታጠብ አልችልም። ጭንቅላቴን ወደ ውስጥ የሚያስገባ የተለየ መሣሪያ አምጥተው ውሃውን በጸጉሬ ላይ ይለቁታል፤ ከዚያም በሆነ ቱቦ ውስጥ አሳልፈው ውሃውን ወደ ቆሻሻ ማጠራቀሚያው ቆርቆሮ ያፈሱታል። ከዚህ በተጨማሪ ታላቅ መልካምነቱን ያሳየኝ ሰው ካሮል ቢንፊልድ ሲሆን ይህ ሰው በአልጋ ላይ በነበርኩበት አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወደ እኔ እየመጣ ጸጉሬን ያስተካክለኝ ነበር። ስድሳ ማይሎች ያህል እያቆራረጠ መጥቶ ያገለግለኝ የነበረው ይህ ሰው ገንዘብም ሆነ ሌላ ነገር ለመቀበል ፈቃደኛ አልነበረም።

ጓደኞቼ፣ ቤተሰቦቼና የህክምና ባለሙያዎች ለሰውነቴ የሚያስፈልገውን ሁሉ ለማሟላት መንገዶችን ሁሉ ይፈልጉ ነበር፤ እኔ ግን ሙሉ ለሙሉ ፈጽሞ ዋጋ እንደሌለኝ አስባለሁ። ያልተሰበረው የቀኝ እጄ በርካታ መድሃኒቶችን ወደ ደም ስሮቼ የሚያስተላልፉ መርፌዎች

ተሰክተውበት ስለነበር እነርሱን ለመደገፍ አነስተኛ ጣውላ ከእጀ ጋር በማሰራቸው ላጥፌው አልችልም ነበር፡፡

መርፌዎቹ በሰውነቴ ሁሉ ላይ ተተክለዋል፡፡ ከደረቴ ጀምሮ ቁልቁል እስከ እግሬ መዳፍ ጫፍ ድረስ ይዘልቃሉ፡፡ በደረቴ ላይ አቋርጦ በቀጥታ ወደ ልቤ የሚያልፍ አንድ ዋንኛ የመድሃኒት ማስተላለፊያ ቱቦ ተከትለው መስመራቸውን ይዘው ተደርድረዋል፡፡ አብዛኛዎቹ የደም ስሮቼ ከጥቅም ውጭ ሆነዋል፡፡ ፈጽሞ መላወስ የማልችል በመሆኔ፤ የቁስል ፋሻዎችን ለመቀየር፤ ለማንቀሳቀስ ወይም ከአልጋው ላይ ለማንሳት የሆነ ስንስለት መጠቀም ያስፈልጋቸው ነበር፡፡

ዶክተሮቹን ስጋት ውስጥ በከተተ ሁኔታ ክብደቴ በሚያስገርም ፍጥነት ያሽቆለቁል ነበር፡፡ ምንም ነገር መመገብ የማልችል በመሆኑ ምግብ የሚሰጠኝ በፈሳሽ መልክ በመርፌ ነበር፡፡ በሆስፒታሉ በቆየሁበት የአራት ወራት ጊዜ ውስጥ ሃያ ስባት ኪሎ ያህል ቀንሻለሁ፡፡ ከአደጋው በፊት ዘጠና አምስት ኪሎ እመዝን ነበር አሁን ወደ ስልሣ ስምንት ኪሎ ወርጃለሁ፡፡ ክብደቴን የሚለኩት የህፃናትን ክብደት ለመለካት በሚጠቀሙበት ዘዴ ማለትም በተንጠልጣይ ሚዛን ከአልጋዬ ላይ ከፍ አድርገው በማንሳት ብቻ ነበር፡፡ የምወዳቸውን የምግብ አይነቶች በማዘጋጀት እንድመገብ ያነሳሱኛል፤ ነገር ግን ምንም ነገር ጣእም አይሰጠኝም፡፡ ገና የምግብ ሽታ ያንገሸግሸኛል፡፡ የመብላት አንዳች ፍላጎት አልነበረኝም፡፡ ለመብላት መሞከሬ አልቀረም፤ በርግጥ ብዙ ተጣጥሬአለሁ፤ ይሁን እንጂ ከጥቂት ጉርሻዎች በላይ መቀጠል አልችልም፡፡

የድብርቱ ሁኔታ የምግብ ፍላጎቴን እንዳጠፋው እገምታለሁ፤ ይሁን እንጂ ችግሩ እርሱ ለመሆኑ እርግጠኛ አይደለሁም፡፡ ለመመገብ



በሞከርኩ ጊዜ ምንም ነገር ለማኘክ እንደማልችል ነው የማውቀው፡፡ ያላመጥኩትን ለመዋጥ አልፈልግም ነበር፡፡

ፒሲ ተብሎ የሚጠራ የህመም ስሜትን የሚያስታግስ የሞርፊን መድሃኒት በመርፌ ወደ ሰውነቴ እንዲገባ ተደርጓል፡፡ ህመሙ እየጨመረ በሄደ ጊዜ ሁሉ መድሃኒት እንዲሰጠኝ የመጥሪያውን ደወል እጫናለሁ፡፡ ያለማቋረጥ የህመም ማስታገሻ መድሃኒቶችን መውሰድ ያስፈልገኝ ነበር፡፡ በመጀመሪያ ላይ በርካታ የህመም ማስታገሻ መድሃኒቶችን መውሰዴን ተቃውሜ ነበር፤ ዶክተሩ ግን ያንን በማድረጌ ገሰጸኝ፡፡ ሰውነቴ በህመሙ ስቃይ ምክንያት ችግር ውስጥ የሚገባ በመሆኑ፤ ፈውሴ እንዳይከናወን የሚያግድ መሆኑን ነገረኝ፡፡

የሌሊት እንቅልፍ እንዲኖረኝ በማሰብ ምሽት ላይ ተጨማሪ መድሃኒቶች ይሰጡኛል፡፡ ይሁን እንጂ መተኛት አልችልም ነበር፤ ምክንያቱም ተጨማሪ መድሃኒቶቹ አይሠሩም ነበር፡፡ የእንቅልፍ እንክብሎችን፣ የህመም ማስታገሻ መርፌዎችን ወይም ተጨማሪ መርፌዎችን ቢሰጡኝም በፍጹም እንዳንቀላፋ አያደርጉኝም፡፡

ዘና ለማለት ወይም የህመም ስቃዩ እንደለቀቀኝ ለማሰብና ከስቃዩ ወደ እፎይታ ለመሸጋገር ምንም መንገድ አልነበረኝም፡፡

እንዲህ ብዬ ብገልጸው ሁኔታውን ያስረዳ ይሆን? "እንዲህ ባለ ሁኔታ ውስጥ እንዳለህ አስብ፤ በአልጋ ላይ ተጋድመሃል፣ በክንዶችህ ውስጥ ብረቶች እንዲያልፉ ተደርገዋል፣ የኤሌክትሪክ ሽቦዎች በእግሮችህ ውስጥ አልፈዋል፤ በዚህ ሁሉ ውስጥ የተኛኸው በጀርባህ ነው፡፡ መገላበጥ እንኳን አትችልም፡፡ ትንሽ ለመንቀሳቀስ እንኳን ከአልጋህ በላይ የተጋደመውን ብረት ካልያዝክ በስተቀር መነቃነቅ አይሞከርም፡፡ እንደ

ምንም ብለህ ከተንቀሳቀስክ እንኳን መላውን ሰውነትህን የሚያዳርስ የህመም ስቃይ ይከተላል። ሙሉ በሙሉ ከእንቅስቃሴ ውጭ ነህ።"

በአንድ አቅጣጫ ማለትም በጀርባዬ ብቻ ለረዥም ጊዜ በመተኛቴ ጀርባዬ በመላጡ፣ በመጨረሻው ሆስፒታሉ ያለማቋረጥ የሚንቀሳቀስ በውሃ የተሞላና የፕላስተክ ሽፋን ያለው አልጋ እንዲዘጋጅልኝ አደረገ። ያ የጀርባዬ መላላጥ እንዲቀር አደረገው።

ያንን ክፍል ለቅቄ የምወጣው በተሽከርካሪ አልጋ ላይ አስተኝተው ወደ ራጂ ክፍል በሚወስዱኝ ጊዜ ብቻ ነው። ያ ለእኔ ሁልጊዜም እንደ ትልቅ ጀብድ የሚቆጠር ነበር። በላዬ ላይ ከተሸከምኩት የብረታ ብረት መአት የተነሣ እንዴት አድርገው ራጂ እንደሚያነሱኝ ይቸገሩ ነበር። ሦስትና አራት የሚሆኑ ሰዎች ጨረር መከላከያ ልብሳቸውን ለብሰው የራጂ ማንሻ መሣሪያውን ስስ፣ ጠፍጣፋ መስተዋት በብረት በተሞሉት እጆቼና እግሮቼ ዙሪያ እያሽከረከሩ ማንሳት ያስፈልጋቸው ነበር። ምክንያቱም እንደኔ ባለ ሁኔታ ውስጥ ላሉ ሰዎች ታቅዶ የተሰራ የራጂ መሣሪያ አልነበረም።

ይህም ማለት አንዳንድ ቀን የራጂ ቴክኒሽያኑ ሃኪም በተፈለገው መንገድ አጥንቶቼ መስተካከላቸውን መመልከት በሚችልበት ሁኔታ የራጂ ምስሎችን ለማዘጋጀት ሁለትና ሦስት ሰዓታትን ይወስድ ነበር ማለት ነው። እንደኔ ላለ ሁኔታ በመደበኛውና በተለመደው ሁኔታ ውስጥ መሥራት የሚችሉበት እድል አልነበራቸውም። ወደ ራጂ ክፍል እያሽከረከረ ሊወስደኝ የሚመጣው ሰው ሁልጊዜም፣ "በኮሪደሩ ላይ ረዥሙን ጉዟችንን እስኪ እንጀምር" ይላል።

ሁሉም የሚሉት ይሄንኑ ነው፣ ምክንያቱም ምን ማለታቸው እንደሆነ ስለሚገባኝ ነው። ተሽከርካሪው አልጋ በጥንቃቄና በዝግታ



እየተገፋ ረዥም መንገድ የሚሄድ ስለነበር፣ ሁኔታዬን ለመርሣት በጣሪያው ላይ ያሉትን የካሬ ቅርጽ ያላቸውን ጌጠኛ ነጠብጣቦች እያገጣጠምኩ እጫወታለሁ። ያንን የጀመርኩት በመጀመሪያው ቀን ከቀዶ ጥገና ክፍል ተመልሼ ስወጣ ነበር። ምናልባትም የሌለውን ነገር እያየሁ ስቃዥ የነበር ይሆናል፣ ይሁን እንጂ ያ የቀዶ ጥገና ክፍል ገና አዲስና እኔም የመጀመሪያው ሰው እንደነበርኩ አስታውሣለሁ። ወደ ውስጥ ሲያስገቡኝ በከፍተኛ ድምጽ እቃትታለሁ እናም ላቆመው አልቻልኩም። ከዚያ ቀና ብዬ በጣሪያው ላይ ያሉትን ጌጠኛ ነጠብጣቦች ተመለከትኩ፣ አተኩሬ ሳያቸው በውል ለይቼ ላውቀው ያልቻልኩትን ቅርጽ እየሠሩ በአንድ አቅጣጫ የሚጓዙ መሰለኝ። በአዕምሮዬ እነኝህን ነጠብጣቦች በመጠቀም ስዕሎችና ቅርጾችን መስራት ጀመርኩ። ያንን እያደረኩ እያለም፣ በቃ ፈጽሞ ወደ እብደት እያመራሁ ነው እያልኩ አስባለሁ። ይሁን እንጂ እንደዚያ ማድረጌን ቀጠልኩ። በመጨረሻውም፣ እነኝህን ነጠብጣቦች የማገጣጠሙ ነገር ያለሁበትን ሁኔታ እንድረሳና ለጊዜውም ቢሆን የሚሰማኝን የህመም ስቃይ ለመርሣት የምጠቀምበት መንገድ ሆነ።

የየዕለቱ ትልቁ ስቃዬ የሚጀምረው ነርሷ ኤሌክትሪክ ሽቦዎች ወደ ቆዳዬ የሚገቡበትን ቀዳዳዎች ማጽዳት ስትጀምር ነው። በቅዱስ ሉቃስ ሆስፒታል ውስጥ በሃያ ሰባተኛው ፎቅ ላይ በሚገኘው የድንገተኛ አደጋ ክፍል የሚያክሙን ነርሶች ሁሉ እነኛን ቀዳዳዎች እንዴት እንደሚያፀዱ ተለማምደዋል። ቆዳው ከገመዶቹ ጋር እንዳይጣበቅ ስለሚፈልጉ፣ ቆዳው ከኤሌክትሪክ ገመዶቹ ጋር የተያያዘባቸውን ስፍራዎች ሁሉ ይፈለቅቋቸዋል-ይህ አንዳንድ ጊዜ የሚፈጠር ነው። ከዚያ በኋላ ነርሶቹ ቆዳዬ እንዳይመረዝ ሃይድሮጅን ፔርኦክሳይድ የተባለ

መድሃኒት በቀዳዳዎቹ ውስጥ ይጨምራሉ:: ይህንን ከመቋቋም የበለጠ ስቃይ እንደሌለ አስባለሁ፤ ይህ የሚሆነው ደግሞ በየቀኑ ነው::

ያም ብቻ አልነበረም:: በየስድስት ሰዓቱ በቀን አራት ጊዜ፤ አለን ሪንች የተባለ መፍቻ በመጠቀም በመሣሪያው ላይ ያሉትን ብሎኖች ይጠመዝዛሉ:: ይህንን የሚያደርጉት የአጥንቶቹ ጫፎች እንዲስጠጡ በማድረግ በጎደለው አጥንት ሥፍራ ላይ በትክክል እንዲገጥሙ በማሰብ ነው::

ብሎኖቹ በሚጠመዘዙ ጊዜ የሚሰማኝን ስቃይ ለመግለጽ አዳጋች ነው:: ምንም እንኳን እያንዳንዱ ጥምዘዛ በጥንቃቄና በዝግታ የሚደረግ ቢሆንም ህመሙ ግን አያድርስ ነው:: ቀንም ይሁን ሌሊት የሚያመጣው ለውጥ የለም፤ በየስድስት ሰዓቱ አንድ ሰው ወደ ክፍሌ ይገባና ብሎኖቹን መጠምዘዝ ይጀምራል::

እንደ ቤተክርስቲያን መጋቢነቴ፤ በርካታ የሆስፒታል ክፍሎችን ጎብኝቻለሁ፤ ይህም የቀዶ ህክምና መስጫ ክፍሎችን ያጠቃልላል:: በብዙዎች ፊት ላይ ጭንቀትን ተመልክቻለሁ፤ ያለማቋረጥም ያለኝን ሃዘኔታ በፊት ገጽታዬ ገልጬላቸዋለሁ:: ይህም ቢሆን በየቀኑ እንዲህ ባለው ሁኔታ ውስጥ ማለፍ ያለውን ስቃይ ገምቼውም አላውቅም ነበር::

ምናልባትም የእኔን ችግር ለየት ባለ ሁኔታ አስከፊ ያደረገው፤ አለመተኛቴ ነበር:: ለአሥራ አንድ ወራት ከተኩል እንቅልፍ የሚባል ነገር አላውቅም፤ ቀናቱንና ሌሊቱን እንዲሁ አሳልፋቸዋለሁ:: በርከት ያለ መጠን ያለው ሞርፊን የተባለውን መድሃኒት ብወስድም ህመም ተሰይቶኝ አያውቅም:: የመተኛ ጊዜዬ ነው ብለው በገመቱበት ሰዓት ነርሷ ሞርፊን ወይም ሌላ መድሃኒት ሦስትና አራት ጊዜ እንድትወጋኝ ተወሰነ:: በአልጋዬ ላይ እንደተጋደምኩ ምንም ያህል ራሴን ዘና እንዲል



ብነግረውም፤ ፈጽሞ መሆን አይችልም:: ህመሙን ለመጋፈጥ እሞክራለሁ፤ ከዚያ በኋላ በግልጽ እንደሚሆነው አዕምሮዬን እስተዋለሁ:: ከዚያ በኋላ ወደአዕምሮዬ በምመለስበት ቅጽበት የማውቀው ነገር ቢኖር መጠነ ሰፊ የሆነ የህመም ስቃይ ውስጥ መሆኔን ነው::

በመጨረሻው፤ የቤተሰቤ አባላትና የሆስፒታሉ ሠራተኞች ብቻዬን ተውኝ፤ ምክንያቱም ከዚያ በኋላ መሥራት የሚችል አካል እንደማይኖረኝ በማወቃቸው ነበር:: የጊዜን ነገር ማሰብ አቆሜአለሁ፤ ዘና ማለትም አልችልም፤ ምክንያቱም በከፍተኛ ውጥረት ውስጥ ነበርኩ:: ለመንቀሳቀስ ትንሽ ጥረት ባደርግ፤ በውስጤ የተቀበረው የኤሌክትሪክ ገመድ ከመገናኛው ላይ ቀዳዬን ይስነጥቀዋል:: እኔ እንቀሳቀሳለሁ፤ ገመዶቹ ግን አይችሉም:: በጥቂቱ እንኳን ነቅነቅ ብል በመላው አካል ላይ የህመም ስቃይ የሚያስከትል ሁኔታ ይፈጠራል::

ከሆነ ጊዜ በኋላ፤ በዚያ ሁኔታ ውስጥ መኖርን ተማርኩ፤ ልላመደው ግን በፍጹም አልቻልኩም::

ምንም እንኳን በአካል አይን በአይን ባንተያይም፤ ኤልዛሮቭ ፍሬም የተባለው መሣሪያ መጀመሪያ ሲፈለሰፍ ስታቀደለት ዓላማ መዋሉን ያወቅኩት ክርስቲ በተባለች ወጣት ላይ ነው:: መሣሪያው ከመጀመሪያውም የተሠራው ገና ከእናታቸው ማህጸን ሲወጡ የአጥንት ችግር ላለባቸው ሰዎች ነው:: ይሁን እንጂ ኤልዛሮቭ ፍሬም፣ አጥንት እድገቱን ከማቆሙ በፊት በእግር ላይ አይገጠምም:: በተለይም የአጥንት እድገት ፈጣን በሆነባቸው የልጅነት ዓመታት መሣሪያውን መጠቀም

አይመከርም፤ በመሆኑም ዶክተሮች ትክክለኛውን ጊዜ በጥንቃቄ ይመርጣሉ::

ወጣቷ ልጃገረድ ክርስቲ እኔ ከተኛሁበት ክፍል አጠገብ ነበር የተኛችው:: የተወለደችው አንደኛው እግሯ ከሌላኛው አጥሮ ነው:: አጥንቶቿ እድገታቸውን ካቆሙ በኋላ፤ ሁለቱም እግሮቿ እኩል መጠን እንዲኖራቸው በኤልዛሮቭ ፍሬም ህክምና መጠቀም መረጠች::

ክርስቲ በዚህ ቀዶ ህክምና ስመታከም ራሷ የመረጠች በመሆኑ ስለሚያስከትለው ስቃይና ህክምናውን ለመጨረስ ስለሚወስደው የጊዜ መጠን የተወሰነ እውቀት ነበራት:: ሰወራቶች ያህል አስፈላጊው ምክር ሲሰጣት የቆየ ሲሆን፤ ቤተሰቦቿም ቁስሉን እንዴት መንከባከብ እንደሚገባቸው እንዲያውቁ ተደርገዋል:: ህክምናው ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ እንዲያውቁና በእነዚህ ጊዜያቶች ውስጥ እርሷን ለመንከባከብ ቁርጠኛ ፈቃደኝነት እንዲያደርጉ ተነግሯቸዋል::

በእኔና በክርስቲ መካከል ያለው ልዩነት፤ ቢያንስ ቢያንስ እርሷ ስለመሣሪያው ማንም ሰው ሊያውቅ የሚገባውን ያህል እንድታውቅና ስለምትገባበት ሁኔታ ግንዛቤ እንዲኖራት ተደርጓል:: እኔ ግን ከቀዶ ጥገና ህክምናው ስነቃ መሣሪያው በሰውነቴ ላይ ተገጥሞ ነው ያገኘሁት:: በድብርት ውስጥ በገባሁበት ጊዜ ይሄ ጉዳይ ችግሩን ይበልጥ አባባሰብኝ:: ምንም እንኳን የኤልዛሮቭ ፍሬሙን በእግሬ ላይ ያደረጉልኝ እግሬን ለማትረፍ ቢሆንም፤ የስቃዬ ሁሉ ትልቁ ምክንያት እርሱ ብቻ እንደነበረ አስባለሁ::

ቀላል ቢሆንም እንኳን ሌላ ችግር ደግሞ ተከሰተ:: ያሉን የተሰያዩ ዶክተሮች ቢሆኑም፤ ብሎኖቹን ስመጠምዘዝ ወደ እኔም ይሁን ወደ ክርስቲ የሚመጡት የተወሰኑ ሰዎች ናቸው:: አንዳንድ ጊዜ



መፍቻዎቹ ያለ ስፍራቸው ይቀመጡና ይጠፋሉ፤ በመሆኑም ተረኛው ሰው በእኔ ክፍል ውስጥ ባጣቸው ጊዜ የእርሷን መፍቻዎች ለመዋስ ወደ ክፍሏ ይሮጣል:: ወይም መጥተው የእኔን ይዋሳሉ:: እንደአጋጣሚ ሆኖ የአንዳችን መፍቻ የሌላችንን ብሎን ሊጠመዝዝ የሚችል ስለነበር፤ አንዳችን የአንዳችንን መፍቻ መዋዋስ እንችል ነበር::

በዚህ ምክንያት ነበር ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ ክርስቲ ያወቁት- በመፍቻ ውስጥ ምክንያት:: ፊት ለፊት ተያይተን አናውቅም፤ አንዳችን የሌላውን ዶክተር ማየት ግን እንችል ነበር:: ይህና ሌሎች ተመሣሣይነት ያላቸው ችግሮቻችን በመካከላችን ግንኙነት እንዲፈጠር አደረጉ::

ክርስቲና እኔ የምንጋራው ሌላ ነገርም ነበረን - የህመም ስቃይ:: ብዙ ጊዜ ስትጮህ እሰማታለሁ:: ታለቅስ ነበር ማለቴ ሳይሆን ትጮህ ነበር ማለቴ ነው:: አንዳንድ ጊዜ ዝቅ ባለ ድምጽ ታቃስታለች:: ምናልባትም እርሷም የእኔን የስቃይ ድምጽ ከእኔ ክፍል ውስጥ ትሰማ ይሆናል:: እኔ እንደርሷ አልጮህም፤ ምክንያቱም በተፈጥሮዬ እንደዚያ ማድረግ አልችልም::

ከነርሶቹ አንዲቱ ልክ እንደርሷ ጨኸቴን እንድለቀው መክራኛለች:: ትክክል ልትሆን ብትችልም እንኳን ቢያንስ ቢያንስ በነቃ አዕምሮዬ ይህንን አድርጌው አላውቅም::

አዕምሮዬን መቆጣጠር እችል በነበረበት ጊዜ ሁሉ አልጮህም:: በስቃያቸው ምክንያት ሰዎች ሲጮሁ ለምቻለሁ፤ ጩኸታቸው ደግሞ እጅጉን ይረብሸኛል:: በተጨማሪም ልቤን መጠበቅና ስሜቴን መቆጣጠርን ተምሬአለሁ:: በዚያ ጊዜ እነኛ የጣር ድምጾች፣ ማቃሰቶችና ጩኸቶች መልካም እንዳልነበሩ አምን ነበር:: እጮህ የነበረባቸው ብቸኛ

ጊዜያት እንድም አዕምሮን በሳትኩ ጊዜ አለዚያም ከባድ መድኃኒቶች በሚሰጡኝ ጊዜ ነው:: እጮህ እንደነበረ ያውቅኩትም ሰዎች ከነገሩኝ በኋላ ነበር::

ክርስቲና እኔ ምንም እንኳን ለአሥራ ሁለት ሳምንታት አጠገብ ለአጠገብ ያሉ ክፍሎች ውስጥ ብንተኛም ተገናኝተን አናውቅም:: ደብዳቤዎችን በመላላክ ግንኙነት ጀመርን፤ ነርሶቹም ልክ እንደ ፖስተኞች ያገለግሉን ነበር::

ክርስቲን ላጽናናት ሞከርኩ:: ታሪኳን ትነግረኛለች፤ ስለደረሰብኝ አደጋም በጣም እንዳዘነች ትጽፍልኛለች:: እርሷም እንደ እኔው አማኝ ነበረች:: ግንኙነታችን መስመሩን የጠበቀም ነበር::

ለራሴ ሃዘን በሚሰማኝ በጣም አስከፊ ጊዜያት፤ ክርስቲ እንደገና ጤነኛ ሴት ትሆናለች፤ እኔ ግን ዳግመኛ ጤነኛ አልሆንም እያልኩ አስባለሁ:: ማንኛውም ወጣት ሊያደርግ የሚችለውን ማንኛውንም ጨዋታ መጫወትና መሮጥ ትችላለች:: በዚያ ጊዜ እንኳን እኔ እንደገና መሮጥ እንደማልችል አውቃለሁ::

ስለራሴ የማዝንባቸው በርካታ ጊዜያት ነበሩ:: እርሷ ስቃይ እንደሚያስከትል አውቃና ምርጫዋ ሆኖ ነው፤ እኔ ግን ምንም አይነት ማስጠንቃቂያ አልተሰጠኝም ምርጫም አልነበረኝ እያልኩ ራሴን አስታውሰዋለሁ:: እርሷ ወደ ምን አይነት ሁኔታ ውስጥ እንደምትገባ አውቃዋለች፤ እኔ ግን ምንም ግንዛቤ አልነበረኝም:: እርሷ በቀሪ የሕይወት ዘመኗ መልካም ውጤት የሚያስከትል ነገር እያደረገች ነው፤ እኔ ግን ሕይወቴን ለማትረፍ ብቻ የማደርገው ነገር ነው:: አዎን እጅግ ብዙ ጊዜ ለራሴ አዝን ነበር::



ይሁን እንጂ ሁልጊዜም፤ ወደ አንድ ነገር ተመልሼ እመጣለሁ፤ እግዚአብሔር በሕይወት እንድኖር መርጧል:: ከፍተኛ በሆነ የድብርትና ሃዘን ውስጥ በገባሁበት ጊዜ እንኳን ይህንን አልረሳውም::

እኔና ክርስቲ እንካፈል የነበረው ተመሳሳይ ስቃይ ነበር:: ይህንን ብቻም አይደለም፤ እጅግ አስከፊ በሆነው የስቃያችን ጊዜ እንኳን ህያው የሆነ አምላካችን ከእኛ ጋር እንደሆነ ያለንን እምነት እንጋራ ነበር:: እርሷ እኔ ካለሁበት ክፍሌ አጠገብ በመሆኗ፤ ስለእኔ ሁኔታ የማውቀው እኔ ብቻ አይደለሁም፤ ምን እንደሚሰማኝ የሚያውቅ ቢያንስ ሌላ አንድ ሰው አለ፤ እያልኩ አስባለሁ::

በዚያ ጊዜ ነው ከተገለሉት ወገኖች መካከል እንደሆንኩ ማሰብ የጀመርኩት:: ከዚያ ሆስፒታል ከወጣሁ በኋላ እንኳን ከሌሎች ጋር መቀላቀልን የማይፈልጉ ጥቂት ሆነው ህብረት ከሚያደርጉ ቡድኖች ጋር ተገናኝቻለሁ:: ስቃይ ማለት ምን እንደሆነ ስለማውቅ ህመማቸው ይሰማኛል-ልክ ክርስቲ የእኔን፣ እኔም የክርስቲን የህመም ስቃይ እናውቅ እንደነበረው ማለት ነ ው::

ስቃዩን መቋቋም ብቻ አይደለም፤ ዶክተሮች ከዚያ በኋላ ልታደርጋቸው አትችልም ያሏቸውን አንዳንድ ነገሮች ማድረግ ጀመርኩ:: እንደገና መራመድን ተማርኩ:: በራሴ እግሮች መቆም ቻልኩ፤ አንዱን እግሬን ከሌላኛው በማስቀደም መንቀሳቀስ ጀመርኩ::

በተሰበረው የቀኝ እግር ጉልበቴና ከግራ እግሬም ላይ ከጠፋው አጥንት የተነሣ (ምንም እንኳን የተተካልኝ አጥንት በመስጠጥ ክፍት የሆነውን ስፍራ ቢደፍነውም እንኳን) እንደገና መራመድ እንደማልችል

አስጠንቅቀውኝ ነበር። ለመራመድ ብፈልግ ሰውነትን ደግፎ የሚይዝ መሣሪያ መጠቀም እንደሚገባኝ ነግረውኛል። በዚህ ሙከራዬ ከአንድ ጊዜ በላይ የግራ እግሬን ለማጣት ተቃርቤ ነበር፤ ይሁን እንጂ በደረሱብኝ በሁሉም ችግሮች ውስጥ በእግዚአብሔር እርዳታ ለማለፍ ችያለሁ።

የተጎዱትን የሰውነቴን አካላት ለማፍታታት የተደረገው ህክምና በእጄ ላይ የተደረገው ዋናው ቀዶ ጥገና ከተደረገ ከአራት ሳምንታት በኋላ ሲሆን፤ በእግሬ ላይ የተደረገው ደግሞ ከዚያ በኋላ ሁለት ሳምንት ያህል ቆይቶ ነበር።

በዚያው ጊዜ ውስጥ፣ በተለየ አልጋ ላይ እንድተኛ ተደረገ! በዚህ አልጋ ላይ ሰውነቴ ጠበቅ ተደርጎ የሚታሰር ሲሆን፤ ከትራስጌው ከፍ እየተደረገ ሲሄድ እግሬ መሬት ይነካል፤ በመሆኑም በዚህ ሁኔታ መቆም እችል ነበር። ሁለት የህክምና ሰዎች በወገቤ ዙሪያ ሁለት ቀበቶዎች አስታጥቀው በሁለት አቅጣጫዎች ይራመዳሉ። ሁለቱም እግሮቼ ያለጥቅም በመቆየታቸው ጡንቻዎቼ በጣም ተዳክመው ነበር፤ በመሆኑም ሃኪሞቹ የመጀመሪያዎቹን እርምጃዎች እንድራመድ ይረዱኛል። እንደገና መቆም ለመለማመድ ቀናት ወስደውብኛል፤ ስለዚህም የራሴን የእግር ጡንቻዎች ለመጠቀም ችያለሁ። የሰውነት ሚዛኔን ለመጠበቅ አስቸግሮኝም ነበር፤ ምክንያቱም የብረቶቹ መጠን በጎን አቅጣጫ የሰፋ በመሆኑ ነው። እንድቆም በሚደረግበት ጊዜ ሁሉ በማይታመን ሁኔታ ያስመልሰኝ ነበር። በትክክለኛው እቋም ላይ ሆኜ የመጀመሪያዎቹን እርምጃዎች ለመራመድ ቀናት አስቆጥሬአለሁ።

ከሆስፒታሉ እስከወጣሁበት ጊዜ ድረስ በትክክል መራመድ አልተለማመድኩም ነበር። በየዕለቱ የሰውነት አካል ህክምና ባለሙያ



እየመጣ ይረዳኛል። ከጥቂት እርምጃዎች በላይ በራሴ መራመድን ለመለማመድ ስድስት ወራት ወስዶብኛል።

ዶክተሬ አደጋው ከደረሰብኝ ከአሥራ አንድ ወር ተኩል በኋላ ኤልዛሮቭ የተባለውን መሳሪያ ከሰውነቴ ላይ አወጣልኝ። ከዚያ በኋላ በመራመጃ መርጃ መሣሪያ በመጨረሻውም ምርኩዝ መጠቀም አስፈልጎኝ ነበር። ከአደጋው በኋላ እስከ አንድ ዓመት ከመንፈቅ ድረስ ያለ እግር መደገፊያ ብረትና ያለከዘራ መራመድ አልችልም ነበር።

አደጋው የደረሰብኝ በጥር ወር 1989 ነበር። በክንዴ ላይ የነበሩትን ውጫዊ ብረቶች ያነሱልኝ በግንቦት ወር ላይ ነው፤ ይሁን እንጂ በክንዴ የመጀመሪያ አጥንቶች ላይ በውስጥ በኩል ብረቶች አድርገውልኝ ነበር። እነኝህ ብረቶች ለብዙ ወራት በዚያው እንዲቆዩ ተደርገዋል።

በህዳር ወር መጨረሻ አካባቢ፤ የማፅኛ ብረቶቹን ከእግሮቼ ላይ አወጧቸው፤ ይሁን እንጂ ያ የመጨረሻው አልነበረም። ከዚያ በኋላ ከጂሶ በተሰራ የአጥንት ማፅኛ ውስጥ ለረዥም ጊዜ ቆይቻለሁ፤ በዚያ ጊዜ ውስጥም ዝርግ ብረቶች በእግሬ ውስጥ እንዲገቡ ተደርጎ ነበር። እነዚህ ብረቶችም ለዘጠኝ ዓመታት በእግሬ ውስጥ ቆይተዋል። በዚያው እንዲተውአቸው ፈቃዴ ነበር፤ ይሁን እንጂ እንደሚያወጧቸው ነግረውኛል። ዶክተሩ፤ እድሜዬ እየገፋ ሲሄድ እነዚህ ለአጥንቱ ጥንካሬ ሲባል የገቡ ብረቶች አጥንቱን ሊሰብሩት እንደሚችሉ ገልጾልኛል። አጥንቶቻችን ጠንካሮች የሚሆኑትና በዚህ ጥንካሬያቸውም የሚቆዩት ስንንቀሳቀስባቸውና ስንጠቀምባቸው ብቻ መሆኑን ተረድቻለሁ።

የአጥንት ማፅኛ ብረቶች በውስጤ በተቀበሩባቸው በእነዚያ ዓመታት ውስጥ በአየር ትራንስፖርት መጠቀም ከነበረብኝ፣ ብረት ነክ

ነገሮችን ከሚጠቁመው መሣሪያ መራቅ ነበረብኝ:: ሌሎች መንገደኞች ብረት ነክ ነገሮችን እንዳልያዙ ለማስፈተሽ በሚያልፉበት መሣሪያው ባለበት መግቢያ አላልፍም፤ ይልቁንም ወደ ፍተሻ ሠራተኛው ጠጋ ብዬ፤ በቤትህ ውስጥ ካሉት የመመገቢያ ማንኪያዎች፣ ቢላዋዎችና ሹካዎች ይልቅ የበለጠ ክብደት ያለው ብረት በውስጤ ተሸክሜአለሁ ማለት ይጠበቅብኝ ነበር::

በመሣሪያው ዳበስ ያደርጉኝና "እውነት ነው" ብለው ፈገግ ይላሉ::

ልጆቼ "በሮቦት የሚንቀሳቀሰው ሰባኪ" እያሉ በመጥራት ኩራታቸውን ይገልጹልኛል: ይህን ስም የወሰዱት በፊልም ውስጥ ከሚታየው "ሮቦቱ ፖሊስ" ከተሰኘው ገጸ ባህሪ ነው:: ከአንድ አስጨናቂ ሁኔታን ከፈጠረ ክስተት በኋላ፤ ሃኪሞች ከፍተኛ ቴክኖሎጂ በመጠቀም በብረት ጥፍጥፎች ከጠጋገኑት በኋላ ፖሊሱ ወንጀልን ለመከላከል እንደገና ወደ ሥራው እንዲመለስ አስችለውታል::

ምንም እንኳን እነዚህ ብረቶች፣ የኤሌክትሪክ ገመዶችና ቁርቁሮዎች ዘመን ያለፈባቸው ቢመስሉም፤ የሚፈለገውን ውጤት አስገኝተው ነበር:: ሰዎች በሰውነቴ ላይ ተተክለው በሚያዩዋቸው ጊዜ ይደነግጡ ነበር:: ስንቀሳቀስ ያዩኝ እነዚያው ሰዎች አሁን ደግሞ በአግራሞት ይደነቃሉ:: ይሁን እንጂ በዚህ መጠነኛ የመጠገን ሁኔታ ውስጥ ብገባም፤ አሁንም ገና እንደገና በመስተካከል ሂደት ውስጥ እያለፍኩ ነው::



# 9

# ማለቂያ የሌለው ማስተካከያ

"ወዳጅ በዘመኑ ሁሉ ይወዳል፣ ወንድምም ለመከራ ይወለዳል"

ምሣ 17፥17

ከአደጋው በኋላ ሰዎች በተለያየ መንገድ እንዴት እርዳታን እንዳደረጉልኝ የሚያስገርም ነው:: ከአደጋው በኋላ በነበሩት የመጀመሪያዎቹ አምስት ቀናት በርካታ ጓደኞቼ የሳውዝ ፓርክ ቤተክርስቲያን አባላት ጎብኝተውኛል:: ከእነዚሁ ሰዎች አብዛኞቹ በዴቪድ ጀንቲሊስ አስተባባሪነት ከተደረገው የሌሊት የምልጃ ጸሎት በኋላ እንደገና አይተውኛል:: እያንዳንዷን ጥቃቅን የማገገም ሁኔታዬን በተመለከቱ ቁጥር ይደሰቱ ነበር:: ወደዚያ ከባድ ድብርት ውስጥ የገባሁትም እያንዳንዱ የማገገም ሂደት እጅግ ዝግ ብሎ ይከናወን ስለነበር እንደሆነ አስተውያለሁ:: ከቀዶ ጥገና ክፍሉ ውስጥ ከወጣሁ በኋላ በሆስፒታሉ ውስጥ ለአንድ መቶ አምስት ቀናት ቆይቻለሁ:: ያን ያህል ጊዜ እኔ በነበርኩበት ሁኔታ ውስጥ የሚቆይ ሰው በቀላሉ በድብርት ውስጥ እንደሚገባ እገምታለሁ::

ማገገም በጀመርኩባቸው ወራት፤ እኔ እንደገና ጠቃሚ ሰው እንደሆንኩ እንዲሰማኝ ቤተክርስቲያን ተግታ እየሠራች ነበር:: ህጻናት ይጎበኙኝ ዘንድ ወደ ሆስፒታሉ ያመጧቸውም ነበር:: አንዳንድ ጊዜ ኮሚቴዎች እኔ በተኛሁበት የሆስፒታል ክፍል ውስጥ ስብሰባቸውን

ያደርጋሉ፤ ይህ የእኔ ውሳኔ ዋጋ ያስው መሆኑ እንዲሰማኝ የተደረገ ነበር። ምንም መናገር ወይም ማድረግ እንደማልችል ያውቃሉ፤ ይሁን እንጂ እኔን ለማጽናናትና ለማነቃቃት የነበራቸው መንገድ ያ እንደሆነ በመገመታቸው ነው። እኔ ዋጋ ያለኝና የምጠቅም ሰው መሆኔን እንዳስብ ማድረግ የሚችሉትን ነገር ሁሉ አድርገዋል።

ይሁን እንጂ አብዛኛውን ጊዜ እኔ በድብርት ውስጥ ነበርኩ፤ ስለራሴም እጅግ አዝናለሁ። የነበረኝ ታላቅ መሻት ወደ መንግስተ ሰማይ መመለስ ነበር።

ከድብርቱ ሌላ፤ ሌላ ችግርም ነበረኝ። ማንም ሰው ለእኔ ምንም ነገር እንዲያደርግልኝ አልፈልግም። ያ ደግሞ ባህሪዬ ነበር።

አንድ ጊዜ ጂይ ቢ.ፐርኪንስ የተባሉ በእረፍት ላይ ያሉ አገልጋይ ሊጎበኙኝ መጡ። ጡረታ ከመውጣታቸው በፊት በደቡብ ቴክሳስ የሚገኙትን አብያተ ክርስቲያናት በመጋቢነት አገልግለዋል፤ በእኔ አገልግሎት ውስጥም ከፍተኛ ኃይል ያላቸው አባትና በጎ ተጽእኖም ያሳደሩ ሰው ናቸው። የሳውዝ ፓርክ ቤተክርስቲያንም፣ እኔ አደጋ በደረሰብኝ ወቅት በጊዜያዊነት በመቅጠር ስአገልግሎት አሰማርታቸው ነበር።

ጂይ በእምነት ይጎበኙኝ ነበር። ይህም ማለት በእያንዳንዱ ጉብኝት ከአርባ ማይሎች የበለጠ መኪናቸውን ያሽከርክሩ ነበር ማለት ነው። አንዳንድ ጊዜ በሳምንት ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ ሊያዩኝ ይመጡ ነበር። ከእርሳቸው ጋር እኩያ አልነበርኩም፤ ይሁን እንጂ ሁልጊዜም ፈገግ እያልኩ አሸኛቸዋለሁ። በተኛሁበት አልጋ ላይ ሆኜ ስለራሴ ሃዘኔታ ይሰማኝ ነበር።



በፍቅር ይናገሩኛል፤ ሁልጊዜም ሊያጽናኑኝ የሚችሉ ቃላትን ይመርጣሉ፤ ምንም እንኳን ችግሩ ከእርሳቸው ባይሆንም፤ የሚናገሩኝ ነገር ሁሉ ምንም አይጠቅመኝም። ማንም ሰው ሊረዳኝ አይችልም ነበር። እኔ አስቸጋሪ ሰው ሆኜ ስለነበር ብቻ አልነበረም፤ በኋላ ላይ እንደተረዳሁት እኔ ሁሉንም ሰው እንደ አስቸጋሪ እቆጥር ስለነበረም ጭምር ነው።

የሚጎበኙኝ ሰዎች ሊረዱኝ ይሞክራሉ፤ አብዛኞቹ ደግም መርዳት በሚችሉበት አቅም ሁሉ ነበር ሊረዱኝ የሚፈልጉት። "የምታነበውን መጽሄት ላምጣልህን?" ሲል አንዱ ይጠይቀኛል። "ከወተት የተሠራ ጂላቲ ትወዳለህን? በእንግዳ መቀበያው ውስጥ ጣፋጭ ኬክ አለ። ወይስ ሃምበርገር ላምጣልህ ይሆን? ..."

"መጽሐፍ ቅዱስ ወይም ሌላ መጽሐፍ እንዳነብልህ ትፈልጋለህ?"

"ትንሽ ላንሸራሽርህ እችላለሁ?"

መልሴ ሁልጊዜም የማይለወጥ ነበር፤ "አመሰግናለሁ አልፈልግም" የሚል ነው።

ነገሮቹ ሳያስፈልጉኝ ቀርተው እንዳልነበር አስባለሁ፤ ነገር ግን መግባባትን ወይም መተባበርን አልፈልግም ነበር። ይሁን እንጂ ሁሉንም ሰው አሉታዊ በሆነ መንገድ እመለከት እንደነበር አይሰማኝም ነበር። ማንንም ማየት አልፈልግም። ከማንም ጋር መነጋገር አልፈልግም። እኔ እፈልግ የነበረው የህመም ስቃዩ እንዲወገድልኝና ቅርጹን ያጣው አካሌ እንደገና እንዲስተካከል ነበር። በምድር ላይ መቆየት ካለብኝ፤ እንዲሻለኝና እንደገና ወደ ተለመደው ሕይወት መመለስ እፈልጋለሁ።

ጂይ አዘውትረው ይጎበኙኝ ስለነበር፤ ከጎደኞቼና ከቤተሰቦቼም ጋር እንዴት እንደተራራቅኩ አስተዋሉ:: አንድ ቀን የሳውዝ ፓርክ ቤተክርስቲያን ዲያቆን የሆነ ሰው ሊጎበኘኝ ሲመጣ አጠገቤ ተቀምጠው ነበር:: ከአስር ደቂቃዎች በኋላ ሰውዬው ከመቀመጫው ተነስቶ፤ "መጥቼ ሁኔታህን መመልከት ስለፈለግኩ ነው በዚህ ያለሁት" አለ:: ቀጠል አድርጎም፤ "ከመሄዴ በፊት ላመጣልህ የሚያስፈልግህ ነገር ይኖራል?" ሲል የተለመደ ጥያቄ ጠየቀኝ::

"አመሰግናለሁ፤ አልፈልግም:: ጥያቄህን ተቀብያለሁ ግን ..."

"እሽ የምትበላው ነገርስ ላምጣልህ፤ ታች ወርጄ ..."

"በእውነት አልፈልግም:: ስለመጣህ አመስግናለሁ" ደህና ሁን ብሎ ተሰናበተኝና ሄደ::

ዲያቆኑ ከሄደ በኋላ ጂይ በጸጥታ ረዘም ላላ ጊዜ በመስኮቱ ወደ ውጭ አሻግረው ሲመለከቱ ቆዩ:: በኋላም ወደ አልጋዬ እየተራመዱ መጥተው ወደ ፊቴ ጎንበስ አሉና፤ "እያደረግክ ስላለው ነገር ልታውቅ የሚያስፈልግህ ይመስለኛል" አሉ::

"ምን አሉ ጌታዬ?" አልኩ ማንም ሰው ለማንያ አመት እድሜ ላላቸው ሰባኪ የሚሰጠውን አክብሮት እየሰጠሁ::

"እያደረግክ ያለውን ነገር ልታውቅ ያስፈልግሃል" ሲሉ ደገሙልኝ::

"ጥሩ ነገር እያደረግክ አይደለም"

"ምን እያሉ እንደሆነ አልተረዳሁም..."



"ከዚያም በላይ ደግሞ" አሉና አሻግሬ ማየት እስከማልችል ድረስ ወደ ፊቴ ተጠግተው፤ "ከዚህም በላይ ደግሞ፤ ድርጊትህ ሁሉ ልክ እንደቀደሙት ፈሪሣውያን ነው" አሉኝ::

"ስለምን እንደሚያወሩ አላውቅም"

"እነዚህ ሰዎች እኮ ስለ አንተ ግድ የሚላቸው ናቸው፤ አንተ ግን ምን ያህል ክልባቸው እንደሚወዱህ ልትገምት አልቻልክም"

"እንደሚወዱኝ አውቃለሁ"

"እርግጠኛ ነህ? እንደዚያ ከሆነ ይህንን እደምታውቅ እንዲያውቁ ለማድረግ ጥሩ ሥራ አልሠራህም:: በትክክለኛው ሁኔታ አይደለም የምታስተናግዳቸው:: እነርሱ እኮ ሊፈውሱህ አይችሉም:: ሊፈውሱህ ቢችሉ ኖሮ ፈጥነው ያደርጉት ነበር:: በአንተ ስፍራ መሆን የሚችሉ ቢሆን አብዛኞቹ ያደርጉት ነበር:: ምንም ነገር እንዲያደርጉልህ ብትጠይቃቸው ምንም ነገር ቢሆን ያለ አንዳች ማወላወል ያደርጉታል::"

"ያንን አውቃለሁ ..."

"ነገር ግን ምንም ነገር እንዲያደርጉልህ አትፈቅድላቸውም::"

"ምንም ነገር እንዲያደርጉልኝ አልፈልግም" ምንም ነገር ሳልደብቅ በቻልኩት መጠን ሁሉ ድምጼን ከፍ አድርጌ፤ "እውነቱን ማወቅ ከፈለጉ እዚህ እንዲመጡ እንኳን አልፈልግም:: ሳይመጡ ቢቀሩ ነው የምመርጠው:: ደስ የማይል ነገር እየተናገርኩ እንደሆነ አውቃሁ:: ሥራቸውን ትተው እንደሚመጡ አውቃለሁ:: ያንን አውቃለሁ:: ማንም ሰው ወደዚህ እየመጣ እንደዚያ እንዲያየኝ ለምን እፈልጋለሁ? አስቀያሚ አስተያየት ነው:: እኔ የምጠቅም ሰው አይደለሁም::"

"እንግዲያስ ጥሪህ አይደለም"

በተናገሯቸው ቃላት እጅግ ደንግጨ ቀና አልኩ::

"ሌሎች ሰዎችን ለማገልገል የሕይወትህን መልካም ጊዜዎች ተጠቅመሃል:: ጉድለታቸውን ለመሙላት፣ በችግራቸው ጊዜ ልትረዳቸው፣ በአደጋ ጊዜ ..."

"አዎ ... እሞክር ነበር ..."

"እና አሁን ደግሞ እነዚያው ሰዎች አንተ ታደርግላቸው የነበረውን ነገር ሊያደርጉልህ ሲፈልጉ አንተ ግን ያልተገባ ሥራ ትሠራለህ"፣ የተናገሩትን ቀጣዮን ቃል በፍጹም አልረሳውም::

"ዶን፤ ሊያቀርቡልህ የሚችሉት ያላቸው ብቸኛው ነገር ያ ነው፤ አንተ ያንን ስጦታ ከእጃቸው ቀምተሃል"

ለመረታት ዝግጁ አልነበርኩም፤ በመቃወም ገለጻዬን ለመቀጠል ሞከርኩ:: እንደገና አቋርጠውኝ ጣልቃ ገቡ::

"እንዲያገለግሉህ አልፈቀድክላቸውም:: ሊያደርጉት የሚፈልጉት ያንን ነበር:: እንዴት ይህንን አትረዳም?"

ለተናገሩት ንግግር እጅግም ቦታ አልሰጠሁትም ነገር ግን፤ "አደንቃቸዋለሁ፤ ሊረዱኝ እንደሚፈልጉም አውቃለሁ:: እያደረጉ ያሉት ነገር ሁሉ ጥሩ ነው ... ግን ..."

"ግን ... ምንም የለም! ያላቸውን ፍቅር መግለጽ እንዳይችሉ መንገድ በመዝጋት እያጭበረበርካቸው ነው::"



የተናገሩት ቃል አስደነበረኝ:: እኔ ራስ ወዳድ ላለመሆንና በእነርሱ ላይ ምንም ጫና እንዳልጭንና ችግር እንዳልፈጥር እየሞከርኩ ነበር:: ከዚያ በኋላ የተናገሯቸው ቃላት አዕምሮዬን እየሰረሰሩ መግባት ጀመሩ:: እውነታው ራስ ወዳድ መሆኔን የሚያሳይ ነበር:: በዚያ ውስጥ ደግሞ የትእቢት ነገርም ነበረበት በጊዜው ልቀበለው ፍቃደኛ ባልሆንም:: ለሌሎች እንዴት ቸርነት አደርግ እንደነበር አውቃለሁ፤ ነገር ግን ኩራት የሌሎችን ቸርነት እንዳልቀበል አድርጎኝ ነበር::

ጄይ መልስ እንድሰጥ የእፎይታ ጊዜ አልሰጡኝም:: ለነገሩ ለመስማት እስረኛ የሆንኩ ሰው ነኝ:: ራሴን ከሌሎች ምን ያህል እንዳገለልኩ አምኜ እንድቀበል እስክገደድ ድረስ ስለራሴ ብዙ ነገር ተናገሩኝ:: እንደዚያም ሆኖ እንኳን ለመሟገት መፈለጌ አልቀረም፤ ጄይ ግን ስህተቴን አምኜ እንድቀበል ተጫኑኝ::

"እንዲረዱህ እንድትፈቅድላቸው እፈልጋለሁ:: እየሰማኸኝ ነው? እንዲረዱህ መፍቀድ አለብህ!"

"አልችልም-ብቃ እንዲረዱኝ ማድረግ አልችልም ..."

"ጥሩ፤ ዶን፤ ስለራስህ ስትል ይህንን ለማድረግ ባትፈልግ ስለ እኔ ስትል አድርገው" አሉ::

ስለእርሳቸው ማንኛውንም ነገር እንደማደርግ ያውቃሉ:: እናም በእሽታ ራሴን ነቀነቅኩ::

"ከዚህ በኋላ ማንም ሰው ወደዚህ መጥቶ አንድ ነገር እንዲያደርግልህ ቢጠይቅህ- ምንም ነገር ይሁን-የፈለገው ነገር ይሁን እሽ እንድትል እፈልጋለሁ:: ምናልባትም ይህንን ለሁሉም ሰው ላታደርገው ትችላላህ፤ ነገር ግን በአንድና በሁለት ሰዎች መጀመር ትችላለህ::

አንተን በመርዳት ጥቂት ሰዎች እንኳን ፍቅራቸውን መግለጽ እንዲችሉ አድርግ:: ይህን እንደምታደርገው ቃል ግባልኝ::"

"ማድረግ እንደምችል እርግጠኛ አይደለሁም"

"አዎ፣ ማድረግ ትችላለህ"

"እሞክራለሁ፤ ያንን የማደርገው ግን ወድጄ አይደለም"

"ወደህ አድርገው" በመሰላቸት ወደ እኔ አትኩረው ሲመለከቱ ቆዩና፤ "አድርገው" አሉኝ::

ዛሬ ዛሬ ሳስበው ጄይ ለእኔ ያሳዩት ትእግስት ያስደንቀኛል:: ድምጻቸውን ልስልስ አድርገው፤ "ለእኔ ስትል ሞክረው:: ታደርገዋለህ? ከዚህ የተሻለ ነገር ማድረግ ትችላለህ:: አሁን እያደረክ ያለኸው ነገር ጥሩ አይደለም:: እግዚአብሔር ልትማራቸው ከሚፈልጋቸው ትምህርቶች አንደኛው ይህ ነው:: ይህን ባለማድረግህ ለረዥም ጊዜ ተጎድተሃል:: ሰዎች እንዳይረዱህ ብትቃወም ከዚህም በላይ ትጎዳለህ::"

"ጥሩ" አልኩ:: ከዚያ በላይ መቋቋም አልቻልኩም::

እናም ቃል ገባሁላቸው:: ይህንን ካላደረኩ በቀር ትተውኝ እንደማይሄዱ ነበር::

በጉዳዩ ላይ የመጀመሪያ የተሰማኝ ብስጭት ነበር እንዲያውም ቁጣ:: ከሚገባቸው በላይ አልፈው እንደተናገሩኝ አሰብኩ፤ እፍ አውጥቼ ግን አልተናገርኩም:: እርሳቸው ከወጡ በኋላ የተናገሯቸውን ነገሮች ሁሉ ማሰላሰል ጀመርኩ:: ቁጣዬን፣ ትእቢቴንና ራስ ወዳድነቴን ካሸነፍኩ በኋላ፤ ይናገሩት የነበረው ነገር ሁሉ እውነት እንደነበር ተገነዘብኩ- ማድመጥ ይገባኝ የነበረ እውነት::



ሁለት ቀናት አለፉ፤ ጄይ የጠየቁኝን ነገር ማድረግ አልቻልኩም::

በሦስተኛው ቀን አንድ የቤተክርስቲያናችን አባል ሊጠይቀኝ ወደ ክፍሌ ገባ:: ሰላምታ እየሰጠኝና እያጫወተኝ አምስት ደቂቃ ያህል ቆይቶ ለመሄድ ከመነሣቱ በፊት፤ "እንደገና መምጣትና ሁኔታህን ለማየት እፈልጋለሁ" አለ:: "ዛሬ ደግሞ ደህና ነህ::"

ፈገግ አልኩ፤ አስከፊ ሁኔታ ውስጥ ነበርኩ፤ ነገር ግን ከእርሱ ጋር መከራከር አልፈለኩም::

ለመሄድ ተነስቶ ቆመ:: "ከመሄዴ በፊት ላደርግልህ የምትፈልገው ነገር አለ?"

"አልፈልግም፤ አመሰግናለሁ" ለማለት ከናፍርቶቼን አንቀሳቀስኩ:: እናም የጄይ ምስል ወደ አዕምሮዬ መጣ:: "ጥሩ፤ የማነበው መጽሔት ባገኝ ደስ ይለኛል::"

"ትፈልጋለህ?" በፊቱ ላይ ታላቅ ፈገግታ ታየ፤ "በርግጥ ትፈልጋለህ?"

"ይመስለኛል:: ለረዥም ጊዜ አንድም መጽሔት አላነበብኩም"

"አሁን ተመልሼ መጣሁ!" ምን አይነት መጽሔት እንደምፈልግ እንኳን ሳልነግረው በሩን በፍጥነት ከፈተና እንደ ነፋስ በረረ:: ሃያ አንድ ፎቆችን ወደ ታች መውረድ ነበረበት:: ይሁን እንጂ ከደቂቃ ባነሰ ፍጥነት ተመልሶ የመጣ ይመስል ነበር:: ተመልሶ በመጣ ጊዜ በእቅፉ የመድሔት መአት ተሸክሟል:: ያመጣቸውን መጽሔቶች ሽፋን እያሳየኝ ሳለ እንኳን ያ ትልቅ ፈገግታው በፊቱ ላይ ይታይ ነበር::

አመሰገንኩትና "ትንሽ ቆይቼ አነባቸዋለሁ" አልኩት::

በጠረጴዛው ላይ አስቀመጣቸውና ፈገግ አለ፤ "ሌላስ የምትፈልገው ነገር አለ?"

"አይ፤ አይ፤ የምፈልገው ያንን ብቻ ነው፤ አመሰግናለሁ" አንድ ሰው መልካም ነገር እንዲያደርግልኝ አንድ ጊዜ በሩን ከከፈትኩ፤ ከዚያ በኋላ ያለው ነገር እንደማይከብደኝ ተገነዘብኩ። እርሱ ከሄደ በኋላ መጽሔቶቹን ማገላበጥ ጀመርኩ። እያነበብኳቸው አልነበረም፤ ምክንያቱም ስለሆነው ነገር እያሰላሰልኩ ነበር።

ጂይ ትክክል ነበሩ። ሰዎች ለእኔ መግለጽ የሚፈልጉትን ፍቅራቸውንና ርህራሄአቸውን መግለጽ እንዳይችሉ መንገድ መዝጋቴ እውነት ነበር።

ከአርባ ደቂቃዎች በኋላ፤ ካላገቡት ቡድን መካከል የሆነች አንዲት ሴት ልትጎበኘኝ መጣች። የተለመደውን ዐይነት የንግግር ጭውውት ስናደርግ ከቆየን በኋላ፤ "አሁን እንዴት ነህ" አለች።

"ደህና ነኝ"

"ላደርግልህ የምትፈልገው ነገር አለ?"

"የለም ... እኔ ... እኔ" እንደገና የጂይ ቃላት በአዕምሮ ውስጥ ማስተጋባት ጀመሩ።

"ጥሩ፤ ምናልባት የዝንጅብል ጣዕም ያለው ከወተት የተሠራ ጣፋጭ ልታመጪልኝ ትችያለሽ"

"የዝንጅብል ጣዕም ያለው ከወተት የተሠራ ጣፋጭ፤ ያንን ላመጣልህ በጣም ደስተኛ ነኝ።" ከዚያ በፊት ፊቷ እንደዚያ በደስታ



ሲያበራ ያየሁበት ጊዜ ትዝ አይለኝም። "ተጨማሪ ነገርስ ትፈልጋለህ? የሆነ የተጠበሰ ነገር ምናልባት ያስፈልግሁ ይሆን"

"አልፈልግም"።

በሩን በፍጥነት ከፍታ ጣፋጩን ይዛ ተመለሰች። "አ! ፓስተር እንደምትወደው አምናለሁ"።

"እወደዋለሁ" አልኳት፤ እንደ እውነቱ ከሆነ የዝንጅብል ጣዕም ያለው ከወተት የተሠራ ጣፋጭ እወዳለሁ

ከዚህ በኋላ የቤተክርስቲያኔ አባላት በተኛሁበት ክፍል በር ላይ ቆመው፤ "የዝንጅብል ጣዕም ያለው ከወተት የተሠራ ጣፋጭ እንዳመጣለት ጠይቆኝ ነበር" የሚል ማስታወቂያ አማርጠው እንዳነበቡ ገመትኩ።

"አዎ እንዳንሸራሸረው ፈቅዶልኝ ነበር"።

ከዚያ በኋላ ነበር ይህንን እድል ሳልጠቀምበት ማባከኔን የተገነዘብኩት። የእኔንም ይሁን የእነሱን ዕድል ነበር የዘጋሁት። በእነርሱ ላይ ጠንክር ለማለት በመሞከሬ እኔን ለማጽናናት የነበራቸውን እድል ሁሉ ነበር ጠርቅሜ የዘጋሁት። የበደለኝነት ስሜት ተሰማኝ፤ ምክንያቱም ቢያንስ ቢያንስ ለእኔ ያላቸውን ስጦታ ማየት ችያለሁ።

ሃፍረቱ ውስጤን ሞላው፤ እናም ማልቀስ ጀመርኩ። ይሄ የእነርሱ አገልግሎት ነው። እኔ ግን ሁሉን ነገር አበላሸሁት ስል አሰብኩ። እንዲረዱኝ ባለመፍቀዴ መጠኑ ሰፊ የሆነ ሃፍረት ተሰማኝ። በመጨረሻው መንገድን በከፈትኩላቸው ጊዜ በእንቅስቃሴያቸውና በፊታቸው ገጽታ ላይ አስገራሚ ለውጥ እንዳየሁ እመሰክራለሁ። እኔን

መርዳታቸውን ወደውት ነበር:: ይፈልጉ የነበረው አንድ ነገር ለማድረግ የእድል በር እንዲከፈትላቸው ነበር፤ በመጨረሻው የሚፈልጉትን ሰጠኋቸው::

"እያደረክ ያሰውን ነገር ልታውቅ ይገባሃል::" ይህ የጆይ ፍቅር የሞላበት የግሳጼ ቃል ሰሚቀጥሉት በርካታ ሰዓታት ከእኔ አልተለየም ነበር:: እንባዬ ይወርድ ጀመር:: በዚያ ሁኔታ ውስጥ ለምን ያህል ሰዓታት እንደቆየሁ አላውቅም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ይቅርታ እንዳደረገልኝ እስከገነዘብ ድረስ ሰዓታት የተቆጠሩ ይመስለኛል::

አደርገው የነበረው ነገር ጥሩ ባይሆንም ብዙ ሰዎች ጆይ ያደረጉትን ነገር አላደረጉም:: ያ ሁኔታ ባህሪዬን ቀየረው:: ከዓመታት በኋላ አሁን እንኳን ከሌሎች ሰዎች እርዳታን ላለመቀበል በብዙ እጣጣራለሁ፤ በመጨረሻው በሩ በጥቂቱ ገርበብ ብሎ ተከፍቷል:: እንደቀድሞው ሙሉ ለሙሉ ጥርቅም ተደርጎ አልተዘጋም::

አንዳንድ ጊዜ ስሜቴ ሲቀዘቅዝ ወይም የአካል መዳከም ሲያጋጥመኝ፤ ሰዎችን የማግለል አዝማሚያ ይሰማኛል ወይም ምንም ነገር እንደማያስፈልገኝ በመቃወም እናገራለሁ:: ይሁን እንጂ ራሴን መክፈት ስችልና ሰዎች ስጦታዎቻቸውን ተጠቅመው እንዲረዱኝ ስፈቅድ ትልቅ ልዩነት እንዲመጣ አደርግ ነበር:: የፊካ ፊታቸውን ስመለከት፤ "በእውነት ይህንን እንዳደርግልህ ትፈቅዳለህ? " የሚሉ ነው የሚመስለው::

እኔ ተቃውሞዬን ሁሉ የምመስከተው በእነርሱ ላይ ችግር ላለመፍጠር እንደፈለግኩ አድርጌ ነበር፤ እነርሱ ደግሞ አሁን ያሰውን



ለውጤን የሚመለከቱት እንዲረዱኝ የእድል በር እንደከፈትኩላቸው አድርገው ነው::

ሰዎች ፍላጎቶቼን እንዲያሟሉልኝ ለመፍቀድ መማር በመቻሌ ትልቅ ውስጣዊ ደስታ ይሰማኛል:: ያንን ትምህርት የተማርኩት ደግሞ ምንም ማድረግ የማልችልበት የሆስፒታል መኝታ ክፍል ውስጥ ሆኜ በመሆኑ ደስታዬ የላቀ ነው::

አንድ ጊዜ አንድ ሰው ካማረ ሸክላ የተሠራ በላዩ ላይ ጽሁፍ የተጻፈበት ሰሌዳ ይዞ ወደ ሆስፒታል መጣ:: በመጀመሪያ የሆነ ቀልድ የመፍጠር ፍላጎት ኖሮት ያደረገው መስሎኝ ነበር፤ ምክንያቱም በላዩ ላይ፤ "እረፉ እኔም አምላክ እንደሆንኩ እወቁ" መዝ (46)፥10 የሚል ጥቅስ ነበር የተጻፈበት:: ምናልባትም ሰውዬው እኔን ለመምከር አስቦ ያደረገው ነገር ይሆናል:: ስጦታውን የሰጠኝ ሰው ማን እንደሆነ በትክክል አላስተውስም:: ያ ሰው ግን አንድ ነገር ስለእኔ ተገንዝቧል፤ ማድረግ የምችለው ነገር ማረፍ ብቻ ነበር::

ይሁን እንጂ ስጦታው የያዘው መልዕክት ለእኔ እጅግ አስፈላጊ የሆነ ነበር፤ ያንን ለመገንዘብ ግን ረዥም ጊዜ ወስዶብኛል::

ያስፈልገኝ የነበረው ነገር ውስጣዊ እረፍትና በደረሰብኝ ነገር ሁሉ እግዚአብሔር የሚያደርገውን የማናውቅ መሆኑን እውቄ መታመን እንደሆነ ለመገንዘብ ሳምንታት ተቆጥረዋል:: በምርጫዬ የመጣልኝ ባይሆንም እንኳን፤ በትክክል ለእኔ አስፈላጊ የነበረ ጥቅስ ነው::

እግዚአብሔር ዐርፌ እንድቀመጥ ግድ አለኝ:: በተፈጥሮዬ በተለየ ሁኔታ እራሴን በጽሞና የምፈትሽ ዐይነት ሰው አልነበርኩም፤ ይሁን እንጂ አመለካከቴን በጥልቀት መፈተሽ ጀመርኩ፤ ሌላ ምርጫ አልነበረኝም:: ለራሴ የነበረኝ የሃዘኔታ ስሜት እየቀነሰ መጣ:: ያለ አንዳች እንቅስቃሴ በአልጋዬ ላይ ተጋድሜ በቆየሁ መጠን፤ ጸጥታና ለውስጣዊ ዝምታ ለእግዚአብሔር ክፍት እየሆንኩለት መጣሁ::

ኢቫ ያንኑ ጥቅስ የያዘ በወርቅ የተቀረጸ እጅግ ያማረ ስጦታ አምጥታ ሰጠችኝ:: ያ ሰሌዳ አሁን በቤተክርስቲያን ባለው ቢሮዬ ውስጥ ይገኛል:: ከመቀመጫየ ላይ ሆኜ ቀና ባልኩ ቁጥር ሁልጊዜም እመለከተዋሁ::

በአልጋዬ ላይ እንደተጋደምኩ ቀናት እየጨመሩ በሄዱ መጠን፤ መንቀሳቀስ አቃተኝ:: በሌላ አቅጣጫ ተገላብጬ መተኛት እስክችል ድረስ በድምሩ ለአሥራ ሦስት ወራት በጀርባዬ ለመተኛት ተገድጃለሁ:: በሌላ አቅጣጫ ተገላብጬ የተኛሁበት ያ ተራ የሚመስል እንቅስቃሴ ከፈውሶቼ ቀናት ታላቁ ቀን ነበር::

"ኦ! እንዲህ ተገላብጦ መተኛት ጥሩ ስሜት እንደሚፈጥር ረስቼው ነበር" አልኩ ጮክ ብዬ::

ረዥምም ጊዜ በወሰደው የፈውሴ ጊዜ፤ ስለራሴ፤ ስለጠባዬና ስለ ተፈጥሮዬ ብዙ ነገር ልማር ችያለሁ:: በዶን ፒፐር (በራሴ) ውስጥ ያየኋቸውን ብዙ ነገሮች አልወደድኳቸውም:: ይሁን እንጂ በዚህ የፍጹም ጸጥታ ጊዜ ውስጥም ድብርቱ እንደቀጠለ ነበር::

ያ ድብርት እስከ ፍጻሜው ይቀጥል ይሆን እያልኩ መገረም ጀመርኩ::

ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር ሌላ ተአምር ወደ እኔ ላከ::



# 10
# ተጨማሪ ተአምራት

"እግዚአብሔርን ሁልጊዜ እባርከዋለሁ
ምስጋናውም ዘወትር በአፌ ነው::
ነፍሴ በእግዚአብሔር ትከብራለች
ገሮች ሰምተው ደስ ይላቸዋል::
እግዚብሔርን ከእኔ ጋር ታላቅ አድርጉት
በአንድነትም ስሙን ከፍ ከፍ እናድርግ::
እግዚአብሔርን ፈለግሁት መለሰልኝም
ከመከራዬ ሁሉ አዳነኝ "

መዝ (34)፥ 1-4

አንዳንድ ጊዜ ድብርቱ በመጥፎ ሁኔታ ይበረታብኛል፤ እንዲህ ሲሆን መተንፈስ እንደምችል እንኳን አላስብም:: ወደ ኋላ መልሶ ገና ቀዶ ጥገና ክፍሉ ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ መተንፈስ ባለመቻሌ የመተንፈሻ መሣሪያ እጠቀምበት ወደነበረው ሁኔታ ይወስደኛል:: ልዩነቱ አሁን ሳንባዎቼ በትክክል ይሠራሉ፤ በትክክል መስራት የማይችለው መንፈሴ ብቻ ነበር:: ተስፋ ቢስነትን የመሳሰሉ ጥቂት ነገሮች የሰውን መንፈስ እንዲዳከም ያደርጋሉ:: በጥቂት ሳምንታትና ወራቶች መቼ፣ ወይም ጭራሹን በቀረው ዘመኔ ተመልሼ ጤነኛ ልሆን እንደምችል

ሊነግረኝ የሚችል ሰው አልነበረም:: በዚህም ምክንያት ሙሉ ወደ ሆነ ድብርት ውስጥ ገባሁ::

ክፉኛ የተጎዳው ሰውነቴ እየተጠገነ እንደነበር፤ መንፈሳዊ ጥገናም ያስፈልገኝ ነበር:: እንዲህ እያልኩ ማሰብ ጀመርኩ፤ መንፈስ የሚለው ቃል የግሪክ ቋንቋ አቻ ትርጉም "ፕኑማ" ነው:: ቃሉ "ነፋስ" ወይም "እስትንፋስ" ተብሎ ሊተረጎምም ይችላል:: የግሪኩ ቃል ፐንዮሞኒያ ብለን ስምንጠራው ቃል ምንጩ ነው:: ልክ "ፐንዮሞኒያ" የተባለው በሽታ ሳንባዎቼን ባጠቃ ጊዜ፤ እርሱን ለመቋቋምና ሳንባዎቼን በአየር መሙላት አስፈላጊ እንደነበረው ሁሉ፤ የመንፈሴን ድብርት ለማስወገድ እንዲረዳኝ የእግዚአብሔር እስትንፋስ ያስፈልገኝ ነበር::

በድብርቱ እንደተያዝኩ ያወቅኩት መች እንደነበር አላውቅም:: ማገገም በጀመርኩባቸው የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ሳምንታት ውስጥ ከባድ በሆነ የአካል ስቃይ ውስጥ ስለነበርኩ ለአንድና ለሁለት ደቂቃዎች ብቻ ካልሆነ በቀር በአዕምሮዬ ውስጥ አንድ የተወሰነ ሃሳብ ለረዥም ጊዜ ማሰብ አልችልም::

በእነዚያ የመጀመሪያዎቹ ሳምንታት በውስጤ ይፈጠር የነበረውን ቁጣ ለመግታት ታላቅ ጦርነት አድርጌአለሁ:: የምቆጣው በእግዚአብሔር ላይ አልነበረም፤ ይልቁንም እግዚአብሔር ከመንግስተ ሰማይ ወደ ምድር ለምን እንደመለሰኝና በዚህ አይነት የአካል ስቃይ ውስጥ እንዳልፍ እንዳደረገ ይደንቀኝ ነበር:: ይሁን እንጂ በስቃይ ውስጥ ማለፌ እንኳን ለእኔ ትልቁ ጉዳይ አልነበረም:: ወደ ሆስፒታል ከገባሁበት የመጀመሪያ ቀን አንስቶ ስቃይ ከእኔ የተለየ ነገር አልነበረም:: እንደ ሌሎች ብዙዎች ሁሉ፤ በዚያ እውነታ ውስጥ መኖርን ተምሬአለሁ:: "ለምን?" እያልኩ እታገል የነበረው፤ ያንን ታላቅ ክብርና



የመንግስተ ሰማይን ግርማ የተመለከትኩት "በቃ ወደምድር ለመመለስ ነው?" የሚል ነበር:: በአካሌ እጅግ ተዳክሜ በነበረበት ጊዜ እንደዚያ ባለ አስቃቂ ሁኔታ እግዚአብሔር ለምን ወደምድር እንደመለሰኝ አይገባኝም ነበር:: ብዙዎች ከዚያ በበለጠ ስቃይ ውስጥም ይኖራሉ፤ ነገር ግን በሕይወት ካሉ እንኳን ጥቂቶች ብቻ ናቸው መንግስተ ሰማይን ያዩ::

ከእግዚአብሔር ይልቅ ቀዳሚው ቁጣዬ የነበረው በህክምና ባለሙያዎች ላይ ነበር:: በምድር ላይ እንድቀር የሆነው እነርሱ ሁልጊዜም ከእኔ አጠገብ የማይለዩ በመሆኑ ምክንያት እንደሆነ እገምታለሁ:: በውስጤ ጥልቅ በሆነ ቁጣና ብስጭት እነዳለሁ፤ ምናልባትም ቁጣዬ በህክምና ባለሙያዎቹ ብቻ ሳይሆን በራሴም ጭምር ነበር:: ለምንድን ነው ፈጥኖ ሊሻለኝ ያልቻለው? ፈውሴ ያልፈጠነው በእነርሱ ምክንያት እንደሆነ አሳብባለሁ:: በትክክል ማሰብ በቻልኩባቸው ጊዜዎች ማድረግ የሚችሉትን ሁሉ እንዳደረጉልኝ አስባለሁ:: ምንም እንኳን እንደምቃወማቸውና እንደምበሳጭባቸው ቢረዱትም፤ ከአጠገቤ ሳይለዩ ያለማቋረጥ ያጽናኑኝ ነበር::

ምንም አይነት ማበረታታት አልፈልግም ነበር-የምፈልገው ውጤት ወይም ለውጥ ነበር:: እንደገና ጤነኛ መሆንን ነበር የምፈልገው:: ሕይወቴ ቀድሞ ወደነበረበት ሁኔታ የማይመለሰው ለምንድነው? በራሴ መራመድ እፈልጋለሁ፤ ሁልጊዜ በሌሎች ላይ መተማመንን አልፈልግም::

የህክምና ባለሙያዎቹ ግልጽ የሆነ መልስ አይሰጡኝም:: ያ ደግሞ አዲስ የሆነ የቁጣ ማዕበል በውስጤ እንዲገባበጥ ያደርጋል:: አሁን ወደ ኋላ ዘወር ብዬ ሳስበው እርግጠኛ ነኝ፣ ይነግሩኝ የነበረው መንገር ይችሉ የነበረውን ነው፤ ይሁን እንጂ የእኔ ጉዳይ ትልቁ ጉዳይ

እንደሆነ አስብ ነበር:: ሁኔታዬን እንዲህ ይሆናል ብሎ ለመናገር ማንም አይችልም እንደ እውነቱ ከሆነ ለበርካታ ሳምንታት የተወሰኑት የሰውነት ክፍሎቼ ሲያገግሙ እንደሚችሉ መናገር ይቅርና፤ በሕይወት ለመቆየቴ እንኳን እርግጠኞች አልነበሩም::

ሌሎችን ሰዎች የመፍራትና የመጠራጠር ስሜት ይሰማኝም ነበር:: የተሻለ እንክብካቤ እንዲደረግልኝ ወይም የህመም ስቃዩ እንዲቀል ተጨማሪ መድሃኒቶች እንዲታዘዙልኝ ስጠይቅ እንኳን በመልካም መንፈስ ውስጥ ሆኜ አልነበረም:: ምንም ነገር አይስማማኝም:: የነገሮች ፍጥነት ሁሉ ተገትቶ ነበር:: ጥያቄዬን ለመመለስ ለረዥም ጊዜ እንደሚያስጠብቁኝ አስባለሁ:: ማንም ጥያቄዎቼን ለመመለስ አይፈልግም::

"ይህ ሌልዛሮቭ ፍሬም የተባለ መሣሪያ እስከመቼ ነው በላዬ ላይ የሚቆየው?" ወደ ክፍሌ የመጣውን የትኛውንም የህክምና ባለሙያ እጠይቀዋለሁ::

"እኔ አላውቅም" የሚለው የተለመደው መልስ ነው::

"ነገር ግን አንድ ነገር ማወቅ እፈልጋለሁ" እላለሁ በመጨረሻው::

"ረዥም ጊዜ፤ በጣም ለረዥም ጊዜ":: ነርሶቹ ወይም ዶክተሮቹ የሚሰጡኝ ሌላው መልስ ነበር::

ሁለት ጊዜ ያህል እርግጠኛ የሆነውን መልስ ማወቅ በመፈለግ ዶክተሩን ተጭኜ መጠየቅ ጀመርኩ::



"ሳምንታት ምናልባትም ወራት" አለኝ:: "እርግጠኛ የሆነውን ጊዜ ልንነግርህ አንችልም፤ ምክንያቱም ያንን ስለማናውቅ ነው:: የማውቀው ቢሆን ኖሮ እነግርህ ነበር::"

በትክክለኛው እሳቤ ሲገመገም ማድረግ የሚችሉትን የመጨረሻ ነገር እያደረጉ ነበር:: እኔ ግን በዚያ ጊዜ ትክክለኛ አስተሳሰብ አልነበረኝም:: የዚህ አንዱ ምክንያት የህመም ስቃዩ ነበር:: ምናልባትም የምወስዳቸው በርካታ መድሃኒቶች እንደዚያ እንድሆን ተጽእኖ አሳድረውብኝም ይሆናል፤ ያም ቢሆን እኔ የምመች በሽተኛ አልነበርኩም:: በነገሮች ሁሉ ከመርካት ይልቅ፤ "ለምንድን ነው የማይነግሩኝ? አውቀው የደበቁኝ ነገር ምንድን ነው? ሆን ብለው ያልነገሩኝ ነገሮች አሉ፤ በእኔ ላይ እየሆነ ያለውን ነገር የማወቅ መብት ደግሞ አለኝ" እያልኩ ራሴን እጠይቃለሁ::

እንቅልፍ ባጣሁባቸው በርካታ ሌሊቶች፤ በአልጋዬ ላይ እንደተጋደምኩ ነርሶቹ በእኔ ላይ ለከፋት ተማከረውብኛል እያልኩ ራሴን አሳምናለሁ:: እንደዚያ ለማድረግ ስለመፈለጋቸው የሚጠቁም አንዳች ነገር በእኔ ላይ ያለማድረጋቸው ደግሞ ያስደንቀኛል::

"እንደዚያ ካላሰቡ ታዲያ ለምንድን ነው ምንም ነገር የማይነግሩኝ፤ እዚህ ተኝቼ ብረቶቹ በእግሬ ውስጥ ተቀርቅርዋል:: ከዚህ በላይ በምን ሊጎዱኝ ይችላሉ?"

መልሱ "በምንም" የሚል ነበር:: በአደጋው በራሱ ከደረሰብኝ ስቃይ በተጨማሪ በፈውሱ ሂደት ውስጥ የደረሰብኝን ተጨማሪ ስቃይ ተቋቋምኩት:: ለምሳሌ ያህል ከቀኝ መቀመጫዬ አካባቢ ካለ ስፍራ አጥንት ወስደው በግራ እጄ ላይ በሚተክሉበት ጊዜ፤ በቆዳዬ ስድስት

ኢንች የሚያህል ስፍራ አጎድጉደው ነበር:: ያንን ክፍተት የዘጉትም የብረት ማያያዣዎችን በመጠቀም ነበር:: የብረት ማያያዣዎችን የሚያወጡበት ቀን በደረሰ ጊዜ፤ ከስጋዬ ላይ እየነቀሉ አወጧቸው:: እያንዳንዱን ብረት በሚነቅሉበት ጊዜ፤ በሳንባዎቼ ምክንያት ድምጼን ከፍ አድርጌ መጮህ ባለመቻሌ ፊቴን በስቃዩ ስሜት እኮማትሬ በታላቅ ስቃዩን የመቻል ብርታት ተቋቋምኩት:: እንደዚያ በህመም ስቃይ የተጎዳሁበትን ጊዜ አላስታውስም:: ምናልባት ይኖር ይሆናል፤ ነገር ግን በአካሌ ላይ የተቀበልኩትን ስቃይ ሁሉ ምን ያህል እንደሆነ አረስቼዋለሁ::

ብረቶቹን ከሰውነቴ ላይ ትነቅል የነበረችዋ ምስኪን ነርስ፤ እያንዳንዱን ብረት ከነቀለች በኋላ ቆም ትል ነበር:: ሃዘን በአይኖቿ ውስጥ ሞልቶ ነበር፤ ሃዘኗ የህክምናው ሂደት ምን ያህል ክፉኛ እንደጎዳኝ በመሆኑ ምክንያት እንደሆነ አውቃለሁ:: ቁመናዋ ረዘም ያለ ሁልጊዜም በተቻላት መጠን በትህትና የምትከባከበኝ ሴት ነበረች:: "በጣም አዝናለሁ፤ መጋቢ" አለች ዝቅ ባለ ድምጽ "አውቃለሁ" ስል አጉተመተምኩ:: "ምንም ልታደርጊው አትችይም":: ለአጭር ጊዜም ቢሆን ወደዚያው ወደ መጋቢነት ተግባሬ ተመልሼ አማክራት ጀመር:: እየተቀበልኩት ባለው ስቃይ ምክንያት እርሷ እንድታዝን አልፈለግኩም ነበር::

"መጋቢ፤ ለምን ትንፋሽህን አውጥተህ ጩኸትህን አትለቀውም?"

"የሚያመጣው አዲስ ነገር የለም"::

"እኔ አንተን ብሆን አንባርቀው ነበር"::



"አውቃለሁ፤ ታደርጊው ነበር" አልኳት:: ትንሽ ፈገግ እንድትልም "እናም በሆስፒታሉ ያሉ በሽተኞችን ሁሉ ትቀሰቅሻቸው ነበር"::

ሆን ብዬ በጭራሽ መጮህ አልችልም:: ምናልባትም ራሴን እስታለሁ ከሚል ፍርሃት የመነጨ ሊሆን ይችላል:: ምናልባትም ደግሞ ጩኸቴን ብለቀው እርሷም ሆነች ሌሎች እንደ ፈሪ ይቆጥሩኛል የሚል ስጋት ኖሮኝም ሊሆን ይችላል:: እስከ አሁን ድረስ እንኳን ስለ ምክንያቱ እርግጠኛ አይደለሁም:: የማውቀው ነገር ቢኖር በእኔ ፎቅ ላይ እንዳሉት ህመምተኞች መጮህ አለመቻሌን ነበር:: በሌሎች በርካታ ክፍሎች፣ በሽተኞች በየቀኑ በህመም ስቃይ ሲጮሁ እሰማቸዋለሁ:: እንደዚያ መጮህ እኔ አልችልም:: ከዚያ ይልቅ ለእኔ የሚቀለኝ ትንፋሼን ዋጥ አድርጌ እሰበስብና ከውስጤ በሚወጣ ቀዝቃዛ ላብ እገላገለዋለሁ፤ ይሁን እንጂ ሆን ብዬ መጮህ አልችልበትም ነበር::

ምንም እንኳን ጥሩ ጠባይ ያለኝ ወይም ለህክምና የምመች ቀላል በሽተኛ እንዳልሆንኩ ባውቅም፤ የድንገተኛ አደጋ ክፍል ነርሶች የሚንከባከቡኝ በከፍተኛ ትህትናና በርህራሄ ነበር:: ስለ እነርሱ ትልቅ አክብሮት እንዲኖረኝና ቁርጠኛ የነበረ ትጋታቸውን ማድነቅ እንደሚገባኝ ተምሬአለሁ:: በእኔ ላይ አንድ የተለየ ነገር እንዳዩ እገምታለሁ:: የነርሶች ቡድን አባላት ስለ እኔ ሲሉ አንዳንዶቹን የሆስፒታሉን ህጎች ያስተካክሏቸው ነበር፤ ለምሳሌም "እንኳን ደስ ያለህ" ሊሉኝ የሚመጡ ጠያቂዎቼ በቀንም ይሁን በሌሊት በየትኛውም ሰዓት ይምጡ እንዲገቡ ይፈቅዱላቸዋል:: ነገር ግን እጅግ ጣፋጭ የሆነችዋ ሰዓት የመጣችው ከአንድ መቶ አምስት ቀናት ቆይታ በኋላ ከቅዱስ ሉቃስ ሆስፒታል የወጣሁባት ዕለት ነች:: በግልጽ እንደታየው የነርስ ቡድን አባላት

እንዳንድ ዝግጅቶችን አድርገው ነበር። በሌሎች የሆስፒታሉ ፎቆች ውስጥ የሚኙትን በማስተባበር፣ ከመኝታ ክፍሌ እስከ አሳንሰሩ (ሊፍቱ) ድረስ ከዚያ ደግሞ ትጠብቀኝ እስከነበረች አምቡላንስ ድረስ በክብር ሸኙተውኛል። ሲመግቡኝ፣ ሲያክሙኝ፣ ሲያጥቡኝ ያደረጉልኝን ቀሪ ነገር የሚያውቀው ጌታ ብቻ ነው፣ በነበሩ ነርሶች ታጅቤ ወደ ቤቴ ያደረኩትን ጉዞ እጅግ አስደሳች አድርጎታል። "ማድረግ የምንችለውን ሁሉ አድርገናል። አሁን እየተሻለህ ነው፣ ወደ ሙሉ ጤንነትህ ተመልሰህ እንደገና ተመልሰህ በመምጣት ጠይቀን" የሚሉ ነበር የሚመስለኝ። በአደጋው ዕለት ወደ ሆስፒታሉ ስገባ የነበርኩበትን በሞትና በሕይወት መካከል የነበረ ሁኔታዬን፣ አሁን ወደ ቤቴ እየሄድኩ ካለሁበት ሁኔታ ጋር ያለውን ልዩነት ያነጻጽሩ እንደ ነበር እገምታለሁ።

የቅዱስ ሉቃስን ሆስፒታል ለቅቄ ከመውጣቴ በፊት ግትርነትና፣ ሁሉን ነገር የመቃወም ስሜት አሳይ የነበር ቢሆንም፣ በእነኛ ወራቶች መካከል ያለፍኩባቸው ጠንካራ የስቃይ ጊዜያቶች መንፈሰ ጠንካራነቴን አንበረከኩት። በእንባ ተሞልቼ እለቅሳለሁ። ዋጋ የሌለኝ የተጣልኩና ጥቅም አልባ እንደሆንኩ ይሰማኛል። ፈጽሞ መልሼ ደህና ልሆን እንደማልችል አድርጌ ራሴን አሳምኜውም ነበር።

"እግዚአብሔር ሆይ፣ ነገሮች እንዲህ የሆኑት ለምንድን ነው? በዚህ ማለቂያ በሌለው ስቃይ ውስጥ እንዳልፍ የተደረገውና የማላገግመውስ?" እያልኩ እንደገና መልሶ እንዲወስደኝ ወደ እግዚአብሔር እጸልያለሁ። ከዚያ በላይ መኖር አልፈልግም ነበር።



እንደገና ወደቤቴ መመለስን እፈልጋለሁ፣ አሁንም ቢሆን እኔ ቤቴ የምለው መንግስተ ሰማይን ነው።

እንዲህ ያለውን ጸሎት ያለማቋረጥ በቀናት መካከል እጸልያለሁ፣ ብዙ ጊዜ እንዲህ ባለ ሁኔታ ውስጥ ተዳክሜ በእንቅልፍ እወሰዳለሁ። ከእንቅልፌ ስነቃ በተስፋ ቢስነት ተሞልቼ ራሴን አገኘዋለሁ። ሊረዳኝ የሚችል አንዳች ነገር አልነበረም።

ከአደጋው ጥቂት ቀደም ብሎ፣ በ1960ዎቹና 70ዎቹ በኢምፔሪያልስና በእነ ዴቪድ ምስ የተዘመሩ ታዋቂ ክርስቲያናዊ ዝማሬዎችን ኦርጂናል በካሴት ቅጂዎች አዝዤ ነበር። ኢቫ፣ እነዚህን ካሴቶች ከቴፕ መጫወቻ ጋር ወደ ሆስፒታሉ አምጥታቸው ነበር፣ ይሁን እንጂ እነርሱን ለማድመጥ ምንም ፍላጎት አላደረብኝም።

ከዚያ ይልቅ ቴሌቭዥን እመለከት ነበር። አንድ ጊዜ ጓደኛዬ ለሆነ ሰው፣ "ብራዲ ባንች የተባለውን ተከታታይ ፊልም ቢያንስ ስምንት ጊዜ ያህል አይቼዋለሁ፣ በመሆኑም ገጸባህሪያቱ የሚጫወቱትን ቃለተውኔት በቃሌ አውቀዋለሁ" አልኩት።

በአንድ ጠዋት ሰዓቱ ከ3:00 - 5:00 በሆነበት ጊዜ፣ ሌላ የቴሌቭዥን ፕሮግራም ለመመልከት አልፈለግኩም፣ በመሆኑም ካሴቶቹን ለማጫወት ወሰንኩ። ነርሷ መጥታ የመጀመሪያውን ካሴት በመክተት እንዳስጀምረው ረዳችኝ።

የመጀመሪያው ካሴት የተቀረጸው በኢምፔሪያልስ የዝማሬ ቡድን ነበር፣ የዝማሬው ካሴት መጠሪያዋ "እግዚአብሔር ይመስገን" የሚል ነበር። የመዝሙሩ ግጥሞች፣ በሕይወት ውጣ ውረድ ትግል ውስጥ ካለንና ወደፊት መቀጠል እንደማንችል ከተሰማን እግዚአብሔርን

ማመስገን እንደሚያስፈልገን የሚመክሩ ስንኞችን ይዟል። ዝማሬውን እያዳመጥኩ ብዙ ብቆይም ሰዓቱ አሁንም 3:00 የሆነ እስኪመስል ድረስ ሳይታወቅ መቆየቱ ሙሉ በሙሉ የማይታመን ነበር። ጥልቅ ከሆነ ሃዘኔ የሚያላቅቀኝን አንዳች እርዳታ ፍለጋ ማድመጤን ቀጠልኩበት። በቀጣዩ የግጥሙ ስንኝ ውስጥ፤ ወደ ምስጋና ስንመለስ በጽኑ ያሰረን የሚመስለው ሰንሰለት ከእኛ ላይ ወልቆ ይወድቃል የሚል ሃሣብ አሰበት። ሙሉው ካሴት የያዘው የዝማሬ መልዕክት ያማከለው፤ ባለንበት ሁኔታ ውስጥ በመንፈስ እግዚአብሔርን ማመስገን እንደሚገባን ነው።

የዝማሬው ቡድን በሁለተኛው ቁጥር፣ ስለ ሰንሰለት ሲዘምሩ፤ ጎንበስ ብዬ የራሴን ሰንሰለት ተመለከትኩ። ብዙ ኪሎ ግራም የሚመዝን ብረታ ብረት በእጄና በእግሬ ላይ ተከምሯል። ከአደጋው በፊት ያንን ዝማሬ መቶ ጊዜ ያህል ሰምቼዋለሁ፣ ዘምሬዋለሁም። እኔ ራሴም ተጫውቼዋለሁ። ከዚያ በኋላ የዝማሬው ቃላት ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆኑ መልዕክቶች እየሆኑ መጡ፤ ከላይ የወረደ ቀጥተኛ መልዕክት።

ዝማሬውን ከመጨረሳቸው በፊት፤ በተጋደምኩበት ስፍራ ሆኜ "እግዚአብሔር ይመስገን! " እያለ የሚዘምረውን የራሴን ድምጽ አዳመጥኩ።

ያ ዝማሬ እንዳበቃ የዴቪድ ምስ፤ "ምክንያቶቹ እኛ ነን" የሚለው ዝማሬ ቀጠለ። የእርሱ ዝማሬ ደግሞ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ያለቀሰበት፣ የተሠቃየበትና የሞተበት ምክንያቶቹ እኛ መሆናችንን የሚያስታውስ ነበር። ዴቪድ በመጨረሻው እንዴት አድርጎ፤ እውተኛው የሕይወት ዓላማ ሁለንተናን ለኢየሱስ ክርስቶስ መስጠት መሆኑን እንደተረዳ ይዘምራል። ያ ለእኔ አዲስ ዝማሬ አልነበረም፤ እንደዚያ ባለ



ውድቀት ጊዜ ውስጥ ግን አንድ ነገር ሆነ። ከሙዚቃው በስተቀር ሌላ ምንም ነገር አልሰማም ነበር- ከሌሎች ክፍሎች የሚወጣ የጣር ድምጽ ወይም በኮሪደሩ ላይ የሚተላለፉ የነርሶች ኮቴ ድምጽ የለም። በአካባቢዬ ከነበረው ዓለም ፈጽሞ እንደተገለልኩ ተሰማኝ።

ከዚያ ግድቡ ተነደለ። እንባ በጉንጮቼ ላይ መዝነብ ጀመረ፤ እናም ልጠርገው አልቻልኩም፤ ልጠርገውም መሞከር አልፈለግኩም። ዝም ብሎ መፍሰሱን ቀጠለ። እንባም ሊቆም አልቻለም፤ ከዚህ በፊት አልቅሼ በማላውቀው ሁኔታ ማልቀሴን ቀጠልኩ። እርግጠኛ አይደለሁም፤ ይሁን እንጂ ያ ለቅሶ ለአንድ ሰዓት ያህል የቀጠለ ይመስለኛል።

በዝግታ እንባዬ እየቀነሰ መጣ። መረጋጋት ውስጤን ሞላው፣ ዘና ብዬና በፍጹም ሰላም ውስጥ ተጋደምኩ። ከዚያ ሌላ ተአምር እንደተከናወነ ተገነዘብኩ። ድብርቱ ከላዬ ላይ ተነሳ። ፈጽሞ ሄደ።

እንደገና ደግሞ ተፈወስኩ።

ግልጽና ቀላል የሆኑ ዝማሬዎቹ ሰወጡኝ። ኢምፔሪያልስ፣ ሰይጣን ውሸታም መሆኑን እንዳስታውስ አደረጉኝ። ሰይጣን ደስታችንን ሰርቆ በተስፋ ቢስነት ሊሞላን ይፈልጋል። በሕይወት ፍልሚያ ውስጥ ከሆንንና በዚያ መቀጠል የማንችል መሆኑ ከተሰማን፤ ያንን ሁኔታ እግዚአብሔርን በማመስገን ልንሰውጠው እንችላለን። ሰንሰለቶቻችን ከእኛ ላይ እየወለቁ ይወድቃሉ።

ዴቪድ ምስ፤ በዚህ ምድር ላይ ስንኖር ሙሉ የሆነው የሕይወት ምክንያት ምን እንደሆነ እንዳስታውስ አደረገኝ። ያለንን ሁሉ

ለእግዚአብሔር ማስረከብ - የልብ ስብረቶቻችንና ስቃያችንን እንኳን ሳይቀር:: ለመኖራችን ምክንያቱ እግዚአብሔር ነው::

ከዚያ ጠዋት ጀምሮ በቀሪው የሕይወት ዘመኔ ሕይወትን በየትኛው ውም መልኩ ተቀብዬ ለመኖር ወሰንኩ:: ያንን ውሳኔ የወሰንኩት ያለ የስነ አዕምሮ ጠበብት እርዳታ፣ ያለ ምንም መድሃኒትና ያለ ምንም የምክር አገልግሎት ነበር:: እነኛን ሁለት ዝማሬዎች በማደምጥበት ጊዜ፤ እግዚአብሔር ራሱ ፈወሰኝ:: ተስፋ ቢስነቱ ከላዬ ላይ ተነቀለ:: በአዕምሮ ላይ የተተበተበው ሰንሰለት ተበጣጠሰ:: በተጨማሪም ያለፍኩበት ማንኛውም ሁኔታ ወይም ስቃይ ኢየሱስ ያለፈበት ሰቆቃ እንደሆነ አወቅሁ::

የሥነ አዕምሮ ጠበብት የሚሰጡትን አገልግሎት እየተቃወምኩ አይደለም:: ከአደጋው በፊትም ሆነ በኋላ ብዙ ሰዎች በእነርሱ ምክር እንዲያገኙ ልኬአለሁ:: ነገር ግን እኔ ማንኛውንም እርዳታ ለመቀበል ፈቃደኛ ስላልነበርኩ፤ እግዚአብሔር አስደናቂና ለመግለጽ አስቸጋሪ በሆነ መንገድ ፈወሰኝ::

በዚያ ሥፍራ ተጋድሜ፤ ጠባዬ መቀየር ጀመረ:: የአካል ስቃዩ መቼ ከእኔ እንደሚወገድ ወይም ኤልዛሮቭ ፍሬም የተሰኘው መሣሪያ መቼ ከእኔ እንደሚላቀቅ አላውቅም፤ ይሁን እንጂ ኢየሱስ ክርስቶስ ከኔ ጋር እንደነበር አውቄአለሁ:: አሁንም ቢሆን እግዚአብሔር በዚህ ስቃይ ውስጥ እንድኖር ለምን መልሶ እንደላከኝ አላውቅም፤ ነገር ግን ያም ቢሆን ከዚያ በኋላ እጅግም ዋጋ የሰጠሁት ጥያቄ አልሆነም::

አሁን ነፃ ሆኛለሁ:: እርሱ እግዚአብሔር አዕምሮዬን ፈውሷል:: ሰውነቴ እያገገመ ያለው በዝግታ ነው፤ ይሁን እንጂ ትልቁን ድል



ተቀዳጅቻለሁ:: ከዚህ በኋላ በፍጹም ድብርት አያጠቃኝም:: ከመንግስተ ሰማይ የሆነልኝ አንድ ተጨማሪ ተአምር ነበር::

# 11

# ወደ ቤተክርስቲያን መመለስ

"እንግዲህ በጊዜው ከፍ እንዲያደርጋችሁ ከኃይለኛው ከእግዚብሔር እጅ በታች እራሳችሁን አዋርዱ፣ እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት "

1ጴጥ 5፥6-7

ለረዥርም ጊዜ የሚያውቁኝ አንዳንድ ሰዎች የመጽናናት ምሳሌ አድርገው ይመለከቱኛል:: እንደ እውነቱ ከሆነ እኔ እንደዚያ አድርጌ አይደለም ራሴን የምመለከተው:: ለአንዴም ቢሆን እንዲህ አስቤ አላውቅም፤ ምክንያቱም ስለእውነተኛው ማንነቴ ብዙ ነገር አውቃለሁ:: በተጨማሪም ከዚያ የመከራ ስቃይ ውስጥ ለመውጣት በራሴ ያደረኩት ነገር በጣም ጥቂት እንደሆነ አውቃለሁ::

እኔ ስለራሴ እንዲህ ባስብም፤ ጓደኞቼና የቤተክርስቲያን አባላት እንደዚያ ካለ ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ ውስጥ ወጥቼ ቀስ በቀስ ወደ መደበኛው ሕይወት ለመሸጋገር መቻሌን በማየታቸው እጅግ እንደተጽናኑ ይናገራሉ:: ብዙ ግለሰቦች ባሉበት ችግር ውስጥ እንዳሉ ወደ እኔ መጥተው፣ "ባለፍክበት በዚያ ሁኔታ ውስጥ አንተ ጸንተህ መቆም ከቻልክ፤ አሁን ባለሁበት ሁኔታ ውስጥ ማለፍ እችላለሁ" ብለውኛል::



በእኔ የሕይወት ልምምድ ሰዎች ልባቸው እንዲበረታታ በመሆኑ በጣም ደስተኛ ነኝ፤ ይሁን እንጂ እንደ ብርታትና የመጽናናት ምንጭ አድርጌ እራሴን ለመቀበል ታላቅ ችግር ይገጥመኛል::

አድናቆታቸውንና ምስጋናቸውን በምን ሁኔታ እንደምቀበል ይቸግረኛል፤ ምክንያቱም እኔ ያደረግኩት አንዳች ነገር የለም:: እኔ እፈልግ የነበረው መሞትን ነበር:: ያ እንዴት አድርጎ ሊያጽናና ይችላል::

ሰዎች ለሕይወታቸው እንዴት መጽናናት እንደሆንኩ ሲነግሩኝ በርግጥ አልከራከራቸውም፤ ነገር ግን ዴቪድ ጄንትልስ ወደ እኔ መጥቶ ጤንነቴ እንዲመለስልኝ እርሱና ሌሎች እንደሚጸልዩልኝ የነገረኝን አስታውሳለሁ:: እኔ አሁን በሕይወት ያለሁት ሌሎች እንድሞት ባለመፍቀዳቸው ነው:: አድናቆት የሚገባቸው ይጸልዩልኝ የነበሩት እነዚያ ጓደኞቼ ናቸው::

አብዛኛውን ጊዜ ሰዎች - አንተ በዚያ ሁኔታ ውስጥ ማለፍ ከቻልክ የሚል ሃሣብ ሲሰነዝሩ፤ ራሴን በአዎንታ እነቀንቃለሁ፤ እየተናገሩ ያሉትን ነገር እደግፋለሁ፤ በተጨማሪም፤ ማድረግ የቻልኩትን አድናቂለሁ እላቸዋለሁ፣ በእውነትም ደግሞ አስቸጋሪ በሆኑት ቀናት ያደረኩት ያንን ነበር:: አንዳንድ ጊዜ ማድረግ የቻልኩት ትልቅ ነገር ሌላ ሳይሆን መጽናት ብቻ ነበር:: ከድብርት ውስጥ ለመውጣት እጣጣር በነበረበት ጊዜም ያደረኩት ትልቁ ነገር ይህንኑ ነው:: ምናልባት እግዚአብሔር ያከበረው እርሱን ሊሆን ይችላል:: እኔ የማውቀው ነገር የለም::

በተፈጥሮዬ፤ በነገሮች ላይ ቁርጥ አድርጌ የምወስን ሰው ነኝ፤ አንዳንድ ጊዜም የግትርነት የአጎቴ ልጅ እንደሆንኩ አምናለሁ:: ይሁን

እንጂ ብዙ ጊዜያት ብቸኛ የሆነ ሰው እንደሆንኩና ማንም ሰው ሊገነዘበኝ እንደማይችል ይሰማኛል:: አሁንም እንኳን ይህ እውነት እንደሆነ አስባለሁ:: ስቃያችን መጠነ ሰፊ ሲሆንና ያለ ምንም ዕረፍት ለሳምንታት ያህል በዚያ ሁኔታ ውስጥ ስንፀና ማንም ሰው ይህን አያውቅልንም:: በምን ሁኔታ ውስጥ እንዳለን ማወቃቸውና ስቃዩን መረዳታቸው ያን ያህል ጠቃሚ መሆኑንም አላውቅም:: ጠቃሚው ነገር ሁኔታው ግድ ያላቸው መሆኑን ነው::

በግንቦት ወር አጋማሽ ላይ ከሆስፒታል ወጥቼ ወደ ቤቴ የተመለስኩ ቢሆንም፣ እስከ የካቲት ወር 1990 ድረስ እንደገና ወደ ሆስፒታል አልጋ መመለስ ግድ ሆኖብኝ ነበር:: ያም ማለት ድፍን አሥራ ሦስት ወራት ማለት ነው:: ወደ ቤቴ ተመልሼ ከተኛሁ በኋላ እንኳን ቁስሉ እያመረቀዘ በተለያዩ ሁኔታዎች ተመርገጬ ነበር:: ወደ ሆስፒታል እየተመለስኩ ከሄድኩባቸው ጊዜያቶች አንዳንዶቹ ይልቁንም የመጀመሪያዎቹ ለሕይወት አስጊ በነበሩ መመረዞች የታጠቃሁባቸው ነበሩ:: አንዳንድ ጊዜ ሁለት እና ሦስት ሳምንታት እቆያለሁ:: አብዛኛውን ጊዜ ወደ ሆስፒታል በመኪና የምትወስደኝ ኢቫ ስትሆን፣ ወደ ቤቴ እመለስ የነበረው ግን ሁልጊዜም በአንቡላንስ ነበር::

በመጀመሪያ ከሆስፒታል እንድወጣ ከተደረገበት ቀን በኋላ፣ የቤተክርስቲያኔ አባላት ከደረሰብኝ ሁኔታ አንጻር አሁን ያለሁበትን ሁኔታ እያገናዘቡ፣ እየተሻለኝ እንደመጣና እንዳማረብኝ ይነግሩኝ ጀመር:: እርግጥ ነው ማንም አፍ አውጥቶ ይህን አልተናገረም፣ ነገር ግን "ለዶን እኮ ጸልየንለታል:: ሁኔታው እንዴት እንዲህ እንደተሰወጠ የማይታመን



ነው:: እርሱ በሕይወት እንዲኖር ጸልየናል፣ ሁኔታው እንዲሰወጥም ጠይቀናል" እንደሚሉ እገምታለሁ:: በቃ እንደዚያ ነው፣ በአሳዛኝ ሁኔታ ውስጥ ነበርኩ፣ ይሁን እንጂ አሁን በሕይወት አለሁ፣ ይህ ደግሞ እነርሱ የጠየቁት ነው::

መንትያዎቼ ልጆቼ ጆይና ክሪስቶፎር በአደጋው ወቅት የስምንት ዓመት እድሜ ነበራቸው:: ሴት ልጃችን ኒኮል ደግሞ የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ ነበረች:: እያገገምኩ በነበርኩበት ጊዜ አጅግ የተጎዳሁበት ሁኔታ ቢኖር በልጆቼ ውስጥ የተፈጠረው የስቃይ ስሜት ነበር:: ብዙ ነገር አይናገሩም፣ ይሁን እንጂ ምን እንደተሰማቸው አውቃለሁ::

ከዚህ በታች ያሰፈርኩት ልጄ ጆይ በራሱ እጅ በሠራው ካርድ ላይ የጻፈልኝ ደብዳቤ ነው:: በዚህ ጊዜ ከአያቶቹ ጋር ሊኖር ሄዶ ነበር::

ሰላም አባ

አንተ እኮ የተለየህ ሰው ነህ:: እወድሃለሁ፣ ካርዱንም እንደምትወደው ተስፋ አደርጋለሁ:: እንደዚያ ያለ ሁኔታ ዳግመኛ እንደማያጋጥምህ ተስፋ አደርጋለሁ:: እወድሃለሁ አባ:: ጆይ

ከወራት በኋላ ወደ ቤቴ ስመለስ፣ የጆይ መንትያ የሆነው ክሪስ ከትምህርት ቤት በሚመለስባቸው በርካታ ከሰዓት በኋላ ጊዜያቶች፣ አልጋዬ ወደነበረበት ወደ ሰፊው ሳሎን ይመጣ ነበር:: አንዳች ቃል ሳይተነፍስ በጸጥታ ወደ እኔ ይመጣና ራሱን በደረቴ ላይ ያሳርፋል:: ምን ያህል ጊዜ በእንደዚህ ያለ ሁኔታ እንደሚቆይ አላውቅም፣ ምናልባትም ሙሉ ደቂቃ ላይቆይም ይችላል::

አንዳች ቃል አይናገርም::

ምንም ነገር ደግሞ አይፈልግም::፤ ጥቂት የፊት ገጽታው ስሜት በቂ ነበር:: ልጄ በጣም እንደሚወደኝ ይሰማኛል::

ከደቂቃዎች በኋላ፤ ክሪስ ወደ መኝታ ክፍሉ ይሄዳል፤ የትምህርት ቤት ልብሱን ያወልቅና የጨዋታ ልብሱን አጥልቆ ለመጫወት ወደ ውጭ ይወጣል:: እንዲህ ባለ ሁኔታ ነበር በየቀኑ ሰላምታ የሚያቀርብልኝ::

ሁኔታው ለእርሱ እጅግ የሚከብድ በእውነት እጅግ የሚከብድ ነበር፤ እናም እርሱ በሚያውቀው መንገድ የልቡን ውስጣዊ ሃዘን ይገልጻል::

ከአደጋው በኋላ ልክ በስድስተኛው ወር፤ ሰልጄ ለኒኮል እጅግ ልዩ በነበረው የደስታ ቀኗ ተሣትፎ ላደርግ ችዬ ነበር::

የደቡብ ባፕቲስት ቤተክርስቲያን ወጣቶችን የምታሳትፍበት ሚስዮናዊ ድርጅቶች አሏት:: ከነዚህ መካከል ታዋቂዎች የሆኑት ወንዶቹ የሚሳተፉበት፤ "የንጉስ አምባሳደሮች" የተሰኘው ሲሆን ልጃገረዶችን ያካተተው ደግሞ፤ "ልጃገረዶች በተግባራዊ ግዳጅ ላይ" የተሰኘው ይገኝባቸዋል፤ ዕድሜዋ በድርጅቱ ውስጥ ለመሳተፍ በቂ በሆነ ጊዜ፤ ኒኮል መሳተፍ ጀመረች:: አስፈላጊ የነበሩትን እንደ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማስታወስ፣ በተለያዩ የአገልግሎት ፕሮጀክቶች መሳተፍንና የተልዕኮ ጉዞዎችን ሁሉ በሚገባ አሟላች::



ዕድሜዋ አስራ አራት አመት በሆነ ጊዜም፤ ሳውዝ ፓርክ ባፕቲስት ቤተክርስቲያን በሰኔ ወር 1989 በሚደረገው ክብረ በዓል ላይ የክብር ተሸላሚ ሆና እንደምትቀርብ ተነገራት::



ዶን፣ ከአደጋው በኋላ ሴት ልጁ በምትሳተፍበት የ "ልጃገረዶች በተግባር" የዘውድ በዓል ላይ ሲሳተፍ

ይህ ሸልማት ለላቀ ተሳትፎ የሚሰጥ ስጦታ ሲሆን የሚበረከተውም በቤተክርስቲያን ውስጥ በሚዘጋጅ ክብረ በዓል ላይ ነው፡፡ እርሷ ይህንን ሽልማት ልታገኝ የቻለችው ባደረገችው የተለየ ቁርጠኛ ውሳኔዋ ነው፡፡ በእነዚህ እንቅስቃሴዎች ለመሳተፍ ራሷን በሰጠችበት ጊዜ በቤት ውስጥ ለመኖር እድሉ አልነበራትም፡፡ ጓደኞቻችን የሆኑት ሱዘንና ስታን ማዛልዲን ነበሩ ቤታቸውን ከፍተው ያስጠጓት፡፡ እናም ከእነርሱ ጋር ነበር የምትኖረው፡፡ ኒኮል ከእኔ ምንም አይነት ስነልቡናዊም ሆነ አካላዊ እርዳታ አላገኘችም፤ ምክንያቱም እኔ በሆስፒታል ውስጥ በሞትና በሕይወት መካከል ነበርኩ፡፡ የሚያበረታቱ ደብዳቤዎችን ብቻ ከእናቷ ታገኝ ነበር፤ ምክንያቱም የኢቫም ሕይወት ቢሆን በአመቺ ሁኔታ ውስጥ አልነበረም፤ እስከ ከሰዓት በኋላ በትምህርት ቤት ውስጥ ታስተምራለች፤ ከዚያ እየሮጠች ወደ ሆስፒታል ትመጣለች፤ ወደ ቤቷ ተመልሳ ትንሽ ጋደም እስክትል ከእኔ ጋር ትቆያለች፡፡

የነበሩብን ተግዳሮቶች በኒኮል ላይ ያለንን ኩራት እንዲጨምር አድርጎታል፡፡

በሽልማቱ ሥነ ሥርዓት ወቅት ከተለመዱት ነገሮች አንዱ፣ አባቶች ልጆቻቸውን አጅበው በህዝቡ መካከል አልፈው ወደ ሽልማቱ ስፍራ ይሄዳሉ፡፡ ልጃገረዶቹ ወንድሞች ካሏቸውም ደግሞ አክሊሉንና ዘንባባውን ይዘው ከኋላ ይከተሏቸዋል፡፡

የሳውዝ ፓርክ ቤተክርስቲያን ካወጣችው የሥነ ሥርዓቱ የጊዜ ሰሌዳ አንጻር ሲገመት፤ እንኳንስ አጅቤአት ወደ ሽልማቱ ሰገነት ልወጣ ይቅርና መገኘቴም አጠራጣሪ ነበር፡፡



ዶክተሮቼ በሽልማት ሥነ ሥርዓቱ ላይ እንድገኝ ከሆስፒታል እንድወጣ ስለፈቀዱልኝ ምስጋናዬ ከፍተኛ ነው፡፡ በዚያ ለመገኘት ትልቅ መሻት ነበረኝ፡፡ እርግጥ ነው ያ የሰርጓ ቀን አልነበረም፤ በወጣትነት ዕድሜዋ ውስጥ ግን ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ስፍራ ነው፤ እናም ያንን የደስታ ጊዜዋን አብሬአት ልካፈል በጣም እፈልግ ነበር፡፡

በተሽከርካሪ ብስክሌቴ ላይ ተቀምጫለሁ፤ በሕዝቡ መካከል በማልፍበት ጊዜ ኒኮላ እጄን ይዛ ነበር፡፡ ክሪስና ጆይ ከኋላችን ነበሩ፤ የእርሷን አክሊል በትራስ ላይ አድርገው ይዘዋል፡፡ በተጨማሪም እኔ የተቀመጥኩበትን ብስክሌት በመግፋት እያገዟት ነበር፡፡ ሱፍ ኮት ለብሼ ከረባት አስሬአለሁ፡፡ ከአደጋው በኋላ ያ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነበር፡፡ የለበስኩት ቱታ ሱሪ ለኤልዛሮቭ ፍሬሙ ሲባል የጎን ዚፕሮቹ ተፈተዋል፡፡

ኒኮል እጅግ የተደሰተችው በሕይወቷ ወሳኝ በነበረው በዚያ ሥነ ሥርዓት ላይ አባቷ በመገኘቱ ብቻ ሳይሆን ይልቁን በአጠገቧ ሆኖ ወደ ሽልማቱ ሥፍራ አጅቧት እየሄደ ስለነበር ነው፡፡

ከሽልማት መስጫ ሰገነቱ ላይ ሆኜ ቁልቁል ስመለከት እንባ በአይኖቼ ሞላ፡፡ ሌሎችም ሲያለቅሱ አዳምጥ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ እናለቅስና እናፌስ የነበረው እንባ በኒኮል ሕይወት ወሳኝ ስለነበረው ጊዜ የደስታ እንደነበር አውቃለሁ፡፡

ዶክተሮቹ በመጀመሪያ ወደ ቤቴ እንድሄድ ያደረጉበት ምክንያት ቤተሰቦቹ በዙሪያዬ ባሉበት ሁኔታ ውስጥ ቶሎ ያገግማል ብለው በማሰብ እንደሆነ አምናለሁ፡፡ በቤት መሆኔም የህክምና ወጭዬን በእጅጉ

የሚቀንስ ነበር፡፡ ለምን እንደሆነ እርግጠኛ ባልሆንም ከሆስፒታል በመውጣቴ በጣም ደስተኛ ነበርኩ፡፡ ለተደረገልኝ ህክምና ሁሉ ኢንሹራንስ አልነበረም ወጭዬን የሚሸፍነው፡፡ በመጀመሪያ የሠራተኞች ህብረት በኋላም የፌዴራሉ ፍርድ ቤት ጥፋተኞች እንደሆኑ ስለወሰነባቸው የቴክሳስ መንግስት ነበር ወጭውን የከፈሉት፡፡

አሁንም እንኳን በራሴ ቤት ውስጥ እያለሁ ለእኔም ይሁን ለቤተሰቤ ይልቁንም ለኢቫ ሁኔታው ቀላል አልነበረም፡፡ በየቀኑ አንድ ሰው መርፌ ሊወጋኝ ያስፈልጋል፡፡ የሰውነት እንቅስቃሴ ልምምድን ማድረግ ይጠበቅብኛል ይህ ሁሉ በእኔ ላይ ሊደረግና ለእኔም ሊደረግልኝ ግድ ነበር፡፡ ሳሎናችን ወደ ሆስፒታልነት የተለወጠ ይመስላል፡፡ ያለ አንዳች እንቅስቃሴ ተቀምጬበት ከነበረው ከዚያ ሁኔታ ውስጥ በመውጣቴ ጥሩ እንደሆነ ተሰምቶኛ ነበር፡፡ በማውቃቸው ነገሮች መካከል መሆኔ መንፈሴን አነቃቃው፡፡ በአልጋዬ ላይ እንደሆንኩ በመስኮቱ አሻግሬ አካባቢዬን መመልከት ወይም ደግሞ ሊጠይቁኝ ወደ እኔ የሚመጡትን ነጭ ጋዋን ያልለበሱ ሰዎችን መመልከቱ ያስደስተኝ ነበር፡፡

የህክምናው ቡድን እተኛበት የነበረውን አልጋና በላዩ ላይ ይተላለፍ የነበረውን ተደግፌ የምንቀሳቀስበትን አግዳሚ ብረት ላኩልኝ - ሁኔታው ሁሉ ሆስፒታል ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ እንደነበር እንዲሆን ተመቻቸ፡፡ ነርሶቹ በየዕለቱ ይጎበኙኛል፤ የአካል እንቅስቃሴዬን የሚከታተሉት ደግሞ አንድ ቀን እያለሰሱ ይመጣሉ፡፡

ፈጽሞ ከማይረሳኝ አስደሳች ትውስታዎቼ አንዱ ኢቫ ወደስራ በምትሄድበት ጊዜ ቀኑን ሙሉ ከእኔ ጋር ይውሉ የነበሩት መልካም ሰዎች ናቸው፡፡ የቤተክርስቲያናችን ሰዎች ኢቫ ወደ ማስተማር ሥራዋ



መመለስ ወይም ሥራዋን መልቀቅ እንዳለባት እንደተነገራት በስሙ ጊዜ፤ ማድረግ የሚችሉትን ሁሉ ለማድረግ ወሰኑ፡፡

የቤተክርስቲያናችን ቀዳሚ መጋቢ ሚስት የሆነችው ጂኒ ፎስተር በየቀኑ ከእኔ ጋር የሚውሉ ሰዎችን በማዘጋጀት እንዲረዱኝ አደረገች፡፡ ጂኒ፣ ያደራጀቻቸውን ሰዎች በቀልድ፤ "የደን ተቆጣጣሪዎች" እያለች ትጠራቸዋለች፤ አብዛኞቹ የቤተክርስቲያን ሴቶች ሲሆኑ ቀሪዎቹ ጥቂት ሰዎች ደግሞ ጡረተኞች ናቸው፡፡

ኢቫ በማለዳ ከቤት ወጥታ የምትመለሰው ከሰባት ሰዓታት በኋላ ነበር፡፡ የእንቅልፍ ሁኔታዬ የሚወሰነው የህመም ስቃዮን መቼ ተቋቁሚ እንደማሳልፈው ባለው ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ነው - ከዚያ በኋላ አንቀላፋለሁ፡፡ በኋላ ላይ ግን ቀስ በቀስ ሁኔታው መልክ እየያዘ መጣ፡፡ በአጠቃላይ ከማለዳው ሁለት ወይም ሦስት ሰዓት ላይ እተኛለሁ፤ ከዚያ በአስር ሰዓት አካባቢ እነቃለሁ፡፡ "የደን ተቆጣጣሪዎች" በእንቅልፍ ላይ በምሆንበት በዘጠኝ ሰዓት አካባቢ ይመጣሉ፡፡ በቤቴ ውስጥ ምሣዬን ያዘጋጁልኛል ወይም ከቤታቸው ያዘጋጁትን ምግብ ያቀርቡልኛል፡፡

አብዛኛውን ጊዜ ስነቃ አንድ ሩህሩህ ሴት ከአልጋዬ ግርጌ ተቀምጣ የእጅ ሥራዋን ስትሠራ ነው የማገኘው፡፡ ወይም ደግሞ አንድ በእድሜ ጠና ያለ ሰው ተቀምጦ ሀውስተን ክሮኒክል የተባለውን የአካባቢ ጋዜጣ ያነባል፡፡ በነቃሁ ጊዜ ጋዜጣውን ወደ ታች ዘቅዘቅ ያደርግና ፈገግ ብሎ፤ "እንዴት አደርክ፤ ምን ትፈልግ ይሆን?" ሲል ይጠይቀኛል፡፡

በየዕለቱ የማየው ትህትና የተሞላው ፈገግ ያለ ፊት ይቀያየራል፡፡ በጎ ፈቃደኞቹ የተለያዩ ቢሆኑም እንኳን ዐላማቸው አንድ ነው፡፡ ዶንን መንከባከብና ብቻውን እንዳይሆን አብሮ መቆየት፡፡

ከቀን ወደ ቀን አልጋዬ ላይ መሆኔ እየቀጠለ ሲሄድ፤ ሌሎች ለእኔ ምን ያህል እያደረጉ እንደሆነ ተገነዘብኩ:: በሆስፒታሉ ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ፤ በአልቪን ቤተክርስቲያን የነበሩ ጓደኞቼ የቤት ዕቃዎቼን ወደ አዲሱ ቤት አንገዘውልኛል:: የቀድሞው ቤት ህንጻ ስለነበር ለአሁኑ ሁኔታዬ ወደሚመችበት ምድር ቤት ብቻ ወዳለው ቤት ተዘዋውረናል::

ቀን ቀን ካለሁበት የሳሎኔ የህክምና ክፍል ውስጥ ሆኜ በመስኮት ውጭ ውጭውን እመለከታለሁ:: ብዙውን ጊዜ ትኩረቴን የማደርገው በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ህንጻ ላይ እና አዋሳኞችን በነበሩት ማት ማለርና የእነርሱም ጓደኛ በሆነው በክሪስ አልስቶን አምሮ በተከረከመው የሳር አትክልት ስፍራ ላይ ነበር:: ክሪስ አንድ ቀን የዕቃ ማጓጓዣችንን ለመዋስ የመጣ አስመስሎ ወደ ፊልም ቤት ይዞኝ በመሄድ አስደሳች ጊዜ አደረገልኝ:: ፊልሙ ምን እንደነበር እንኳን አላስታውሰውም፤ ይሁን እንጂ ምን ያህል አስቦልኝ እንደ ነበር ግን ፈጽሞ አልረሳውም:: አንድ ጊዜ የቤታችን አጥር በከፍተኛ ንፋስ ተመትቶ በወደቀ ጊዜ፤ ማንንም ለእርዳታ ከመጥራታችን በፊት መልሶ እንዲስተካከል አድርገዋል:: በማገገም ላይ በነበርኩበት ጊዜ የተደረገልንን መልካምነት ሁሉ የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው::

ማለዳው ላይ ገና በአልጋዬ ውስጥ መንቀሳቀስ ስጀምር፤ ጠባቂዎቼ ተነስተው ጥርሶቼን እንዳጸዳና ፊቴን እንድታጠብ የጥርስ ቡርሹንና የመታጠቢያ ዕቃ ያቀርቡልኛል:: አስቀድመው ጭማቂውን በብርጭቆ ቀጥሎ ደግሞ ከበድ ያለ ምሣ ይመጣልኛል::



ከመገቡኝ፣ ካጣጠቡኝና አካላዊ ሁኔታዬ በፈቀደለኝ መጠን ዘና ማለቴን ካረጋገጡ በኋላ የተለመደውን ጥያቄ ይጠይቁኛል፤ "ከመሄዴ በፊት እንዳደረግልህ የምትፈልገው ተጨማሪ ነገር ይኖራል?"

የእኔም መልስ ሁልጊዜም አይለወጥም፤ "ምንም የለም አመሰግናለሁ" እላለሁ:: አለኝ የምለው የመጨረሻ ፈገግታ ነው ብዬ ተስፋ የማደርገውን ፈገግታዬን አሣያቸዋለሁ:: ምናልባትም አልተሳካልኝም ይሆን ይሆናል፤ እነርሱ ግን ሁልጊዜም በፈገግታ ይመልሱልኛል::

"ሁሉም ነገር ጥሩ ነው አሁን ይሻለኛል::"

የሰው ልጆች አንዳቸው ለሌላቸው የሚያደርጉት መስዋእትነትና የሚሰጡት አገልግሎት ስፋት ምንም ዐይነት ድንበር የለውም:: ከጉድለቶቻችን ሁሉ ጋር፤ በአደጋውና በማገገም ላይ በነበርኩበት ጊዜ ሰዎች ያደረጉልኝ መልካምነት፤ በእርግጥም እግዚአብሔር በመልኩ እኛ ን መፍጠሩን የሚያረጋግጥ ምሳሌ ነበር::

የዕለቱ የዶን ጠባቂ መላእክት ከቤት ከወጡ አንድ ሰዓት ያህል ጊዜ ቆይቶ በሩ ይከፈታል፤ ኢቫ ረዥሙን ጊዜ በት/ቤት ካሣለፈች በኋላ ወደ ቤት ትገባለች:: ሁልጊዜም ሞቅ ያለ ፈገግታ ካሳየችኝ በኋላ ትስመኛለች::

"እንዴት ነህ ዛሬ ... ሻል አለህ?" ስትል ትጠይቃለች::

"ደህና ነኝ" እላታለሁ የምሬን::

ከዚያ በኋላ ያለውን ስሜቴን በቃላት መግለጽ አልችልም፤ በዶን ጠባቂ መላእክት መጎብኘቴ የሚፈጥርብኝ እርግጠኝነት መንፈሴን ከፍ ያደርገዋል::

ወደ ቤቴ ከገባሁ ለወራት ያህል፤ መልካም ልብ ያላቸው የዶን ጠባቂዎች አባላት፤ በውሃ ውስጥ ለሚደረግልኝ የአካል ማፍታታት ህክምና በአሊቪን አካባቢ ወደሚገኘው ስፍራ ያመላልሱኝ ነበር:: በመጀመሪዎቹ አስራ ሦስት ወራት፤ በሆስፒታል ውስጥ ባልነበርኩባቸው ጊዜዎች ሁሉ በቤት ውስጥ በነበረው የሆስፒታል አልጋዬ ውስጥ እተኛ ነበር:: ለወራት ያህል ለህክምና ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር በቀን ውስጥ ከአምስት ደቂቃ በላይ ከአልጋ ውጭ የምሆንበት ሁኔታ አልነበረም:: አንዳንድ ቀን ጭራሹን ከአልጋዬ ውስጥ አልወጣም::

በጣም አስከፊው ነገር አንድ ጊዜ በሆስፒታሉ አልጋ ውስጥ ከገባሁ ሙሉ ለሙሉ ከእንቅስቃሴ ውጭ እሆናለሁ:: ቀና ማለት አልችልም ወይም በራሴ ማድረግ የምችለው ነገር የለም:: ከሃኪሞቹ እገዛ በስተቀር በጭራሽ ተነስቼ መቀመጥ ወይም በራሴ መንቀሳቀስ አልችልም::

በዝግታና ቀስ በቀስ እንደገና መራመድን ተለማመድኩ:: ከአልጋዬ ላይ በራሴ በወረድኩበት የመጀመሪያ ቀን እንደምንም ብዬ ሦስት እርምጃዎች ተራመድኩ:: ተመልሼ ወደ ኋላዬ በአልጋዬ ላይ ወደቅኩ፤ ድካሜ ወሰን አልነበረውም:፤ ይሁን እንጂ ፈገግ አልኩ::



መራመድ ቻልኩ:: ሦስት እርምጃ ማለት ትንሽ ማለት ይመስላል፤ ይሁን እንጂ የተሰማኝ ታላቅ የድል አድራጊነት ስሜት ነው::

በዚህ ዐይነቱ አደጋ ከደረሰ ችግር የማገገምን ሁኔታ አንድን ህፃን ከማለማመድ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው:: ለረዥም ጊዜያት ተስፋ የለሽ ሆኜ ተቀምጬ ስኖር ሳለ በመጨረሻው በራሴ ወደ መጸዳጃ ቤት መሄድ ቻልኩ፤ ይህንንም እንደ ወሳኝ ድል ቆጠርኩት::

እንደገና መሄድ መቻሌ፤ አንድ ድል ብቻ አልነበረም፤ ይልቁንም እኔን ለመርዳት ያለ አንዳች ድካም ይሠሩ ለነበሩ በመቶ ለሚቆጠሩ የህክምና ባለሙያዎችም ክብር ነበር:: አንዱን እግሬን አንስቼ ከሌላ ፊት ማስቀደም ለእኔ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ ባያውቁትም፤ በእኔ ይተማመኑ ለነበሩ ጓደኞቼና ቤተሰቦቼ ሁሉ ጭምር ታላቅ ክብርም ነው::

እኔ፣ መራመድ መቻልን የተወሰኑ ድሎችን እንደሚወክል አድርጌ ነው የምቆጥረው፤ ይህንንም ስል በመጠኑም ቢሆን እንደገና ወደ መደበኛው ሕይወት መመለሴን ነው የሚያሳየው:: ሁልጊዜም ወደ ኋላ መለስ ብዬ በትሪኒቲ ፒንስ የጉባኤ አዳራሽ ግቢ ውስጥ እኔና ጄ.ቪ. ቶማስ የነበረንን የመጨረሻውን የጉዞዬን ምሽት አስበዋለሁ:: ያ ከዚያ በኋላ ያልተራመድኩት የመጨረሻው የጤነኝነት እርምጃዬ ነበር:: ከአደጋው በኋላ ባሉ ለብዙ ወራት እንደገና ለመራመዴ ማንም ሰው እርግጠኛ አልነበረም:: በጣም ለረዥም ጊዜ እነኛን ሦስት እርምጃዎች የመራመዴ ጉዳይ ልክ ኤቨረስት ተራራን እንደወጣሁ ያህል የተቆጠረ ነበር::

“ተሳካልኝ!” ጾጥ ባለው ክፍል ውስጥ ጩኸቴን ለቀቅኩት::

“ተራመድኩ! ተራመድኩ እኮ!”

በቤቴ ውስጥ በራሴ እነዚያን ሦስት እርምጃዎች መራመዴ ቀስ በቀስ ከተፈጸመው የማገገሚያዬ ጊዜያቶች ሁሉ ትልቁን ስፍራ የያዘው ነው:: እነዚያ ሦስት እርምጃዎች እንደገና ጤነኛ እንደምሆን እሳምነውኛል:: አሁን ወደ ፊት ጠንክሬ ለመሥራት ዓላማ አለኝ:: ያለፍኩበት የማገገም ሂደት እጅግ ዘግናኝ ነበር:: ገናም ሁኔታዬ እየተሻሻለ እንደሚሄድ አውቃለሁ:: በእያንዳንዱ ቀን ሌሎች ተጨማሪ እርምጃዎች አደረግኩ:: በሳምንቱም መጨረሻ ላይ ሳሎኑን ሙሉ ለሙሉ መዞር ጀመርኩ::

ኢቫ ወደ ቤት መጥታ የእለቱን የተሻሻለ እንቅስቃሴዬን ሳደርግ በተመለከተች ጊዜ ያሳየችኝ ፈገግታ፤ የማራቶን ሩጫ ሮጬ ያሸነፍኩ ያህል እንዲሰመኝ ነው ያደረገኝ:: በዚያ ከሰዓት በኋላ በፍጹም ደስታ ውስጥ ስትፍለቀለቅ ቆየች፤ እኔም በቤቱ ዙሪያ በራሴ መራመድ መቻሌን አሳየኋት::

ከሆስፒታሉ ወደ ቤት ከገባሁበት ከሳምንት በኋላ ወደ ቤተክርስቲያን ለመሄድና በእሁድ ማለዳ ፕሮግራም ለመሳተፍ ወሰንኩ::

ዛሬ ወደ ኋላ ዘወር ብዬ ሳስበው ያለጊዜው የተደረገ ውሳኔ ነበር፤ ነገር ግን ከምወዳቸው ሰዎች ጋር እንደገና አብሮ የመሆንና እብሮም የማምለክ በውስጤ የሚቀጣጠል መሻት ነበረኝ:: ጥቂት ሰዎች ባሉበት ቡድን እረዳትነት ወደ ስፍራው እንዲወስዱኝ እቅድ አወጣን:: ምን አልባት ሁኔታው የማይሳካ ከሆነ በሚል ስጋት ሌሎችን ሰዎች ግራ ላለማጋባት ለጉባኤው አስቀድመን ማስታወቂያ ላለመናገር ወሰንን::



አንድ ሰው ከአልጋዬ ውስጥ ሊያወጣኝና ሊያስገባኝ እስከቻለ ድረስ፤ በዚያን ጊዜ በተሽከርካሪው ብስክሌት ላይ በራሴ መቀመጥ እችላለሁ፤ ይሁን እንጂ ያኔም በራሴ መቆም አልችልም:: ስድስት ሰዎች ከቤተክርስቲያን ወደ ቤታችን መጡ፤ ከቤተክርስቲያን ካሉ መኪናዎች አንዱን ይዘውም መጡ:: በቤተክርስቲያን ውስጥም በበሮቹ ያለ ችግር መግባት የምችልበትን ሁኔታ አመቻችተውልኝ ነበር::

በእነዚህ ሰዎች' ላይ የጣልኩባቸውን ትልቅ ሃላፊነት ማሰብ ጀመርኩ፤ ደጋግሜም ይቅርታን እጠይቃቸው ነበር፤ እነርሱ ግን ይህን በማድረጋቸው ደስተኞች እንደሆኑ ይገልጹልኝ ነበር::

ከዚያ በኋላ የጂይን ቃላት ማሰብ ጀመርኩ:: በአደጋው የመጀመሪያ ቀን ጓደኞቼና ቤተሰቦቼ መጥተው ተመለከቱኝ:: ምን እመስል እንደነበረ በጭራሽ አላየሁም:: ድንጋጤውንና ፍርሃቱን ሁሉ ታግሰው ተቋቋሙ:: እንደምሞት ወይም እስከዘለቄታው አካለ ስንኩል ሆኖ ይቀራል በሚል ግምት መሪር ሃዘን አዘኑ:: በተወሰነ መልኩ ይህ አሰቃቂ ክስተት ከእኔ ይልቅ አስቸጋሪነቱ ለቤተሰቦቼና ለጓደኞቼ ነበር:: እኔን ለመርዳት ፍጹም ፈቃደኞች ነበሩ:: በሌላ እቅጣጫ ከተመለከትነው፤ አሁን ያሳየሁት ለውጥ የእነርሱም ማገገም ነው፤ በመሆኑም ለእኔ አሁንም የተለየ ነገር ማድረጋቸውን እንደ ትልቅ ደስታ ነው የቆጠሩት::

በዚያ ማለዳ በአምልኮ ፕሮግራም ላይ ለመሳተፍ ከፍተኛ ፍላጎት ቢኖረኝም፤ ሰዎቹ ሁሉንም ነገር ለእኔ እንዲያደርጉልኝ ማድረግ አስቸጋሪ ነበር:: ሙሉ ለሙሉ ምንም ማድረግ የማልችልና ሙሉ ለሙሉ በእነርሱ ላይ ራሴን የጣልኩኝ ነበርኩ:: ያንን ሁኔታ ደግሜ ሳስታውሰው ፈገግ እላለሁ::

“እመሰግናለሁ” አልኳቸውና እንዲረዱኝ ሁሉን ነገር ተውኩላቸው::

በጥንቃቄ ከመኪናው ላይ አወጡኝ፤ እናም ወደ ቤተክርስቲያን ወስደው በኋላው በር በኩል አስገቡኝ:: የመኪናውን በር አንድ ሰው ሲከፍት ወደ አምልኮው አዳራሽ ይሄዱ የነበሩ ሰዎች አዩኝ::

“ተመልከቱ! ፓስተር ዶን እኮ ነው!” ሲል አንድ ሰው ጮኸ::

ሰዎቹ በተንቀሳቃሹ ወንበር ላይ እየገፉ ሲወስዱኝ፤ መንገድ እየለቀቁ በምስጋናና በጭብጨባ ሲጮሁ እሰማቸው ነበር::

ከዚያ በኋላ ሁኔታዎች ሁሉ ድብልቅልቅ አሉ:: ሰዎች እየሮጡ ወደ እኔ መጡ:: እጅግ ብዙዎች እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር:: እያንዳንዱ ሰው እኔን ለመንካት ወይ ለመጨበጥ የሚፈልግ ይመስል ነበር::

በመጨረሻው አንድ ሰው በተሽከርካሪው ብስክሌት እየገፋ ወስዶ በመድረክ ላይ ከኦርጋን መሣሪያው አጠገብ አስቀመጠኝ:: እኔን ከብስክሌቱ ላይ ማንሳት የሚቻል ነገር አልነበረም::

ከዚያ በኋላ መላው የጉባኤ ተካፋይ በመድረኩ ላይ እንደወጣሁ አወቀ:: ፈገግ እንዳልኩ እንዲህ ስል አሰብኩ፤ በትሪኒቲ ፒንስ ካደረጉት የመጨረሻ ጉባኤ ወደ ቤተክርስቲያኔ እስከቀላቀል ድረስ አምስት ወራት ፈጅተውብኛል:: ምናልባት በጣም ዝግ ብዬ ይሆናል፤ ነገር ግን ታማኝ ነኝ::

ከዚህ በኋላ ደግሞ አንድ ሰው ወደ ጆሮዬ ጠጋ አለና፤ ለጉባኤው አንድ ነገር እንድትናገር እንፈልጋለን አለ:: ወደ ኋላዬ ዞሮ ብስክሌቱን እየገፋ ወስደና ከመድረኩ ፊት ለፊት አቆመኝ::



በዚያ ጊዜ ነበር የድካም ስሜት በውስጤ ሲፈስ የተሰማኝ:: ምናልባትም ከቤቴ እሁን እስካለሁበት ስፍራ ባደረኩት ጉዞ ጉልበቴ አልቆ ይሆናል፤ ነገር ግን ተመልሼ በቤተክርስቲያን ለመገኘት ከነበረ ቁርጠኛነት የተነሳ፤ እየተሰማኝ የነበረውን የድካም ስሜት እምኜ አልተቀበልኩትም:: ከአልጋ ውስጥ ከወጣሁ ከሁለት ሰዓት በላይ ተቆጥሯል:: እስከዚያ ሰዓት ድረስ ከአልጋ ወጥቼ የቆየሁበት ረዥሙ ሰዓት ያ ነበር:: በተጨማሪም በተሽከርካሪ ብስክሌት ላይ የቆየሁበትም ረዥሙ ጊዜ እርሱ ነው::

በዚያች ቅጽበት ወደ ቤተክርስቲያን ተመልሼ ለመምጣት በመወሰኔ የሞኝነት ሥራ እንደሠራሁ ተገነዘብኩ:: ምክንያቱም ያን ለማድረግ በሰውነቴ አልጠነከርኩም ነበር:: እልኸኝነቴ ቁርጠኝነቴን ከፍ አድርጌ እንዳይ አድርጎኝ ነበር::

ምናልባትም የዚያኑ ያህል ከፉ የሆነው ነገር፤ ጉባኤው የፍቅር ምላሹን የሰጠኝ ጊዜ ኃይለኛ በሆነ ስሜታዊ ማዕበል ውስጥ መግባቴ ነበር:: መናገር መቻሌን እንኳን በእርግጠኝነት አላወቅኩም::

ለብዙ ሳምንታት በመካከላቸው ሳልገኝ ቆይቼና ደግሞም አሁን በማየውና በምሰማው ሁኔታ ውስጥ ሆኜ ምን ማለት እችል ነበር?

ይህንን ሁሉ በማገናዘብ ላይ በነበርኩበት ጊዜ አንድ ሰው የድምጽ ማጉያውን አምጥቶ በእጄ አስጨበጠኝ:: መናገሪያውን አጥብቄ እንደያዝኩ እንዲህ ስል ማሰቤን ቀጠልኩ፤ እናንተ በዚህ ያላችሁ ሰዎች፤ እየተሻለኝ ለመሄዴና ለማገገሜ ያደረግኩት አስተዋጽኦ በጣም ጥቂት መሆኑን ገና አላውቃችሁም:: እናንተ ድል እንዳደርኩ ቆጥራችሁታል:: እኔ ግን የማየው በሕይወት መቆየት መቻሌን ብቻ ነው::

ከዚያ በኋላ ድንገት የፈነዳ የማያቋርጥ ጭብጨባ ተሰማ:: እኔን በማየታቸው የተሰማቸውን ደስታ ለመግለጽ ያደረጉት ነው የመሰለኝ:: እንደዚያ ባለ ሁኔታ ለእግዚአብሔር የቀረበውን ምስጋና ለመቀበል ዝግጁ አልነበርኩም:: በህንጻው ውስጥ የነበረው ሰው ሁሉ ቆሟል ጭብጨባውም ቀጥሏል ለረዥምም ጊዜም ያለማቋረጥ ዘልቀዋል:: በመጨረሻም እንዲያቆሙ እጄን በማወዛወዝ ምልክት አሳየኋቸው::

ወደ እነርሱ ትኩር ብዬ ስመለከት፣ ስለጭብጨባቸውና ስለ ታላቁ ደስታቸው የሀሊና ወቀሳ ተሰማኝ:: እነኛ ሰዎች ለእኔ ማጨብጨባቸውን ማመን አልቻልኩም:: ቢያውቁ ኖሮ . . . ቢያውቁ ኖሮ፣ ስል አሰብኩ::

ከዚያ እግዚአብሔር ተናገረኝ:: የእግዚአብሔርን ድምጽ በውስጤ በግልጽ ከሰማሁበት ጊዜዎች አንዱ ነበር::

"የሚያጨበጭቡት ለአንተ አይደለም"

የሰማሁት እነኝህን ቃላት ብቻ ነው፣ ነገር ግን ልዩነት ያመጡ ቃላት ነበሩ፣ እናም መናገር ቻልኩ:: በመጨረሻው ሁሉም ነገር ግልጽ ሆነልኝ:: እግዚአብሔር ለእኔ ስላደረገው ነገር ሁሉ ምስጋናን እያቀረቡ ነበር:: እግዚአብሔር እንደገና አንድ ጊዜ ከሞት ወደ ሕይወት መለሰኝ:: ትንሽ ዘና አልኩ:: ያ እግዚአብሔርን የማመስገን ጊዜ ነበር:: እኔን ለማግነስ የተደረገ ነገር አልነበረም::

ጭብጨባው እስኪቆም ድረስ ረዥም ለሚመስል ጊዜ መጠበቅ ነበረብኝ:: አራት ቃላትን ብቻ ነበር የተናገርኩት:: በዚያ የተከበረ ቀን በዚያ የነበረ ማንኛውም ሰው ቃላቶቹ ምን እንደነበሩ ይነግራችኋል፣ "እናንተ ስለጸለያችሁ በዚህ አለሁ::"



ጉባኤው እንደገና ጭብጨባውን አስተጋባው:: ሌላ ነገር ጨምሬ ብናገርም እንኳ ማንም ሰው እንደማይሰማኝ እርግጠኛ ነበርኩ::

ልናገረው አልቻልኩም፣ ይሁን እንጂ በዚያ ጊዜም ይሁን አሁን ድረስ፣ ልተርፍ የቻልኩት በርካታ ሰዎች እንድተርፍ በመፈለጋቸው ምክንያት መሆኑን አምናለሁ:: ድካም የማያውቁ፣ ፍቅርን የተሞሉና ተስፋን የማይቆርጡ እንዲሁም እግዚአብሔር እንደሚሰማቸው የሚያምኑ ሰዎች ነበሩ:: ከዚያ በፊት የምር ጸልየው የማያውቁ ሰዎች እንኳን ለእኔ ጸልየዋል:: አንዳንዶቹም ለዓመታት ያህል የምልጃን ጸሎት ጸልየው የማያውቁ ናቸው፣ እግዚአብሔር እንዲምረኝ ለእኔ ግን ይጮኹ ነበር:: በእኔ ላይ የደረሰው ነገር ሰዎችን በጉልበታቸው እንዲወድቁ አደረገ፤ እናም አብዛኞዎቹ በዚህ ሂደት ውስጥ ለእኔ በመጸለይ የጸሎት ሕይወታቸው ተቀይሯል::

በሕይወት መኖር በቻልኩ ጊዜ፤ የጸለዩልኝ እነዚያው ሰዎች፣ በተለይም አስቀድሞ እምብዛም የመጸለይ ልምድ ያልነበራቸው፤ ያ ልምምዳቸው የጸሎት ነገራቸውን ወደ አዲስ እመርታ እንደቀየረው ተናግረዋል:: አንዳንድ ሁኔታዎችን ስንመለከት፤ በኮተንውድ፣ በአሪዞና፣ በቡፋሎና በኒዩርክ የነበሩ፤ ፈጽሞ የማላውቃቸው የደረሰብኝን ነገር የሰሚ ሰሚ የሰሙ ናቸው:: ቀጥሎ በነበሩት ሦስት ዓመታት ሰዎች ወደ እኔ እየቀረቡ፤ "በቪዲዮ በተሠራጨ ቃለ ምልልስ ውስጥ ተመልክቼሃለሁ፤ እጸልይልህ የነበርከው ሰው አንተ ነህ!" ይሉኛል:: ወይም ደግሞ የእኔ ቤተክርስቲያን ያሰራጨችውን ቴፕ ክር አድምጠው ከሆነ፤ "አንተ ነገሩ ምን እንደሆነ ላታውቅ ትችላለህ:: እግዚአብሔር ጸሎታችንን ሰምቷል፤ እንተም በሕይወት በመኖርህ በጣም ደስተኞች ነን" ይሉኛል::

አንዳንድ ግለሰቦች፣ እኔ ሰው ብቻ ሳልሆን ምሳሌ አድርገው ነው የሚ.ቆጥሩኝ። ለእነርሱ እኔ የጸሎት መልስ ነኝ። በሳውዝ ፓርክ ቤተክርስቲያን የነበረኝን አገልግሎት ያስታውሱ ይሆናል ወይም ደግሞ ምናልባት የሰብኳቸውን አንዳንድ ስብከቶችም አድምጠው ይሆናል። ነገር ግን አብልጠው ያስታውሱ የነበረው ነገር የእግዚአብሔርን ፊት ለመፈለግ አጥብቀው፣ በትህትናና በቁርጠኝነት የጸለዩበትን ሁኔታ ነው። እኔ በሕይወት እንድኖር ለእግዚአብሔር ልመናን አቀረቡ - እናም በሕይወት አለሁ። እንዴት በሕይወት እንደኖርኩ አላውቅም፤ ማለት የምችለው ይህ ነገር ከእኔ ውጭ የሆነና ከእኔም አቅም በላይ የተከናወነ ነው።

እንደገናም ደግሞ ሰዎች እንዲመለሱላቸው ለሚፈልጓቸው ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የተገባኝ ሰው እንደሆንኩም አስባለሁ።

በመንግስተ ሰማይ ስለነበረኝ ቆይታ ለሰዎች መናገር ከጀመርኩበት ጊዜ አንስቶ፤ ወደኔ እየመጡ፤ "መንግስተ ሰማይ በእርግጥ እውን ናት?" እያሉ የጠየቁኝን ሰዎች ቁጥር ማስላት አልችልም። በእውነት መንግሥተ ሰማይ ምን ትመስላለች? እያሉ ይጠይቁኛል ወይም ደግሞ የተለዩ ጉዳዮችን ማለትም "ለእግዚአብሔር ይቀርብ ስለነበረው ምስጋና" ወይም "ከወርቅ ስለተሠሩት መንገዶች" ይጠይቁኛል አንዳንድ ሰዎች በቅርቡ የተለዩዋቸውን የሚወዷቸውን ሰዎች ሁልጊዜም ደጋግመው የሚጠቅሱዋቸው ይመስላሉ።

እኔ በእዚያ እንደነበርኩ ማወቃቸው፤ ወደ ምድር መመለሴና ከእነርሱም ጋር ለመነጋገር የመቻሌ ነገር ለብዙዎች ጥልቅ የሆነ መጽናናት ያመጣላቸው ይመስላል። አንዳንዴ ለኔም ግርም ይለኛል።



ሌሎች ደግሞ ዛሬ ድረስ በሰውነቴ ላይ ያሉትን ጠባሳዎች ከተመለከቱ በኋላ፤ በዚህ ሁሉ ነገር አልፈህ በሕይወት በመቆየትህ፤ "አንተ ራስህ ተአምር ነህ!" "አንተ ተጓዥ ተአምር ነህ!" ይሉኛል።

# 12

# መንገዱ ተከፈተ

"ድንኳን የሚሆነው ምድራዊ መኖሪያችን ቢፈርስ በሰማይ ያለ በእጅ ያልተሠራ የዘላለም ቤት የሚሆን ከእግዚአብሔር የተሠራ ህንጻ እንዳለን እናውቃለን። በዚህ ውስጥ በእውነት እንቃትታለንና፤ ከሰማይም የሚሆነውን መኖሪያችንን እንድንለብስ እንናፍቃለን፤ ለብሰን ራቁታችንን እንገኝም። በእውነትም የሚሞተው በሕይወት ይዋጥ ዘንድ ልንለብስ እንጂ ልንገፈፍ የማንወድ ስለሆነ በድንኳኑ ያለን እኛ ከብዶን እንቃትታለን"

2ቆሮ 5፥1-4

እግዚአብሔር የቅርብ ጓደኛዬ የሆነውን ዴቪድ ጂንቲልስን ተጠቅሞ በሕይወት እንድኖር አደረገ፤ ስለዚህ ነገር አመሰግናለሁ። እንደገናም ደግሞ በግምት ከአደጋው ከሁለት ዓመታት በኋላ በሕይወቴ የተጠቀመበት ይህንኑ ሰው ነበር።

ከዚያ በፊት መንግስተ ሰማይ ስለመድረሴ ለማንም ሰው አልተናገርኩም። ጠቅለል ባለ መልኩ ለኢቫ ነግሬአለሁ፤ ነገር ግን ሁልጊዜም እርሷ ጥያቄ ከመጠየቋ በፊት ነበር ጭውውታችንን ፈጥኜ የምዘጋው። እርሷ እኔ ሳልናገራትም ያጋጠመኝ ነገር ከመታወቅ የሚያልፍ እንደነበረ ተረድታዋለች። ሌላ አንዳች ተጨማሪ ነገር እንድናገር ባለመጫኗ ላመሰግናት እወዳለሁ።

ከኢቫ ልደብቀው የምፈልገው ኖሮኝ አልነበረም፣ ጉዳዩ፤ ስለ መንግስተ ሰማይ ልምምዴ መናገር አልችልም ነበር። በዚያ ጊዜ



ሁኔታው እጅግ የሚያስፈራ በመሆኑና እርሱን ለመግለጽ መሞከር ክስተቱን ሊያሳንሰው ይችላል የሚል ስሜት ነበረኝ።

ከሆስፒታል ከወጣሁ ከአንድ ዓመት ተኩል በኋላ ዴቪድ ወደ ሀውስተን አካባቢ ለደቀመዝሙር ሳምንት ጉባኤ መጣ። ይህንን ያደረገው ሁኔታውን በመጠቀም ወደ ቤቴ መጥቶ ሊጎበኘኝና ጥቂት ሰዓቶችን አብረን እንድናሳልፍ በማሰብ ነው።

ሁለታችን ብቻችንን በሆንን ጊዜ፤ በቀዶ ህክምናው ክፍል ውስጥ በነበርኩበትና ከእርሱ ጋር በተገናኘን ጊዜ፥ ከዚያ በላይ መቀጠል እንደማልችል የነገርኩት ነገር ትዝ አለኝ። በዚያ ጊዜ ነበር በዚህ ጉዳይ ላይ እንደሚጸልይልኝ የነገረኝ ስለዚያን ቀኑ ነገር አወራን፤ ስለጓደኝነቱና ስላደረገልኝ ያላሰለሰ ፀሎት አመሰገንኩት።

"አሁን እንዴት ይሰማሃል?" ሲል ጠየቀኝ።

"የህመም ስሜት" ፈገግ ለማለት እየሞከርኩም፤ "እኔ ሁልጊዜም በህመም ስሜት ውስጥ ነኝ፤ ይሁን እንጂ አሁን የከፋው ችግሬ እርሱ አይደለም" አልኩት።

ወደ እኔ ጠጋ አለና፤ "የከፋው ችግር ምንድን ነው?" አለኝ። "በቃ ወዴት እየሄድኩ እንደሆነ አላውቅም፤ ስለ መጻኢ ሕይወቴ ጥርት ያለ መመሪያ አላገኘሁም።"

ዴቪድ ምን ማድረግ እንደምፈልግ፣ በአካል ጉዳቴ ምክንያት ማድረግ የማልችላቸውን ነገሮችና በሳውዝ ፓርክ ቤተክርስቲያን መቀጠሌን እግዚአብሔር ይፈልገው እንደሆነ እርግጠኛ አለመሆኑን ስነግረው ያደምጠኝ ነበር። በዚያ ተወዳጅና ተፈላጊም ሰው እንደሆንኩ፤

ነገር ግን መሆን የሚገባኝ በዚያ ስፍራ ስለመሆኑ እርግጠኛ እንዳልሆንኩ አጫወትኩት::

ለረዥም ጊዜ ዝም ብሎ ሲያዳምጠኝ ከቆዬ በኋላ፤ "ከአደጋውና ከማገገምህም የተማርከው ነገር ምን ነበር?" ሲል በትህትና ጠየቀኝ::

ለሦስትና ለአራት ደቂቃዎች ያህል ብዙ ነገሮችን በተለይ ደግሞ ሌሎች ሰዎች በእኔ ጉዳይ እንዲገቡ ስለመፍቀዴና እንዲረዱኝም መንገድ ስለመክፈቴ ነገርኩት:: በመቀጠልም፤ ነገር ግን በዚህ ሁሉ ስቃይና ተስፋ በመቁረጥ ሁኔታ ውስጥ፤ "መንግስተ ሰማይ እውን መሆኗን አውቄአለሁ" አልኩት::

ቅንድቦቹን በአግራሞት ከፍ አድርጎ "እንደዚህ ስትል ምን ማለትህ ነው?" ሲል ጠየቀኝ::

ቀስ በቀስ ፈራ ተባ እያልኩ በጥቂቱ በጣም ጥቂት - በመንግስተ ሰማይ ስለነበረኝ አጭር ቆይታ አጫወትኩት:: "እባክህ ጨምረህ ንገረኝ" አለ:: ጓደኛዬ ስለነበር ስለጉዳዩ እንዲያውቅ እፈልግ ነበር:: እንዲሁም ደግሞ ስለ መንግስተ ሰማይ ለዴቪድ ብነግረው እጅግ በርካታ ሰዎች ሊረዱኝ ከሚችሉት ይልቅ እርሱ ሊረዳኝ ይችላል ስል ገምቻለሁ::

"በአደጋው ወቅት ሞቼ ነበር:: ቀጥሎ በነበረው ቅጽበት ግን በመንግስተ ሰማይ ነበርኩ" አልኩት::

ወደ እኔ ተጠጋ፤ በጸጥታ ሆኖ ቀጣዩን ነገር እስክናገር ይጠብቅ ነበር:: በአይኖቹ ውስጥ የሚያበራው ደስታ ይታየኝ ነበር::

ብዙ በነገርኩት መጠን፤ ብዙ ለመስማት ያለው ጉጉት እየጨመረ ሄደ:: ዛሬ ሁኔታውን ወደ ኋላ መለስ ብዬ ሳስበው፤ ዴቪድ



በመንፈሱ ሃሴት ያደረገበት ምክንያት በሁለት ምክንያቶች ማለትም እኔ ደግሜ እያረጋገጥኩለት ስለነበረው የመንግስተ ሰማይ እውነታና ከረዥሙ የስቃይ ሁኔታዬ ውስጥ መልካም ነገር እንደወጣ በማወቁ እንደሆነ አምናለሁ::

በመንግስተ ሰማይ ስለነበረኝ ቆይታ ካጫወትኩት በኋላ ምንም ነገር አልተናገረም፤ በመሆኑም ሰላም ያለው ጸጥታ ክፍሉን ሞላው:: በወዳጅነታችን መካከል ያለውን ክፍተት በቃላት ልንሞላው የምንችል ዐይነት አልነበረም::

በመጨረሻው ዴቪድ ራሱን በአዎንታ ነቀነቀና፤ "ስለዚህ ነገር አስቀድመህ ያልተናገርከው ለምንድን ነው?" ሲል ጠየቀኝ::

"ሁለት በጣም ጠንካራ የሆኑ ምክንያቶች አሉኝ:: አንደኛው በመንግስተ ሰማይ ስለነበረኝ ቆይታ እየዘርኩ ማውራት ብጀምር ሰዎች እንደ እብድ ይቆጥሩኛል:: "

"ግን ለምን እንደዚያ አሰብክ?" ለምሳሌ አሁን እኔ ሰማሁህ፤ እንደምትለው ግን አልቆጠርኩህም::

ሁለተኛው ምክንያቴ፤" አልኩት የጀመረውን አቋርጬው፤ "ስለዚያ ክስተት እንደገና መናገር ስለማልፈልግ ነው:: ... ማለቴ በጣም ግላዊ የሆነ ነገር ነው:: በጣም የተለየ:: ይህ ነገር እኔ ራሴ እንኳን ሙሉ በሙሉ ልረዳው የቻልኩት ነገር አይደለም:: እኔ ሁኔታውን ለመናገር ባለመፈለጌ ምክንያት አይደለም፤ ነገር ግን ይህን ማድረግ እንደምችል አላስብም::"

"ይህን ነገር ለሌሎች ማካፈል ካልቻልክ መንግስተ ሰማይን ያየኸው ታዲያ ለምን እንደሆነ ታስባለህ?"

"ለዚያ ጥያቄ መልስ የለኝም"

"ለምን?"

"ራሴን የጠየቅኩትን የተሻለ ጥያቄ ልነግርህ እችላለሁ፤ ለምን ወደ መንግስተ ሰማይ ገባሁ? ለምንስ እንደገና ከእኔ ተወሰደች? ያ ሁሉ ሁኔታ ለምን ተከሰተ? ምንስ ማለት ነው?" ለወራቶች በውስጤ ተቀብሮ የቆየ ልቆጣጠረው ያልቻልኩት ቁጣ ገንፍሎ ወጣ፤ ውስጣዊ ስቃዬ ሁሉ ገፍቶ ተገለጠ። ጥሩ፤ በዚህ ሁሉ ነገር ውስጥ ያለፍኩት ለምንድን ነው? ክብሩንና ውበቱን ተመልከቻለሁ፤ እጅግ ኃይል፣ በሕይወት ሊታይ ከሚችለው ነገር ሁሉ እጅግ በላጭነት ያለው ልምምድ ነው - እና ከዚህ ሁሉ በኋላ ተመልሼ መጣሁ። ለምን? ለዚህ?" ወደ እጄና ወደ እግሬ አመለከትኩት። ስማ ሕይወቴን ነጥቆ በወሰደ አደጋ ውስጥ ነበርኩ። ፊጥኜ ነበር ወደ መንግስተ ሰማይ የተጓዝኩት። እናም ከምገምተው በላይ ሁሉም ነገር እጅግ ታላቅና አስደናቂ ነበር። የመንግስተ ሰማይን አስገራሚ ውበት አይቻለሁ፤ እና እንደገና ተጎትቼ ወደዚህ ሕይወት መጥቻለሁ። አካሌ በብዙ ተጎድቷል። በማያቋርጥ የህመም ስቃይ ውስጥ ነኝ። ከዚህ በኋላ እንደገና ሙሉ ጤነኛና እንደቀድሞው ጠንካራ ልሆን አልችልም። አሁንም በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለፍኩ አለሁ፤ ምክንያቱም ... ምክንያቱም፤ እውነቱን ለመናገር ሁሉም ነገር ስቃይ ነው የሆነብኝ።"



ዴቪድ አትኩሮ ሲመለከተኝ ቆየና፤ "የመንግስተ ሰማይ ቆይታህን የማትናገር ከሆነ፤ ወደዚያ የሄድከው ለምን እንደሆነ ታስባለህ? ሲል ደገመና ጠየቀኝ።

"ቅድም እንደነገርኩህ ለዚህ ጥያቄ መልስ የለኝም" ።

"እግዚአብሔር ወደ መንግስተ ሰማያት የወሰደህና መልሶም ወደ ምድር ያመጣህ በአንተ የደረሰውን ነገር ሁሉ ለሰዎች እንድትናገር ሊሆን አይችልም? ለሌሎች ምን ያህል ታላቅ መጽናናት ልትሆን እንደምትችልስ አትገነዘብምን?"

የተናገራቸው ቃላት አስደነገጡኝ። በጣም አትኩሬ የነበረው በራሴ ላይ ነበር፤ ስለማንም ሌላ ሰው አስቤ አላውቅም። ምን እንደተሰማኝ ልነግረውና ለእራሴም ለማስረዳት በሞከርኩ ጊዜ ውስጤ ባዶ ሆኖ አገኘሁት። እናም በእርሱ ፊት ማልቀስ ጀመርኩ፤ ደግሞ ትክክል እንደነበር አውቃለሁ።

ከዚያ በኋላ ለሃያ ደቂቃዎች ያህል ተወያየንበት። ዴቪድ ይገፋፋኝ ጀመር፤ ምንም እንኳን ትክክል እንደሆነ ባውቅም፤ የመንግስተ ሰማይ ቆይታዬን ለመግለጽ ለእኔ ቀላል ነገር አልነበረም።

በመጨረሻው ዴቪድ፤ "ከእኔ ጋር ቃል ኪዳን እንድታደርግ እፈልጋለሁ" አለ።

"ምን አይነት ቃል ኪዳን?"

"በጣም ቀላል። የምታምናቸውን ሁለት ሰዎች ምረጥ። የመንግስተ ሰማይ ልምምድህን በጥቂቱ አጫውታቸው፤ ከዚያ በኋላ ምን እንደተሰማቸው የራስህን ግምገማ ውሰድ"። ሰዎቹ እንደ አብድ

ከቆጠሩኝ ወይም ቅዠታም እንደሆንኩ የሚቆጥሩኝ ከሆነ ከዚያ በኋላ ለማንም መናገር እንደማይገባኝ ገለጸልኝ::

"ነገር ግን በአንተ ደስ የሚላቸው ከሆነ" አለ፤ "ጨምረህ እንድትነግራቸው የሚጠይቁህ ከሆነ፤ ይህንን እንደምልክት እንድትቆጥረው እፈልጋለሁ፤ እግዚአብሔር በመንግስተ ሰማይ በቆየህባቸው ዘጠና ደቂቃዎች ያየኸውን ለሰዎች እንድትናገር መፈለጉን የሚያሣይ ምልክት:: " ጉዳዮን በጥንቃቄ ካሰለሰልኩት በኋላ ከእርሱ ጋር ቃል ኪዳን አደረኩ፤ "ያንን ማድረግ እችላለሁ::"

"መቼ? "

"ፈጥኜ እንደማደርገው ቃል እገባለሁ"::

"በጣም ፈጥነህ እንደምታደርገው እርግጠኛ ነህ? " ::

"ጥሩ፤ እንደማይዘገይ ቃል እገባለሁ"::

ዴቪድ ጸለየልኝ፤ እናም ሲናገር አደምጠው ነበር፤ በእርግጠኝነት አሸንፎኛል:: ጉዳዩ ከዚህ በኋላ የምርጫ ጉዳይ አይደለም፤ የግድ መናገር አለብኝ በራሴ መንገድ ላደርገው ግድ ነው::

በመጀመሪያ የተቀደሰውን ሚስጥሬን የማካፍላቸውን የማምናቸውን ሰዎች ወሰንኩ:: አንድ ጊዜ ቁጥራቸው ጥቂት እንዲሆን ከወሰንኩ በኋላ፤ አቀራረቤን ጥንቃቄ የተሞላበት አደረኩ:: የምነግራቸው ለእያንዳንዳቸው በግል መሆን እንደሚገባው አረጋግጫለሁ:: ጤንነቴ ትንሽ እስኪሻሻል ድረስ ጠበቅኩ፤ ደግሞም እለት እለት እየተሻለኝ ነበር:: ከዚያ በኋላ፤ "ታውቃለህ፤ በዚያ ቀን እኮ ሞቼ ነበር:: የነቃሁት



ደግሞ በመንግስተ ሰማይ ነው" የመሳሰሉትን ቀለል ያሉ ነገሮች መናገር ጀመርኩ::

የሰዎቹ ምላሽ ሁልጊዜም ተመሳሳይ ነበር፤ "እባክህ ጨምረህ ንገረኝ":: ሁልጊዜም ይህንን ቃል ይናገሩት ነበር ማለቴ አይደለም፤ ይሁን እንጂ የሚፈልጉት ይህንን ነበር:: ዓይኖቻቸው በአግራሞት ሲፈጡ እያለሁ፤ እናም ተጨማሪ መስማት ይፈልጋሉ::

ጥቂት ጨመር አድርጌ በነገርኳቸው ቁጥር፤ ስለ አእምሮዬ ጤንነት ተጠራጥሮ የጠየቀኝ ማንም የለም:: ማናቸውም ቢሆኑ ቅዥታም እንደሆንኩ አልተናገሩም::

"ይህንን ነገር ለሰዎች መናገር ይገባሃል አለኝ" አንደኛው::

"ይህ ያየኸው ነገር ለአንተ ብቻ አይደለም" ሌላው ጓደኛዬ ደግሞ አስተያየቱን ሰጠ:: "ለሁላችንም ነው:: ለእኔ ነው"::

በቀጣዮቹ ሁለት ሳምንታት እያንዳንዳቸውን ባዳመጥኩ ጊዜ፤ ወደ ኋላ ተመልሼ በሆስፒታሉ ውስጥ ጀይ በገለጹኝ ጊዜ የነበረውን ሁኔታ ማገናዘብ ጀመርኩ:: በዚያ ጊዜ ማንም እንዲረዳኝ አልፈቀድኩም፤ ያ ደግሞ ራስ ወዳድነት ነበር:: በዚህ ጊዜ ደግሞ በእኔ ሕይወት የሆነውን ነገር ለሌሎች እላካፈልኳቸውም ይህም ደግሞ ራስ ወዳድነት ነበር::

"ጥሩ፤ ስለዚህ ጉዳይ እናገራለሁ" ስል ለራሴ ቃል ገባሁ::

በአንጻሩ ደግሞ ሁሉም ሰው በመኪና አደጋ እንደደረሰብኝ ያውቅ ስለነበር፤ በመንግስተ ሰማይ የነበረኝን ቆይታ ለመናገር ውይይት እንደመክፈቻ አጋጣሚ ተጠቀምኩበት፤ በተለይም በመጀመሪያው አካባቢ

ስህተት ላለመፍጠር ጥንቃቄ አድርጌአለሁ:: ሰዎች ፍጹም ደስተኞች መሆናቸውን በማሳየት የድጋፍ ምላሽ በሰጡኝ ጊዜ፤ ታሪኬን ለማካፍላቸው ለሰዎች ይበልጥ ግልጽ እየሆንኩ ጥንቃቄ ከማድረግ እየላላሁ መጣሁ:: ነገሮችን ሁሉ ግልጽልጽ አድርጌ ማብራራት እንደሚጠበቅብኝ ስለማውቅ ሁሉን በግልጽ መናገር እፈልግ ነበር፤ ይሁን እንጅ ይህ ለእኔ ቀላል ነገር አልነበረም:: አሁን እንኳን ከዓመታት በኋላ በሕይወቴ የሆነውን ነገር በጥልቀትና በግልም ለመናገር ከተፈጥሮ አቅሜ በላይ ይሆንብኛል:: ዛሬ የመንግስተ ሰማይ ልምምዴን የምናገርበት ምክንያቶች አንደኛ ሰዎች ከጠየቁኝ ብቻ ነው፤ ይህም ብቻ ሳይሆን ያ ሰው በእርግጥ ሁኔታውን ለማወቅ መፈለጉ ከተለማኝ ጭምር ነው:: እንዲህ ካልሆነ አሁንም ቢሆን ለማንም አልናገርም::

ይህኛው የምክንያቱ ክፍል ይህንን መጽሐፍ ለመጻፍ ለብዙ ዓመታት በውስጤ ጉዳዩ እንዲብላላ ያደረገ ነው:: አሁን በሕይወት ያለሁበት ዋንኛ ምክንያት በመንግስተ ሰማይ የነበረኝ ልምምድና ወደ ምድርም የመመለሴ ነገር እንዲሆን አልፈለግኩም:: ይልቁን በተቃራኒው፤ ይህ ከሕይወት የተለመደ ነገር የወጣ ግላዊና ለእኔ ብቻ እጅግ ቅርብ የሆነውን ልምምዴን ወደ ኋላ ተመልሼ እያስብኩ ደጋግሜ መናገሩ ለእኔ የሚመች ነገር አድርጌ አልቆጠርኩትም::

ያንን የሕይወት ልምምዴን በአደባባይና በግልም ለሰዎች ተናግሬአለሁ:: የሆነውን ነገር አስመልክቼ ጽሑፍ አዘጋጅቻለሁ፤ ምክንያቱም በተለያዩ ምክንያቶቻቸው ታሪኬ ለእነርሱ ዋጋ ያለው ነገር መሆኑን በማወቄ ነው:: ለምሳሌ ያህል፤ በርካታ ሰዎች ባሉበት ሥፍራ በተናገርኩ ጊዜ፤ ቢያንስ ቢያንስ በዚያ ስፍራ በቅርቡ የሚወደው ሰው



የሞተበት እናም የዚያ ወዳጁ ፍጻሜ ምን እንደሆነ ማረጋገጫ የሚፈልግ አንድ ሰው ይኖራል::

ንግግሬን በምጨርስበት ጊዜ፤ እኔን ለማነጋገር ሰዎች ፈጥነው የሚሰሯቸው ሰልፎች አሁን ድረስ ይገርመኛል:: ወደ እኔ የሚመጡት እንባ በአይኖቻቸው ተሞልቶ ነው፤ በፊታቸውም ላይ የሃዘን ድባብ ያጠላበታል:: እነርሱ በሰላም እንዲሞሉና እርግጠኞች እንዲሆኑ ማድረግ በመቻሌ ደስታ ይሰማኛል::

የምናገራቸው ቃላት ወደሰዎቹ መረጋጋትን እንደሚያመጣ አምኜ ተቀብያለሁ፤ ይሁን እንጂ ይህንን አደርገዋለሁ ብዬ በጭራሽ አስቤውም አላውቅም:: ዴቪድ ጄንቲሊስ ባያበረታታኝ ኖሮ እርግጠኛ ነኝ እስከ ዛሬም ድረስ ቢሆን ለማንም አልናገርም ነበር::

እኔን በማነሳሳቱም ለእርሱ ምስጋና አቀርባለሁ፤ ምክንያቱም ውጤቱን በአምልኮ ጉባኤዎች ላይ ብቻ ሳይሆን በቀብር ስፍራዎች ላይ በተገኘሁባቸውም ሁኔታዎች ውስጥ ተመልክቼዋለሁ:: እንደ እውነቱ ከሆነ፤ ያ የሕይወት ልምምዴ የእኔንም የሕይወት ገጽታ በእጅጉ ለውጦታል:: በቀብር ሥፍራ ላይ አደርግ የነበረውን ነገር ቀይሬአለሁ:: አሁን ስለመንግስተ ሰማይ የአይን ምስክር በመሆኔ እንደ ባለ ስልጣን እናገራለሁ::

ተአምራዊ ከሆነው የግል ልምምዴ በተጨማሪ፤ በመንግስተ ሰማይ ጉዞዬ አማካይነት አራት ነገሮች ጎልተው ሊታዩኝ ችለዋል:: የመጀመሪያው በእርግጠኝነት እግዚአብሔር ጸሎትን እንደሚመልስ አምኛለሁ:: እኔ አሁን በሕይወት ያለሁት እግዚአብሔር ጸሎትን በመመለሱ ምክንያት ነው:: በሁለተኛ ደረጃ፤ እግዚአብሔር አሁንም ተአምራዊ በሆነ ሥራ ላይ መሆኑን ያለ አንዳች ተጠየቅ አምኛለሁ::

በጣም ብዙ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፉትን ተአምራት ካነበቡ በኋላ፣ "ይሄማ መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት ዘመን እግዚአብሔር የሠራበት መንገድ ነው" እያሉ ያስባሉ። እግዚአብሔር መደበኛ ከሆነው ነገር በላይ መሥራት መቀጠሉን እምኛለሁ። በእያንዳንዱ ቀን በተአምር በሕይወት ስለመኖሬ፣ መራመድ ስለመቻሌና መናገር ስለመቻሌ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ።

ሦስተኛ፣ በተቻለ መጠን ሁሉ ሰዎች ወደ መንግስተ ሰማይ እንዲገቡ እፈልጋለሁ። ሁልጊዜም መንግስተ ሰማይ እውን እንደሆነና ለእግዚአብሔር ህዝብ የተዘጋጀ ሥፍራ መሆኑን በሚያስተምሩ ክርስቲያናዊ አስተምህሮዎች አምናለሁ።

እኔ በዚያ ተገኝቼ ይህን የተመለከትኩ በመሆኔ ምክንያት የነገሩን ፍጹም እርግጠኝነት በግልጽ የመናገር ጠንካራ የሃላፊነት ስሜት ይሰማኛል። ሰዎች ወደ መንግስተ ሰማይ እንዲገቡ በመፈለጌ ብቻ አይደለም፣ አሁን አሁን ሰዎች በሞቱ ጊዜ ወዴት እንደሚሄዱ እርግጠኞች ይሆኑ ዘንድ ሕይወታቸውን በመክፈት እንድረዳቸው የመቻኮል ስሜት ይሰማኛል።

እንደ እውነቱ ከሆነ በአውራ ጎዳናዎች ላይ በአደጋ ስለሞቱ ሰዎች አስባለሁ፣ በወንጌል አገልግሎት ወቅት ሰዎች ለኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወታቸውን እንዲሰጡ ለማግባባት የዚህን አስከፊና አሰቃቂ ክስተት ታሪክ አንዳንዶች ይጠቀሙበታል። ይሁን እንጂ እኔ ከተለማመድኩት ሁኔታ አንጻር ስመለከተው፣ እንደዚህ አይነት አደጋዎች በሕይወታችን ውስጥ በማንኛውም ቅጽበት ሊያጋጥሙን የሚችሉ የሞት ምክንያቶች እንደሆኑ አይቻለሁ። ሰዎች ያለ ክርስቶስ ሆነው ሲሞቱ ማየትን አልፈልግም።



በመጨረሻውም አንድ ጊዜ፣ ዲክ ዋንሪከርና እኔ ስለዚህ አጣዳፊነት ተወያየንበት። ለምን እንደዚያ እንደሚሰማኝ ገባው። ከዚያ በኋላ፣ "ዲክ፣ ነፍሴን ስላተርፍካት እንደገና ላመሰግንህ እፈልጋለሁ። በዚያ ዝናባማ ቀን እግዚአብሔርን ስለመታዘዝህ የሚገባውን ያህል እንዳላመሰገንኩህ ግልጽ ነው።"

"ማንም ሰው ቢሆን ሊያደርገው የሚችለው ነገር ነበር።" አለኝ፣ ከዚያ በኋላ ማልቀስ ጀመረ።

"አንተ እንድታዝን ለማድረግ አልነበረም ይህን የተናገርኩት አልኩት። " እንደዚያ እንዲያለቅስ ያደረገውን ነገር ስለተናገርኩ በውስጤ ሀዘን ተሰማኝ። "በምድር ላይ ላደርገው ፈጽሞ የማልፈልገው ነገር ነው።"

"ያለቀስኩበት ምክንያት ያ አይደለም"

ሃሳቡን ለመሰብሰብ ረዥም ጊዜ ነበር የወሰደበት።

"ያለቀስክበት ምክንያት ምንድነው" ስል ጠየኩት።

"የአደጋውን ሁኔታ እያስታወስኩ ነበር፣ በዚያ ጊዜ ፖሊሱን ለአንተ መጸለይ እችል እንደሆን ጠየቅኩት፣ ማንኛውም ክርስቲያን ሊያደርገው የሚችል ነገር እንደነበር አስባለሁ። ምንም እንኳን እንደሞትክ ቢናገርም፣ ለአንተ መጸለይ እንደነበረብኝ አውቀው ነበር በርግጥ አውቀው ነበር። ተጎድተህ እንደነበረ ብቻ ነው አስብ የነበረው፣ እናም ከዚያ ሁኔታ እንድትወጣ እፈልግ ነበር። ለዚህ ነው ያልተለመደ ነገር እንዳደረግኩ የማልቆጥረው።"

"ነገር ግን አድርገሃል። ፖሊሱ አስቀድሞ መሞቴን በነገረህ ጊዜ ..."

"አንድ ጊዜ አድምጠኝ፤ ዶን። አንድ ትንሽ ልጅ በአስፋልት ላይ ሲሮጥ ብታየው፤ ባለህ ፍጥነት ሁሉ ሮጠህ የልጁን ሕይወት ለማትረፍ ትሞክራለህ። የሰው ተፈጥሮው እንደዚያ ነው። ሕይወት ተጠብቃ እንድትቆይ እንፈልጋለን፤ እድሉን ባገኘህበት በየትኛውም ጊዜ አሁንም ቢሆን አደርገዋለህ። አንተም ብትሆን ታደርገዋለህ።"

ተቀምጠን የነበረው በአንድ ምግብ ቤት ውስጥ ነበር፤ እናም ዙሪያውን ለመቃኘት ንግግሩን አቋረጠ። "እዚህ ስፍራ ላይ በብዙ ሰዎች ተከበን ተቀምጠናል ይሁን እንጂ ምናልባትም ብዙዎቹ የጠፉና ወደ ሲኦል የሚሄዱ ሊሆኑ ይችላሉ። እኛ ግን እንዴት የዘላለምን ሕይወት እንደሚያገኙ አንዲትም ቃል አንናገራቸውም። እኛ ትልቅ ስህተት እየሠራን እኮ ነው"

"ሙሉ ለሙሉ ትክክል ነህ" አልኩት። በሚታይ ሁኔታ አደጋ ውስጥ ያለን ሰው ልናድነው ፈቃደኞች ነን፤ ይሁን እንጂ ብዙ ወገኖቻችን መንፈሳዊ በሆነ ቀውስ ውስጥ ናቸው፤ እናም ከዚያ ሁኔታቸው ውስጥ ስለሚወጡበት መንገድ አንዲት ቃል አንተነፍስም"።

"አለቅስ የነበረው ለዚህ ነበር። ስለዝምታዬ፣ ለሰዎች ወንጌልን መናገር ስለመፍራቴና፤ ነገሮችን ለማድረግ ስላለብኝ ፍርሃት እየተወቀስኩ ነበር።"

ከዚያ በኋላ ዲክ ደግሞ ደጋግሞ፤ እኔ ስላለፍኩበት ሁኔታ ማወቁና እኔ ወደ ምድር በመመለሴ ጉዳይ ላይ እርሱ የተጫወተው



ሚና ነፃ እንዳወጣው ይናገር ነበር። ከዚያ በኋላ ከዚያ በፊት አድርጎት በማያውቀው ሁኔታ ስለ ኢየሱስ በድፍረት መናገር ይሰማዋል።

# 13

# አጥብቆ የያዘኝ እጅ

"ዓይኖችህ ያዩትን እነዚህን ታላላቆች፣ የሚያስፈሩትንም ነገሮች ያደረገልህ፤ እርሱ ክብርህ ነው፤ እርሱም አምላክህ ነው"

ዘዳ 10÷21

አደጋው ከደረሰብኝ ከአንድ ዓመት በላይ ከሆነው በኋላ፤ በክሌን የመጀመሪያው መጥምቃውያን የዲክ ቤተክርስቲያን ውስጥ ታሪኬን ለማካፈል ዕድል አግኝቼ ነበር። የዲክ ባለቤት አኒታና የእኔም ቤተሰቦች በዚያ ተገኝተው ነበር። በእግር አጥንቶች መደገፊያውን ብረት አጥልቄ ስለነበር ወደ መድረኩ ላይ የወጣሁት በሁለት ሰዎች ተደግፌ ነው።

እዚያ ለነበሩት ሁሉ ስለአደጋውና የእኔን ወደ ምድር መመለስ አስመልክቶ ዲክ የነበረው ሚና ምን እንደነበር ተረኩላቸው። "ዛሬ በሕይወት ልኖር የቻልኩበት ምክንያት ዲክ ወደ ምድር እንድመለስ ስለጸለየልኝ እንደሆነ አምናለሁ" አልኳቸው። "ወደ አዕምሮዬ በተመለስኩባት የመጀመሪያዋ ቅጽበት ሁለት ነገሮች ሆነው ነበር። የመጀመሪያው፤ ከኢየሱስ ጋር ያለን ወዳጅነት እንዴት ድንቅ ነው። የሚለውን ዝማሬ እየዘመርኩ ነበር፤ ሁለተኛው ደግሞ የዴክ እጅ የእኔን እጅ አጥብቆ ጨብጦ ይዞ ነበር።"



ከጠዋቱ የአምልኮ ጊዜ በኋላ ብዙዎቻችን በአንድነት ሆነን ምሳችንን ለመብላት ወደ ቻይና ምግብ ቤት አመራን። አኒታ ከእኔ ፊት ለፊት ተቀምጣ ነበር። በዚያ የቀረበልኝን ሾርባ እየተመገብኩ ከቤተክርስቲያን አባላት ጋር የነበረኝን አስደሳች ጊዜ አስታውሳለሁ። የንግግር ልውውጣችን ለአፍታ ጋብ ሲል አኒታ ወደ ጠረጴዛው ተጠግታ ዝቅ ባለ ድምጽ፤ "በዚህ ጠዋት ስለተናገርካቸው ነገሮች ሁሉ ከልቤ አመሰግንሃለሁ" አለች።

"አመሰግናለሁ"

"አንድ ነገር ግን አለ ... በመልዕክትህ ውስጥ ከተናገርከው ነገር ሳርምህ የሚገባው አንድ ነገር ግን አለ።"

"በእውነት?" የተናገረቻቸው ቃላት አስደንግጠውኝ ነበር። "በተቻለኝ መጠን በንግግሬ ሁሉንም በትክክል ለመግለጽ ሞክሬአለሁ። እንደ እውነቱ ከሆነ ምንም አይነት የተጋነነ ነገር አልጨመርኩም። የተናገርኩት የተሳሳተ ነገር ምን ነበር?"

"ዲክ ወደ መኪናው ውስጥ ገብቶ ከአንተ ጋር እንደነበር ተናግረሃል፤ በተጨማሪም እጅህን አጥብቆ እንደያዘ ይጸልይልህ እንደነበር ስትናገር ነበር።"

"አዎን፤ ያንን ነገር በተለይ በትክክል አስታውሰዋለሁ። ብዙ የማስታውሳቸው ነገሮች ነበሩ፤ እንዲያውም አብዛኛዎቹን ነገሮች አላስታውሳቸውም" በዚያ ጠዋት ስለሆኑት አንዳንድ ነገሮች መረጃ ያገኘ ሁት በስፍራው ከነበሩ ሰዎች ነው። "እጅግ ግልጽ የሆነው አንድ ነገር

ግን፤ ዲክ በመኪናው ውስጥ ተገኝቶ ከእኔ ጋር ይጸልይ እንደነበር ነው::"

"ያ ትክክል ነው:: ወደ መኪናው ውስጥ ገብቷል:: ከአንተም ጋር ጸልዮአል::" ወደ እኔ በጣም ቀረብ አለችና፤ "ነገር ግን ዶን፤ በጭራሽ እጅህን አልያዘም ነበር::"

"ግልጽ በሆነ ሁኔታ እጄን ይዤ እንደነበር አስታውሳለሁ"

"የሆነው እንደዚያ አልነበረም:: በአካል ያንን ለማድረግ አይቻልም"

"ነገር ግን ያንን በትክክል አስታውሳለሁ፤ በጣም ግልጽ ከሆኑት ..."

"እስኪ አንድ ጊዜ አስበው:: ዲክ ያደረገው በኋለኛው መቀመጫ በኩል ሆኖ በደረቱ በመጠጋትና እጁን በመዘርጋት በአንተ ትከሻ ላይ ነው ያሳረፈው:: ፊትህ ወደፊት ተደፍቶ ነበር፤ የግራ እጅህ ደግሞ እርስ በእርሱ የተያያዘው ላመል ያህል ብቻ ነበር::"

"አዎ፤ ያ እውነት ነው"

"ያን ጊዜ ተዘርረህ የነበረው ከአሽከርካሪው አጠገብ ባለው የተሣፋሪ መቀመጫ ላይ እንደሆነ ዲክ ተናግሯል"

አይኖቼን ጨፈን አድርጌ እየተናገረች ያለችውን ነገር በአዕምሮዬ በመሳል ለመመልከት ሞከርኩ:: እናም በአዎንታ ራሴን ነቀነቅኩ::

"ቀኝ እጅህ በተሣፋሪው መቀመጫ በኩል ባለው የመኪናው ወለል ላይ ነበር:: ምንም እንኳን መኪናው የተሸፈነ ቢሆንም በዚያ



የተጋደመውን እጅህን ለማየት በቂ ብርሃን ነበር:: ዲክ ያንን እጅህን ለመያዝ እጁ ሊደርስ የሚችልበት ምንም መንገድ የለም"

"ግን ... ግን ... ድምጼ በፍርሃት ይቆራረጥ ጀመር:: "አንድ ሰው እጅህን ጨብጦ ይዞ ነበር:: ነገር ግን ዲክ አልነበረም!"

"ያ እጅ የዲክ ካልነበረ፤ የማን እጅ ነበር?"

ፈገግ ብላ "እንደምታውቀው አስባለሁ" አለች:: የሾርባውን ማንኪያ አስቀመጥኩና ለበርካታ ሰከንዶች አትኩሬ ተመለከትኳት:: ማንም ይሁን ማን አንድ ሰው እጄን አጥብቆ ይዞ እንደነበር አልጠራጠርም:: ከዚያ በኋላ ነገሩ ገባኝ:: "አዎ፤ እኔም እንደ ማውቀው አስባለሁ::"

ወዲያውኑ በዕብራውያን መጽሐፍ ላይ አንዳንዶች ሳያውቁት መላእክትን በእንግድነት እንደተቀበሉ የሚናገረውን ጥቅስ አስላሰል ጀመር:: በጥልቅ እያስላሰልኩ እያለሁ፤ መንፈሳዊ ገለጻ ብቻ ሊፈታቸው የሚችል ሌሎች ክስተቶችንም ማስታወስ ጀመርኩ:: ለምሳሌ ያህል፤ በሆስፒታሉ ክፍል ውስጥ እጅግ ብዙ ጊዜ በውድቀት ሌሊት በከፍተኛ ስቃይ ውስጥ እሆናለሁ:: ማንንም አላይም ወይም የማንንም ድምጽ አልሰማም - የሆነ ማንነት ህልውና ግን ይሰማኛል - የሆነ ነገር - የሆነ ስብእና - የሚደግፍ የሚያጽናና:: ይህንንም ነገር ተናግሬው የማላውቀው ነገር ነበር:: ልገልጸው የምችለው ነገር አልነበረም፤ በመሆኑም ሰዎች ሊረዱት አይችሉም ብዬ እገምት ነበር::

ይህ ሌላኛው ተአምር ነበር:: አኒታ ባታርመኝ ኖሮ ላውቀው አልችልም ነበር::

ከአደጋው በኋላ አምስት ዓመት ያህል ቆይቶ፤ እኔና ዲክ ሁለታችንም ፖት ሮበርትሰንስ 700 ክለብ በሚል የቴሌቭዥን ፕሮግራም ቀርበን ነበር:: የፊልም አንሺ ቡድን ወደ ቴክሳስ መጥቶ የነበረውን ክስተት እንደገና እንድንደግመው በማድረግ ፊልሙን አንስቶ ነበር:: በተጨማሪም በመንግስተ ሰማይ ስለነበረኝ ቆይታ ጠይቀውኛል:: የ700 ክለብ ከዚያ በኋላ በነበሩ ሁለት ዓመታት ውስጥ ያንን ታሪክ ብዙ ጊዜ ደጋግሞ በአየር ላይ ለቆታል::

በሕይወት እጅግ አስደናቂ ከሆኑት እንቆቅልሾች አንዱ ተከናወነ፤ በ2001 ዲክ በልብ ድካም በሽታ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ:: ሞቱን በሰማሁ ጊዜ እጅግ ማዘኔን እናዘዛለሁ፤ ነገር ግን አሁን በክብር ስላለ ደስተኛ ነኝ:: ዲክ የእኔን ሕይወት አዳነ፤ እናም እግዚአብሔር እርሱን አስቀድሞ ወደ መንግስተ ሰማይ ወሰደው:: ወደ መንግስተ ሰማይ የሚያደርገውን ጉዞ ከመጀመሩ በፊት የእኔን ምስክርነት በመስማቱ ተደስቼ ነበር::

ከአደጋው በኋላ አንድ ዓመት በላይ ቆይቶ ከአኒታ ጋር ያንን ጭውውት ካደረግን ወዲህ፤ እግዚአብሔር ወደዚህ ምድር የመለሰኝ ለዐላማ መሆኑ ከመቼውም ይልቅ እያሳመነኝ መጣ:: መልአኩ የእኔን እጅ መያዙ፤ ምንም እንኳን ነገሮች ከባድ እየሆኑ ቢሄዱም እንደማይተወኝና እንደሚደግፈኝ እንዳውቅ የተጠቀመበት መንገድ ነበር::

ምናልባትም ያ እጅ በእያንዳንዱ ቀን እንደያዘኝ አይታወቀኝ ይሆናል፤ ነገር ግን ከእኔ ጋር እንዳለ አውቃለሁ::



# 14

# አዲሱ ሕይወት

"እኔ ጤናህን እመልስልሃለሁ፤ ቁስልህንም እፈውሳለሁ፤ ይላል እግዚአብሔር ማንም የማይሻት፣ የተጣለች ጽዮን ብለው ጠርተውሻልና"

ኤር 30፥17

ፈጽሞ ልናገግም የማንችልባቸው አንዳንድ ነገሮች ወደ እኛ ይመጣሉ፤ እናም የተለመደውን የሕይወት ምልልስ ያናውጣሉ:: እንግዲህ ሕይወት እንዲህ ናት::

የሰው ተፈጥሯዊ ባህሪ የቀደሙ ነገሮችን መልሶ የመገንባትና የተውናቸውን ነገሮች ከጣልንበት ሥፍራ እንደገና የመሰብሰብ ዝንባሌ አለው:: አስተዋዮች ብንሆን ኖሮ ነገሮችን ቀድሞ ወደነበሩበት ሥፍራ ለመመለስ ጥረታችንን እንቀጥልም (ብንሞክርም አይሳካም):: ከዚያ ይልቅ የቀደመውን የተለመደ ነገር እየረሳን አዲሱን ሕይወት መቀበል ይገባናል::

ጤነኛ የነበርኩበትንና አንዳችም አካላዊ ችግር ባልነበረብኝ ጊዜ የነበረኝን ሁኔታዬን ብዙ ጊዜ በማሰብ እጅግ ብዙ ጊዜ አጥፍቻለሁ:: በአዕምሮዬም፤ ሕይወት ምን መምሰል እንደነበረባት እንደገና እቀርጻለሁ፤ እውነታው ግን ከዚያ በኋላ ሕይወት እንደቀደመው እንደማይቀጥል አውቅ ነበር:: አካላዊ ጉድለቶቼን እንደ አዲሱ ሕይወቴ